ማስመሰያው እንደማይሠራ ሲያሳምነው ብዙ ጥረት አድርጓል። እንዳለውም ጫን ብሎ እየሠራ አይደለም።

"ለዛሬው ጨርሰናል" አለው ዘሩባቤል።"

"እየተከታተልኩ የደረስኩበትን እገልጽላችኂለሁ።" መውጣቱን ስታረጋግጥ ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ዘሩባቤል መጣች።

"ምን ይመስልሻል?" አላት ፊቷን እያጠና። ትክሻዋን ነቅነቅ አደረገች "ይህቺ ፊጠራ የሱና የዚያ ጠማማ ይሁዳ አለቃው እንደምትሆን አልጠራጠርም።"

በመስማማት ራሱን ነቀነቀ። ዘሩባቤል ሁሉንም ነገር ነካክቶ ራሱን አጣብቂኝ ውስጥ ከትቷል። ወሮበላዎቹና ከምሽት ክበብ ያያቸው ሰዎች ሁሉ ነፍሱን የሚፈልጉ ሆነዋል።





# ምእራፍ አሥራ ሰባት

በየደቂቃው በሚንጫረር የስልክ ጩኸት የመረጃ ቁርጥራጭ ጥንቅራቸው እንዲቆራረጥና ስሜት እንዲያጣ አይፈልግም። አዕምሮው ክፉኛ ተወጥሯል። በምንም ነገር መረበሽ የለበትም።

"የደላላ ስልክ ይመስል" አለ ዘሩባቤል በመነጫነጭ ስሜት። ይቅርታ በሚጠይቅ መልኩ ከአስተዋላቸው በኋላ ከተቀመጠበት ተነስቶ ከሳሎኑ ፊት ለፊት ያለውን የገላ መታጠቢያ ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ። መደወል በነበረበት ሰዓት ነው የደወለለት። ሁሉም ነገር ተጠናቅቆ መሆን አለበት። ሙሉ የአንድ ሰዓት ጊዜ ተጠቅመዋል። "ፈጣሪ -ኧ-ኧ-ኧ ሳጥናኤል አንተ መልካም ነገር ለጆሮዬ አሰማኝ" በልቡ አጉተመተመ። ብዙ ሚሊዮን ዶላር ከፊት ለፊቱ ተደቅኖበት ከተደበላለቀው ስሜቱ ጋር ተፋጠጠ። ቶሎ ደውሎ ውጤቱን ማወቅ አለበት። በግብርህ ለመጀመሪያ ጊዜም ቢሆን ሰውን ለማስደሰት ሞክር እባክህ ደግ ነገር አሰማኝ። የተማጸነው ሳጥናኤልን ነበር። ቁጥሩን እየደጋገመ በጥንቃቄ አስተዋለው። እርግጠኛ ነው።

ብሔራዊ ባንክ ለሚሠራው የሥራ ባልደረባው ነው የደወለው።

ከትንሽ ሰኮንዶች በኋላ ስልኩ ተነሳና ድምጽ ከወድያኛው ጫፍ እየተቆራረጠ ወደ ጆሮው መጣ።

"ከዋናው ብሔራዊ ባንክ ጊዜያዊ የጸጥታ ቢሮ..." ንግግሩን ቆም አድርጕ አደመጠ።

የሚጠብቀው ጥሪ ነበር። የሚለውን ለመስማት ጆሮውን ብቻ ሳይሆን ልቡንም ከፈተና አቆበቆበ።

"አዲስ ነገር አለ እንዴ? ዝም አልከኝ እሳ?" አለው።

"ጉዳዩ አብቅቷል" ባጭሩ መለሰለትና በረጅሙ ተነፈሰ።

"ተሳክቷል እያልከኝ ነው..." ልቡ ክፉኛ እየደለቀበት ጠየቀው።

"በታቀደለት መንገድ ተጠናቅቋል።"

የሚጠብቀው ቢሆንም መላ ሰውነቱ ሲረበሽበት ውስጡ ሲናጥ ተሰማው። አደገኛ ውቅያኖስ ውስጥ ለምን እራሱን መወርወር እንደ ፈለገ በርግጠኝነት የተረዳው ዘግይቶ ነው። አፉን የመረረ ወፍራም ምራቅ ሲሞላው ታወቀው። ልግ የተባለው ወፍራም ምራቅ ነበር። በመጸዳጃ ሳህኑ ውስጥ ተፋ። ሁሉም ነገር በፊት እንዳሰበው ቀላል አልነበረም። ከፊት ለፊቱ ከተሰቀለው መስታወት ላይ ለሰከንድ አፍጥጦ የገዛ ምስሉን ተመለከተ። መጣጣ ሪዛም ፊቱ የመከራ ያህል ከብዶ በተቆጣጠረ ሪዙ ተሸፍኖ ሲመለከት ደነገጠ።

ስህተት ሰርተሃል እያለ የሚያስፈራራው እስኪመስለው ድረስ የገዛ ገጹ አሸማቀቀው። በዚህ ሁኔታ ሲመለከተው እራሱን ለራሱ ሳያስጠላው አልቀረም።

ከመጠን በላይ ያደገው ጺሙ ከአጥንት ላይ የሰፈረ ጉንዳን እንጂ የራሱ ፀጉር አልመሰለውም። ረጅም የነፍጠኛ ጎራዴ መሳይ አፍንጫው የመሬት አካልን የከፈለ ቱራራ መስሎ ከሲታ ሪዛም ፊቱን ለሁለት ሰንጥቆ በመውረድ ከጫፍ ወደ ግራ በኩል ተጣምሟል። በአውራና በሌባ ጣቱ መካከል አስገብቶ እንደ መጫን አደረገው። ቅርጽና ይዘቱን መለወጡ አስደነገጠው።

"እስከዚህ ድረስ?" ከምን የተነሳ ነው አፍንጫዬ እንደ አጋዘን ቀንድ የተጠማዘዘው? ይህ አስገራሚ ነገር ነው። በሌባና በአውራ ጣቱ ጫፍ ያዘና እየደጋገመ ወደታች በመላግ እንደ ማስተካከል አደረገው።

"የሞኝ ሥራ" አለ ለራሱ። ከትልቅ ጭንቅላቱ ላይ ያለው አፍሮ ጸጉሩ የራስ ቅሉን የበለጠ አክብዶታል። መልኩ የቀይ ዳማ ተብሎ የሚጠራ ነው። ተራርቀው የበቀሉት ጥርሶቹ ጫትና ሲጋራ አብልዟቸው የዛገ ብረት መስለዋል። በሲጋራ ጢስ የበለዘው ከንፈሩ ከተጠበሰ ጉበት ይጠቁራል። ገጽታው የሚጠቁመው ምሁርነቱን ሳይሆን ብልጣብልጥና መሰሪ ተንኮለኛነቱን ይመስላል። 'እህል ለወዳጁ' አይሆንም የተባለው ተረት ለሱ እንደ ተነገረ ሁሉ እየበላና እየጠጣ ውስጡን ይሰርቀዋል። አጥንቱ ላይ የቀረው ቆዳ ብቻ ነው ብሎ ለመናገር ያስደፍራል።

"ሴቶች እየቀረቡ የሚሸሹትም በዚሁ አስፈሪ ገጽታው እንደሚሆን ያምናል። ለገንዘቡ ካልሆነ በቀር አንድም ሴት እሱን ወዳውና አፍቅራው እንደማትቀርበው ያውቃል። በትላልቅ አጥንት የተወነጋገረ አካላት ምኑ ይፈቀራል። በእሱ እምነት ሴቶች ገንዘብ እንጂ ፍቅር አያውቁም። ዕድሜ ለሥራ ይላል። የፈረንጅ ሽማግሌ ስትጎትት ለምትውል የአበሻ ሴት ስለ ውበት መጨነቅ ትክክል አይደለም። ገንዘብ አሁንም ገንዘብ የዘመኗ ወጣት ገንዘብን ከፍቅር እንደምታስቀድም ያውቃል። የገንዘብ እንጂ የፍቅር ልብ ያላት ሴት እንደሌለች ያምናል። በቃ ብር ብር አሁንም እየሠራ ያለው ለብር ነው። ለዚህ ብር ካልሞተ እና ካልተዋደቀ ለምን ሊወድቅ ነበር? በመልኩ ከተደነቀ ወጣት ይልቅ ብር ያለው ሽማግሌ ሴቶችን እንደ ልቡ ማፈራረቅ ይችላል። የአበሻ ሴቶች ውበት እንጂ ሞራል የላቸውም የሚል እምነት አለው። የእነሱን ውበት ከሱቅ እንደሚገዛው ዕቃ አድርጎ ነው የሚገምተው። መልክና የሥልጣን ኃላፊነት ሁሉም ነገር ጀሃነብ መግባት ይችላል። ሁሉም ነገር ወደ ገንዘቡ… ትምክህቱንና ፍላጎቱን በገንዘቡ ላይ እንደቆለለ ከመታጠቢያ ክፍሉ ወጣ። በሆነው በተደረገው ሁሉ ተደስቷል ያም ሆኖ እጅግ እየተረበሸ ነው። ይህ መዘዘኛ ተውሳክ እንደ ጥላው ይከታተለዋል። ሊያጠፋው ብዙ ጊዜ ያቀደ ቢሆንም አልተሳካለትም አሁን ጭራሽ ደላላ እያለ በአሽሙር መውጋት ጀምሯል። ቆይ አለ ደገመና።

ሠልጥነው ከተመረቁት የመረጃና የጸጥታ ሠራተኞች አንደኛው ነው። ሌሎቹ በየተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ተሰግስገው እንዲሠሩ ሲደረጉ እሱ





ግን በአገር ውስጥ የደኅንነት ቢሮ በሦስተኛነት ደረጃ ኃላፊነት ተጥሎበት ሥልጣኑን ተረከበ። ሕዝብና አገሩን ከአደጋ ለመጠበቅ ቃልኪዳን ገብቶ ኃላፊነትን የተረከበው ከዓመታት ቀደም ብሎ ነበር። ከአሜሪካን እንደተመለሰ ለተወሰኑ ጊዜያት ሠርቶ ለተጨማሪ ኮርስ ተመልሶ ሄዶም ነበር። ለአንድ ዓመት ያህል ልዩ ሥልጠና ከወሰደ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሷል። ሳምሶን ደበሌ የአርባ አምስት ዓመት ጉልማሳ ነው። ለትምህርት ከሱ ጋር የሄዱት አሥራ አምስት ቢሆኑም ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ አገር የተመለሱት አሥሩ ብቻ ናቸው። አምስቱ በዚያው በወጡበት የመቅረታቸው ምሥጢር አይታወቅም። ከአሥሩ ሦስቱ በዋናው የጸጥታ ቢሮ እየሠሩ ሲሆኑ ሰባቱ በተለያዩ መሥርያ ቤቶች ስውር የመረጃ ሠራተኛ በኢትዮጵያውያን አነጋገር ጆሮ ጠቢ ሆነው የተመደቡ ናቸው።

በአሜሪካን የሲአይኤ ቢሮ በየዓመቱ የዚህ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች ለኢትዮጵያ በነፃ ያሰለጥናል። አርባ አምስተኛ ዕድሜውን እያገባደደ ያለው ሰው ሥልጠናቸውን እንደ ጨረሱ ወደ አገር እንመለስም በማለት አሜሪካን አገር ከጠፉት ጓደኞቹ ጋር ለመቅረት አስቦም ነበር። በዚያው መቅረቱን ባይጠላውም በቤተሰቦቹ ላይ ችግር ሊደርስባቸው ይችላል የሚል ስጋት ስለ ገባው ወደ አገር ቤት ለመመለስ ተገደደ። ጠፍቶ የመቅረት አሳቡን ካመነጩት መካከል አንደኛው እሱ ቢሆንም ለአንድ ልጁና ለሚስቱ ሲል ወደ አገር መመለሱን የወሰነው ብዙ ካሰበበት በኋላ እንደ ነበር ያስታውሰዋል። አሳቡን ሰርዞ ወደ አገሩ በመመለሱ ጓደኞቹ እንደ ከሃዲ ቢቆጥሩትም ትክክለኛ ምርጫ እንደ ሆነ በመጨረሻው ሰዓት ነግሯቸው ነው የተለያዩት። የህሊና ጸጸት አላደረበትም። ከተሳካ በፈረንጅ አገር ሳህን እያጠበ ከሚያገኘው የበለጠ የተሻለ ነው። ይህ የሚሆነው ታድያ ድራማው በትክክል ከተተወነ ብቻ እንደሚሆን ይረዳል።

ከመጸዳጃ ክፍል የተመለሰው ከሚያገኘው ሀብት በተጨማሪ የተለያዩ ነገሮች አዕምሮውን ወጥረው እንዳስጨነቁት ነበር። የአካልና የመንፈስ ጥንካሬው እንደ ጉም እየተነነ ከላዩ ላይ የተነሳ እስከሚመስለው ድረስ ሰውነቱን ቀለለው። የአገሪቱ የምሥጢራዊ ኮድ የምርመራ ዘዴ ባለ ሙያ ምርጥ ሰው ተብሎ በአንድ ወቅት ከአገሪቱ ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ተሸልሞም እንደ ነበር ሁሉም ያውቃሉ። የዚህች ሀገር አለኝታ እየተባለ ያልተጠቀሰውን ያህል እጁን የፊጥኝ ተጠፍሮ እንደ ታሰረ ዘብጥያ ሲወርድና በአገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን ምስሉ ለሕዝቡ እይታ ሲቀርብ ያለውን ትርዒት በዓይነ ልቦናው እየደጋገመ ተመለከተ። ሥርዓት የለሽና ለሙያቸው ሳይሆን ለአለቆቻቸው ለሕሊናቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ያደሩ የሚላቸው ጋዜጠኞች እየተቀባበሉ የስድብ ናዳ ሲያወርዱበት አስቀያሚ ድምጻቸው በሕሊናው ደወለበት። ያልተጠየቁትን

ያልተባሉትን የሚለፈልፉ በቀቀኖች መሆናቸውን ያውቃል:: በሱ ዕምነት በነዚህ ወራዳ ፍጥረቶች ሊጥ ስትደፋ እንደተያዘች ውሻ መደበቂያ ሲያሳጡት የከበረው ዝናው ሲጎድፍ ከፊት ለፊቱ ብኸ እያለ ምስሉ እየደጋገመ መጣበት:: ሳይታሰብበት ሚሊየነር የመሆን ምኞቱ ዕድሜ ልኩን ከማይወጣበት ጦስ ከቶታል:: የሚጠብቀው ዝናና ክብር ሳይሆን ዘብጥያ መውረድ ብቻ ነው:: ዘሩባቤል የሚባል የማይድን ነቀርሳ ጥሎበታል::

"ስልክ እየፈለገህ ነበር:: ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት መሰለኝ::" በሌባ ጣቱ ወደ ስልኩ እጀታ እየጠቆመው ተናገረ ረዳቱ::

"ክፍት ነው?" በመደናገጥ ዓይነት ተመለከተው::

"ይመስለኛል::" ሲል መለሰለት::

የስልኩን እጀታ አነሳና የድምጽ ማስተላለፊያውን በመዳፉ በማፈን ረዳቱን አትኩሮ ተመለከተው::

"ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት መደወሉን በምን አወቅህ?" ትላልቅ ዓይኖቹን እያጉረጠረጠ ጠየቀው::

"አንስቼው ነበር::" አንገቱን ደፋ አደረገ::

"ስልክ ማንሳት ከየት የመጣ ልማድ ነው?" በብሽቀት አንክራፋ::

"ለስህተቴ ይቅርታ" አለው ከወንበሩ እንደ መነሳት እያለ::

የሰጠው መልስ የበለጠ አበሽቀውና ቢሰድበው ወደደ:: ወኔው ከበረዶ እየቀዘቀዘበት ስለ ነበር እንደዚያ ለማድረግ አልደፈረም:: የተሰላቸ በሚመስል ስሜት በድጋሚ ተመለከተው:: ቀኑ ደመናማና ቀዝቃዛ ቢሆንም እጁን ሁሉ እያላበው ነበር:: ከፊት ለፊቱ እንደ ሕልም እየመጣ ያለው መጥፎ ዕድል ስቃዩን ለማብዛት ያሴረበት መሰለው::

"ሄሎ" አለ በተቆራረጠና በሻከረ ድምጽ::

"ሄሎ ከጠቅላይ ምኒስቴር ጸጥታ ክፍል" ቀጭንና ጥርት ያለ የሴት ድምጽ ነበር ከወድያኛው ጫፍ የመጣው:: የሚጠላው ሰውም አጠገቡ ነው::

"አቤት አውቄለሁ" እንደ መደነጋገር አለ::

"አንድ ጊዜ ጠብቅ::" አለችውና የሴቷ ድምጽ ተቋረጠ::

ባለ ሥልጣኑ የበላይነቱን በሚገልጽ ትእዛዝ "በግል ስልኬ ደውል::" አለውና ዘጋ::

"መጥፎ ዕድል" አለ ለራሱ:: "መጥፎ አጋጣሚ ያቺ ቀን የተረገመች ትሁን::" የትኛዋን የተወለደባትን ወይስ ወደ ሕገወጥ ሥራ የገባበት? ለራሱም ግልጽ አልነበረም:: ብቻ ያችን ቀን አምርሮ ረገማት::

ከወዲኛው የስልክ ጫፍ እየመጣ ያለው ድምጽ የተረጋጋ ቢሆንም ቁጣው በነበረበት ነው::

"ምን እየሠራህ ነው?" ስሜቱን እየደፈጠጠ ጠየቀው::

መልስ ለማግኘት በፍለጋ ላይ እንዳለ ቃላቱን ደገመለት::

"ምን እየተፈጠረ እንደ ሆነ ታውቃለህ?" በዚያው የተረጋጋ





በሚመስል ድምጽ ጥያቄውን አከለለት::

"ምን.... ተፈጠረ?" እየተንተባተበ የተናገረው ያልተገባ ቃል እንደ ነበር የተከሰተለት ዘግይቶ ነው::

"ምን እንደ ተፈጠረ አታውቅም ማለት ነው? እንዳልከው ያልሰማህና የማታውቅ ከሆነ ዕድለኛ ሰው ሳትሆን አትቀርም:: በአስቸኳይ እንድትመጣ እፈልጋለሁ::" ለተወሰኑ ሴኮንዶች ያህል ጸጥታ ሰፈነ::

አፉ በግማሽ ተከፍቶ እጁ ከስልኩ እጀታ ላይ ተጣብቆ ቀረ:: ዓይኖቹ ወደ ውጭ ፈጥጠው በወጥመድ የተያዘች አይጥ መሰለ:: ሁኔታው ለጥያቄ የሚጋብዝ ሳይሆን ጭንቀትን የሚለቅ በመሆኑ አልጠየቁትም::

"ከይቅርታ ጋር" አለ ግራ በተጋባ በሚመስል አኳኋን "ከይቅርታ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ከቢሮ ውጭ ትጠብቁኛላችሁ::" የስልኩን መነጋገሪያ በመዳፉ አፍኖ ረዳቱንና ዘሩባቤልን በየተራ ተመለከታቸው:: ሁለቱ ሰዎች ተነስተው ወጡ:: ያወራው ለትንሽ ደቂቃ ቢሆንም የዓመት ያህል ረዝሞበት ነበር:: ስልኩን ዘግቶ ለማሰብ ሲሞክር አንዲት ሴት በሩን ከፍታ ገባች:: ሴትየዋ የሰውነቷን ቅርጽ አጉልቶ ያወጣ ጥቁር ቀሚስ የለበሰች መልከግቡ ነበረች:: የደረበችው ሹራብ መንታ ጡቶቿን እንደተደገነ ቀስት ወጥሮ ይዟቸዋል:: ውብ ልትባል የሚገባትና ረጅም ጸጉር ያላት የቀይ ዳማ ቦግ ቦግ ያሉ ትላልቅ ዓይኖችና የእንቁላል ቅርጽ ያለው ሰልካካ ፊት አላት::

"የተረገመች ነጠላ" ክፉኛ ረገማት::

"በተወጣጠርኩበት ቀን ትመጣለች?" አምላኬ ምን ዓይነት ውበት ነው?...!!" አመንዝራ ልቡ የቀደመውን ጭንቀቱን እንደ ጉም አትንኖ አውጥቶለት ድንጋጤውን ስሜቱ አሸንፎት ሲወጣ ተሰማው በስሜት አፉን መክፈት ጀመረ::

እጇን ለሰላምታ ስትዘረጋለት እንደ መደነጋገር ሲል ልቡ የተንደፋደፈች መሰለው::

"ከጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ነው የመጣሁት:: የሀገር ውስጥ የደኅንነት ምርመራ የፖሊስ አባል ነኝ:: በአገሪቱ ውስጥ የማህበራዊና የጸጥታ ቢሮ አብሮን ይሠራል:: የናንተ መሥርያ ቤት ከእኛ ጋር ብዙም ጥምረት ስለሌለው እኔን ልታውቀኝ አትችልም:: እኔ ግን በደንብ አድርጌ አውቅሃለሁ::"

እያንዳንዷን ቃላት እንደ ቀስት ጥይት ስታስወነጭፋቸው ወደ ሰውነቱ እየሰረሰሩ ሲገቡ ተቀስቅሶ የነበረው ስሜቱ መልሶ እንደ ፊኛ ሲሟሽሽ ታወቀው::

"እንዳንቺ ያለች ብዙ ልምድ ያላት ሴት ወደኔ በመምጣትዋ ደስተኛ ነኝ::" በእጁ ወደ ወንበሩ አቅጣጫ እየጋበዛት ተናገረ:: ሳምሶን ደበሌ::

"የወይንሸት ዓለሙ እባላለሁ::" ሳቅ አለችለት::

"እኔም ሳምሶን ደበሌ።" በላብ በተጠመቀ እጁ ስለ ጨበጣት ተበሳጨ።

"በመምጣትሽ እንዴት ደስ ብሎኛል መሰለሽ" አላት በድጋሚ።

ወደሱ ከምትመጣ ወደ ጥልቅ ገደል ገብታ ብትሞት በወደደ ነበር።

"እንደዚያ እንደምትመኝ እገምታለሁ።" ሳቅ ብላ በጎሪጥ ተመለከተችው።

"አልተሳሳትሽም። ለሴቶች ትልቅ ክብር እሰጣለሁ።" ትላልቅ ዓይኖቿን ከላዩ ላይ ተክላ ተመለከተችው። ደስ የሚሉ ዓይኖች ቢኖሯትም አይታዋን አልወደደውም። በውስጡ ያለውን ያልጸዳውን እሱነቱን በጥንቃቄ እየመረመረች የምትመለከት መሰለውና ግራ ተጋባ። ምክንያቱ ባይገባውም ውስጡ እየፈራበት ነው።

"ከመምጣቱ በፊት መደወል ነበረብኝ። ስልክህ ስሞክረው ዝግ ነው ከአለቃዬ ጋር በስልክ እንደ ተነጋገራችሁ አውቃለሁ።" ትኩር ብላ ተመለከተችው።

"ከሰዎች ጋር እየተነጋገርሁ ስለ ነበር ነው የዘጋሁት።" ለመረጋጋት እየሞከረ መለሰላት።

ፀሐይ እንደ መታው አረም መጠውለጉ ገርሞታል። "አገኘቼዋለሁ።" አለች በውስጧ።

"ያለ ምክንያት እንዳልዘጋኸው እገምታለሁ። ቢሆንም ከነመጨረሻው መዝጋት ብዙም አስፈላጊ አይመስለኝም።" ስሜቱን ማጥናት ስለ ጀመረች የበለጠ ተረብሿል።

"የዘጋሁት ያለ ምክንያት አልነበረም። ወሳኝ በሆነ ጉዳይ ላይ እየተነጋገርን ነበር።" ይቅርታ በሚጠይቅ መልኩ አስተዋላት።

ሳቅ ብላ ተመለከተችው። በጣም ተደናግጧል። የሚጠላው የዘሩባቤል ፍቅረኛ መሆኗን ቢያውቅ ኖሮ ይበልጥ እያራጠበው ነበር።

"አስቸጋሪ ጉዳይ ላይ የገባህ ይመስለኛል።" ከአንገቷ ወደ ፊት ተጠጋች።

"ስለ ችግሩ ከመዘርዘሬ በፊት አንተ ራስህ የሆነውን ሁሉ ብትነግረኝ የሚሻል ይመስለኛል። የተደረገውን ሁሉ የጠቅላይ ሚኒስቴር የጸጥታ ሰዎች ደርሰውበታል።"

በአሜሪካን የጸጥታ ቢሮ ድጋፍ የተዋቀረው አዲሱ የደኅንነት ቢሮ የአሠራር ቴክኒኩ እጅግ የተወሳሰበ ሆኖ ነው የተዘረጋው። አንደኛው ሌላውን ማወቅ አይችልም። እራሷን ገለጠችለት እንጂ የመረጃና ጸጥታ ሠራተኛ ልትሆን ትችላለች ብሎ አልገመታትም ነበር። ብዙ ነገር እየዘላበደ ወንጀሉን ሳያበዛ እውነተኛ ማንነቷን ነግራዋለች። ማን መሆኗን መግለጿ ከውሻ አሳንሳ ገምታው መሆኑ ቢገባውም ብዙ አልከፋውም። የፈለገችውን ያህል በፈለገችው መንገድ ግምት ብትሰጠው አልተሳሳተችም። የማይጠቅም ከንቱ ፍጥረት መሆኑን ተረድቶአል።

"የሥነምግባር ግድፈት እያደረግሽ እንደሆነ የተረዳሽው አልመሰለኝም።





የምትይውን በትክክል አውቀሽዋል? ትንሽ የአእምሮ ቀውስ . . . " አቋረጠችው።

"እንዳልከው ጉዳዩ የሰውን አእምሮ የሚጎዳ ነው። የአገሪቱን ደኅንነት ያስጠብቃል ተብሎ ከሚታመን መሥርያ ቤት የዚህን ያህል ክህደት ሲፈጸም ማየት አእምሮን ቢያቃውስ አያስደንቅም።" ፌዝ በተቀላቀለበት ቅላጼ ቀጠለች። "ለመሆኑ ስለሚደረገው ሁሉ የምታውቀው ምን ያህል ነው? አንተን ከማስቸግርህ እራሴ የማውቀውን ያህል ልንገርህ። የተደናገጥህ ስለምትመስል ራሴ ላብራራልህ እና ትቀጥላለህ። በከተማችን አፋኝ ቡድን ተቋቁሞ ሰዎችን ከነሕይወታቸው እያፈነ በወጡበት እያስቀራቸው ሕዝቡ በሽብር ውስጥ ወድቋል። እንዲህ መሆኑን ካልሰማህ በጣም ዕድለኛ ሰው ነህ። የዚህ ቡድን መጠሪያ ስምስ ምን እንደ ሆነ ታውቃለህ? ቤርሙዳ ትሪአንግል። ልክ እንደ ቤርሙዳው ሰዋሪ ኃይል በአዲስ አበባ ሰዎች እየተሰወሩና እየጠፉ አለዚያም እየተጠለፉ እየተወሰዱ ናቸው። ትናንት የት እንደ ነበርክ ልንገርህ።" ሳቅ አለችና በዚያው ቀጠለችለት።

"አካላቸውን ለቅርጫ ከሚያስማሙ እኅቶቻችን ጋር በውስኪ ጦዘህ በነሱ ጭን ስር... የውሻ ተግባር ስትፈጽም ነበር ያመሸኸው። ይህንን ሐሰት ነው ብለህ እንዳትጋተረኝ። አየህ የዕምነትና የባህል ደሴት የተባለች አገር የወሲብ ሽቀጥ መሸቀጫና ማራገፊያ ሆና እንደነ ሰዶምና ጎመራ ምሳሌ የወጣላት አስቀያሚ ሆናለች። አገርን ይጠብቃል ተብሎ ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም የወሲበኛ ደላላ ሆኗል። በዓለም ዙሪያ ያሉ ወሲበኞች ዓይናቸውና ልባቸው ወደዚች የጥንት ገናናዋ የጽዮን ቤተ-መቅደስ ቅድስት አገር ሆነ። ከአፍሪካ አገራት የሚመጡ ከሃዲ ዲፕሎማት ነን ባዮች የአገራቸው ሕዝብ በረሃብ፣ በበሽታና በእርስ በርስ ጦርነት ተቧድኖ እንደ አውሬ እየተላለቀ እነሱ ሴቶችን ፍለጋ በየምሽት ክበቡ ማብቂያ የሌለው ዶላር ሲበትኑ ያድራሉ። ያልታደለች አፍሪካ እነዚህን ፈጠረች። አይደለም አይደለም እናንተን ፈጠረች። አፍሪካን ከቅኝ ገዢዎች ነጻ ለማውጣት የተከፈለውን የደም መስዋዕት በርካሽ ፍላጎታችሁ አረከሳችሁት። ብዙዎች የደም መስዋእት ከፍለው ነጻ ሕዝብና ነጻ መሬት ቢያስረክቧችሁ ሴሰናችሁበት። ብዙዎች ለተሸጠውና ለተለወጠው ወገናቸው ነጻነት ሲታገሉ ወደቁ። እናንተ ደግሞ ለግል ስሜታችሁ እና ፍላጎታችሁ ለነጻነት የፈሰሰ ቅዱስ ደማቸውን አረከሳችሁ። 'እሳት አመድ ወለደ' የተባለውን ተረት ሰምተሃል?" ቁልቁል ተመለከተችው ።

ብታፈጥበትም እጅ መስጠት አልፈለገም። "ግምትሽ በማስረጃ ያልተደገፈ ስለሆነ ይህንን ያህል ደፍረሽ መናገር የለብሽም።"

ደህና አድርጋ በጠለዘችው ቃል መንጋጭላው እስከሚነቃነቅ ድረስ ቢሰማውም መንገዳገድ አልፈለገም።

"ሁሉም ነገር ልክ ስለመሆኑ መሥርያ ቤቱም ያውቃል፡፡ አንተም እራስህ ታውቃለህ፡፡ ከሳጥናኤል በወረስከው የተለመደ ቅጥፈትህ ልታወናብደኝ ብትሞክር እገድልሃለሁ" ሽጉጡን ከቦርሳዋ ላጥ አድርጋ አሣየችው፡፡

"ይህ መሥሪያ ቤት የሚያውቀው ምሥጢር እንዳለ ምን ማረጋገጫ አለሽ? ልብ ወለድ ታሪክሽን፡፡" አሁንም አቋረጠችው፡፡

"ታውቃለህ፡፡ መሥርያ ቤቱም ያውቃል፡፡ በትክክል ድርጊቱ ሲቀነባበር የድርጊቱ ተዋንያኖች ከዚህ መሥርያ ቤት የተለያየ ድጋፍና ሽፋን ይሰጣቸው እንደ ነበር የጠቅላይ ሚኒስትር የጸጥታና የደኅንነት ጽሕፈት ቤት ከመጀመሪያ ጀምሮ ጉዳዩን እየተከታተለው ነው የቆየው፡፡" ትክሻዋን በኃይል ከፍና ዝቅ አደረገችና ተመለከተችው፡፡

እንቅስቃሴዋ ጭምር ከደቂቃ ወደ ደቂቃ መለዋወጥ ሲጀምር እሱም ደም ፍላት ያዘውና ለሽጉጡ አፈ-ሙዝ ግድ ያጣ መሰለ፡፡

"ዝባዝንኬሽ ጭራሽ የማላውቀው እንግዳ ጉዳይ ነው፡፡" በሃይል አንኮራፋና ከተቀመጠበት ተነስቶ ሲቆም በግራ እጇ እየተከላከለች እንዳይንቀሳቀስ አስጠነቀቀችው፡፡

"ሁሉም ነገር አሁን በምትመልስልኝ መልኩ አይደለም፡፡ በትክክል ታውቃለህ፡፡ ድርጊቱ እንዲሳካ ከፍተኛ እገዛ አድርገሃል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር የጸጥታ ሠራተኞች ከዚህ መሥርያ ቤት ጋር በተገናኘ የምሥጢር ድምጽ ማስተላለፊያ እየተጠቀሙ ሁሉንም ነገር እስከ መጨረሻው ድረስ ይከታተሉ ነበር፡፡ ለኔ የምታደርገው ራስን የመከላከል ሙከራህ ያለቀበት ብልጣ ብልጥነት እንደ ሆነ ይግባህ፡፡ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የነበራችሁን እንቅስቃሴ ቢሮው ይከታተል ነበር፡፡"

እንዲቀመጥ በእጇ ምልክት ስትሰጠው የዓይኑ ቅንድቦች ግራ በመጋባት ሽቅብ ተሰበሰቡ፡፡ በዚህ ቢሮ ውስጥ የምሥጢር የድምጽ ማስተላለፊያ አለ ማለት ምን ማለት ነው? ደግሞስ ማን ይሆን የገጠመው? እሷ እራሷ ልትሆን ትችላለች፡፡ ከአንዴም ሁለቴ ቢሮው ገብታ መውጣቷን ረዳቱ ነግሮታል፡፡ ቃል በቃል የተደረገ ውይይት ባይኖራቸውም በሩቁ ያውቋታል፡፡ አንድ ነገር ለመናገር አፉን ከፈተና መልሶ ከንፈሩን ገጠመ፡፡ ከሷ ጋር አተካራ መግጠሙ ፋይዳ የለውም፡፡ ዘመናይ ወፈፌ ናትና የፈለገችውን ከማድረግ የምትመለስ አትመስልም፡፡ ጌታዋን ያመነች በግ... ፈገግ አለ በምፀት፡፡

"ትሰማኛለህ?" ግራ እጇን ወደ ጠረጴዛው ሆድ እየወሰደች ተናገረች፡፡ "ስማ ወንድሜ ሁሉም ነገር አብቅቶለታል፡፡ ይህ መሣሪያ ከአሁን በኋላ ስለማያስፈልግ አንተ ፊት ማንሳት ይኖርብኛል፡፡ የነበረው አገልግሎት አብቅቷል፡፡ ዓይኔን ግንባር ያድርገው በሚል የጅል አሳብ ስትንገታገት ራስህን እንዳትጎዳ ተጠንቀቅ፡፡ ይደረጉ የነበሩትን ጉዳዮች ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ የጸጥታ ሠራተኞች እንድታስተላልፍ





የተገጠመች ናት፡፡" በጣቶቿ ይዛ ከፍ አድርጋ እያሳየችው ስትናገር አፍና ዓይኑን ከፍቶ ተመለከታት፡፡

ጥፊ አቅምሷት ከእጇ ሊቀማት አሰበና መልሶ ተወው፡፡ ምሥጢሩ ከአበቃለት በኋላ ባዶ ቀፎ ተወሰደ አልተወሰደ ምን ይጠቅማል፡፡ በተሸናፊነት አንገቱን አቀርቅሮ ጸጥ ብሎ የምታወርድበትን የዘለፋና የዛቻ ቃል መስማቱን መረጠ፡፡ የተቀባበለ ሽጉጥ በጇ ላይ አለ፡፡ እሱን ለመግደል ምክንያቱ በቂ ነው፡፡

"ልስጥህ እንዴ? የምትፈልገው ከሆነ ልሰጥህ ዝግጁ ነኝ፡፡" በምጸት ሳቀች፡፡ ምርመራዋን እያጠናቀቀች እንደሆነ ገባው፡፡ እራሱን በዝግታ አወዛወዘላት፡፡ ልክ በርግማን ዓይነት፡፡ የማትረቢ ሴት ፍየል አለ በውስጡ፡፡ ሴት ቁብ ፍየል፡፡

ተንቀሳቃሽ ስልኳን አውጥታ የተወሰኑ የኮድ ቃላት ከተነጋገረች በኋላ ስልኩን ዘግታ ወደ ቦርሳዋ በመመለስ እንደልዩ ፍጡር በአግራሞት ተመለከተችው፡፡ የማይጠቅም አሮጌ ፍየል መሰላት፡፡ የማይበላ ማንጆ ፍየል፡፡

ከዓይኑ ብዥ የሚል ምስል እየታየው ሁሉም ነገር ተደበላልቆበት በሰውነቱ ላይ የድካም አለዚያም የመንቀጥቀጥ ስሜት ወረረው፡፡ ራሱን ስቶ ከወንበሩ ከመውደቁ በፊት ሁለት የጸጥታ ሠራተኞች ገብተው እጁን ግራና ቀኝ ደግፈው ሲያነሱት የሕልም ያህል ይታየዋል፡፡ ሁሉም ነገር እንደ ጉም እየተነነ ከፊቱ እየተሰወረ ሲጠፋ እንደ ሕልም ታየው፡፡ ሳምሶን ደበሌ ሁሉን ተመኝቶ ሁሉንም አጥቶ በቅዥት ውስጥ እያለ ኪሩቤል ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ረዳቱም ተከትሎት ነበር፡፡ ከሴቷ ጋር ተያዩ፡፡ በድል አድራጊነት ሳቅ አለችና ኪሩቤልን ተመለከተችው፡፡

"የነገሩ ውል ተገኝቷል ከጉተትነው ግን ያሰጋናል፡፡" አላት፡፡

"ገና ነው፡፡ የተወሳሰበ ስለሆነ ሊበጠስ ይችላል፡፡ ከተበጠሰ እንደገና መፈለግ አለብን፡፡" አለችው፡፡

የመነኩሴ ልብስ ለብሶ በቤተ-መቅደስ እንደሚገኝ በኢንተርኔት የለቀቀው ማን እንደሆነ አውቀሃል?" ትኩር ብላ ተመለከተችው፡፡

"ማነው?" ሲል ጠየቃት ዘሩባቤል፡፡

"ሳምሶንና ረዳቱ ናቸው፡፡"

"ረዳቱ ነበር እኮ መጥቶ የነገረኝ፡፡" አለ ዘሩባቤል፡፡

"እነሱ የሠሩት ድራማ ነበር፡፡" ሳቅ ብላ መለሰችለት፡፡

"ይህንን ማን ነገረሽ?" አለ ዘሩባቤል፡፡

"ረዳቱ ነው፡፡"

"እንዴት? ምን ብሎ ነገረሽ?"

"ተይዞ በምርመራ ላይ ነው፡፡" አለችው፡፡

"ወጥመድሽ ሠርቷል፡፡" አላት እየሳቀ፡፡

# ምእራፍ አሥራ ስምንት

ልቡ ክፉኛ ትንሰፍሰፎ የፍቅር ትዝታ ስሜቱ በእጥፍ አየለበት። አዕምሮው በምትሀትዋ ተስቦ ወደ ኋላው ተመለሰ። ከሌሎች ሴቶች የተለየች መሆኗን ያውቃል። ምትክ የማይገኝላት በዓለም ሁሉ ካሉት ሴቶች ልቃና በልጣ የምትታይ እንደ እንቁ ውድ ሆና ተሰማችው። ትናንት ምሽት እንዴት ነበር ያሳለፍነው? እራሱን እየጠየቀ በውስጠት ፈገግ አለ። ቅብጥብጥ እርቃኗ እጆቿን ግራና ቀኝ ዘርግታና ተመነቃቅራ ትላልቅ አይኖቿን ገርበብ አድርጋ በአንዳች የተለየ ስሜት ስትመለከተው እንደ ሁለት ዓመት ሕፃን ቅጥ አምባር የጠፋው ሞልቃቃነቷ ሁሉም ነገር እንደ ፊልም ከፊቱ እየተከታተለ መጣበት። .

እብደቷ ቅብጥብጥ ባሕሪዋ ልዩ ስልት ያለው ቀበጥነቷ ሁሉም ነገር ደስ ይላል። በገደብ የለሽ የስሜት እርካታ ጠቅላላ ኃይሏ ተንጠፍጥፎ አልቆ ተሸንፋና ተረትታ በሰፊው አልጋ ላይ በጀርባዋ ተንጋልላ ከንፈሯን በሌባ ጣቷ እየነካካች ጣራ ጣራውን አየች። እርቃንዋን ለመሸፈን ምንም ግድ ሳይኖራት የራስጌውን መብራት አበራችው። ትንፋሿ በጣም ርቋል። በስሜት እየቃተተች ወደ ታች አንሸራትታ በእግሯ አሽቀንጥራ የጣለችውን ብርድ ልብስ መልሶ እርቃኗን ሊሸፍናት አልሞከረም። ሆን ብላ ያደረገችው እንደሆን ያውቃል። የእብደት መጀመሪያዋ ነው። ማበድ በሚገባት ሰዓት አብዳለች። ጀማሪ እብድ አይደለችም። መቼና እንዴት ማበድ እንዳለባት ታውቃለች። በጊዜና በቦታው ሲሆን እብደትም ደስ ይላል። እብድ የፈለገውን ለመሆን ነጻነት አለው። እናም የወደደችውን የፈለገችውን ዓይነት እብደት።

ፍጹም ስትረካ ነው እንደዚያ የምትሆነው። እራሷ እስከምትነቃ መጠበቅ አለበት። ሰውነቷ እንደ ገና ወደ ቀድሞው ሙቀቱ ሲመለስ ከማደንዘዣው እንደ ነቃ በሽተኛ ዓይኖቿን ቀስ በቀስ እየገለጠች ዙሪያ ገባውን በእይታዋ ካማተረች በኋላ አንድ ነገር ትጠይቀዋለች። ከዚያ በኋላ ነው ልብስ መልበስ የምትፈልገው። ከጠለቀችበት ሰመመን ባንናና ተወራጭታ እስከምትነቃ መጠበቅ የግድ ነው። በተደጋጋሚ አስጠንቅቃዋለች። የተራቆተ ገላዋን ለማልበስ ሞክሮ ለብዙ ጊዜ በጥፍሮቿና በጥርሶቿ በልታዋለች።

"የቀዘቀዘ ነገር አምጣልኝ?" ፍሪጁን በእጇ አመለከተችው።

ከዋክብት ዓይኖቿን ከኮርኒሱ ላይ ሽቅብ ተክላ አንዳች ነገር በሰውነቷ ላይ እያደመጠች ተንጠራራች። ወገቧን እየወጠረች በኃይል ተንጠራራች። ሙሉ በሙሉ ከሰመመን የመንቃቷ ምልክት ነው።

ፎጣ አገለደመና ወደ ማቀዝቀዣው ደርሶ ተመለሰ። የሚበቃትን ያህል ወስዳ ጠርሙሱን ወለሉ ላይ የመወርወር ያህል አስቀመጠችው።





የቀረ ጭላጭ ስላልነበረው ከምንጣፉ ጠብ ያለ ርጥበት አልነበረም። የቢራ ጠርሙሱን በእጇ አመለከተችው። ገባኝ በሚል ራሱን ሲነቀንቅ አትኩራ እየተመለከተችው ሳቅ አለች። የሕፃን ዓይነት ሳቅ። እየደጋገመች ትስቅ ጀመር። እንደ ቃልቻ እግሮቿን በማቆላለፍ ራቁቷን ተነስታ ተቀምጣ ስትመለከተው ደስ ይለዋል።

ይዞት የመጣውን ግማሽ ብርጭቆ ጅን በእጁ እንደ ጨበጠ ለጤናችን በሚል ዓይነት ብርጭቆውን አመልክቷት ወደ አፉ መለሰና በርከት አድርጎ ተጎነጨለት። ጥሩ ነው በሚል ዓይነት እራሱን ላይና ታች በአድናቆት እየናጠ የአልጋ ልብሱን ሽቅብ መልሶ ሲያለብሳት የበለጠ ተደሰተች። ብርድልብሱ ውስጥ እስከ አንገቷ ተቀብራ ለመተኛት ቁልቁል እየተንሸራተተች ፈገግ ብላ ተመለከተችው። ሁለተኛውን ቢራ ቢከፍተውም አልጠጣችውም።

የተጠማህ ትመስላለህ። እንዳትቃጠል።" እናት ለልጇ የምታሳየውን ዓይነት መኰሳተር ተኰሳተረችበት።

ወደ ብርድ ልብሱ ዘልቃ እየተደበቀች ነበረች። ጦርነቱ ተጠናቅቆ ሰላም ነግሷል። የተሰማትን ለማወቅ ራሷን በስሜት እያደመጠች ናት። ብርጭቆውን አጋብቶ ወደ አልጋው ተመለሰና ብርድ ልብሱ ውስጥ ገብቶ አቀፋት። የምትፈልገው ይህንን ብቻ ነው። ከብብቱ ገብታ እንደ ሕፃን ተደበቀች። አታላይ መልቲ...። ጸጉሯን እያሻሸላት አጉተመተመ። ግን አታላይ እንዳልሆነች ልቡናው ያምናል።

"ለምን እንደ ደከመኝ አውቀሃል?" ትኩር ብላ ተመለከተችው።

"ለምንድን ነው?" ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰው።

"ረጅም ቀናት ስለ ቆየን።" ሳቅ አለች።

ደስ የሚል ረጅም ሳቅ መሳቅ ትወዳለች። እንደዚያ ካልሆነች የሳቀች አትመስልም። የምትስቀው ከውስጧ ነው። ሽንገላ ያልተዋዠረበት የሕፃን ዓይነት ሳቅ። እናም እየደጋገመች ትስቅ ጀመር። ደረቱን አንገቱን ሁለመናውን እየዳበሰችው ከልቧ ተንከተከተች። ምን ዓይነት የሕይወት ሌባ ናት እባካችሁ? ውስጡን ልዩ ደስታ እየተሰማው ያጉተመተመው በቅሬታ አልነበረም።

"ልክ ነሽ።" አላት። ግን እንዳልነበረች ያውቃል። በቀናቶቹ መርዘም የተፈጠረ እንዳልነበር እሷም እሱም ያውቃሉ። ብቻ የትዝብት ወጀብ ለመከላከል ስትል ሁል ጊዜ ይህንን ቃል ትናገራለች። ከሱ የሷ ደስታ ስለሚያረካው ይጠብቃታል። ሁሉ ነገሯ ያስደስተዋል።

"በጣም ናፍቀሽኝ ነበር ማለት ነው?" ከንድና ደረቱን ያለበሰውን ጸጉሯን እያስተካከለ ጠየቃት።

"መናፈቁን እንደ ዳዊት መድገም አለብኝ ማለት ነው?" የተከፋች

መሰለች፡፡ ልክ መጫወቻዋን እንደተቀማች ሕፃን ዓይነት መከፋት፡፡

"እንደዚያ ለማለት አስቤ አይደለም፡፡ ምን ያህል እንደናፈቅሽኝ እንድትነግሪኝ ፈልጌ ነበር፡፡" ከግንባሯ ላይ ሳማት፡፡

"መናፈቄን እንድናዘዝልህ ትጠብቃለህ? ትዕቢተኛ ነህ አጉል አበሻዊ ኩራት" በረጃጅም ጣቶቿ ከርዳዳ ጸጉሩን ማበጠር ጀመረች፡፡ ወደዚያው እጇን በድንገት ሰብስባ "በስመአብ..." አለችና ሰውነቷ እየተኮመታተረ ተንቀጠቀጠች፡፡ የእባብ ምስል እንዳየች ሁሉ ሰውነቷ በሙሉ ሲርድ ተሰማው፡፡ ልቧ እንደ ወፍ እየበረረ ነበር፡፡

"ምነው?" ከትራሱ ቀና ብሎ እየተመለከታት ጠየቃት፡፡

"ከኔ ጋር ተኝተህ ስለ ሌላ ሴት የምታስብ መሰለኝ፡፡" መንቀጥቀጧ እየጨመረ ጥርቅም አድርጋ አቀፈችው፡፡ በሁለት እጆቿ ጭንቅላቷን ጭምድድ አድርጋ እንደ ያዘች አቃሰተች፡፡ አንዳንድ ጊዜ የምታሳየው ትርኢት ያስገርመዋል፡፡ በየደቂቃው የምትፈጥረው የሕይወት እንቅስቃሴ ሁሉ ኪናዊ ውበት ያለው ምትሐት የተዋሐደው ስለሆነ ቀልብያውን ይስበዋል፡፡ ሁሉ ነገሯ የአጋጣሚ ሳይሆን ጊዜና ቦታ አለው፡፡ ሁሉም ነገር በቦታውና በጊዜው ውብና ድንቅ ነው፡፡ እብደትም እንደዚሁ በቦታውና በጊዜው ውብ ነው፡፡ እሷ ደግሞ የሁሉንም ሰዓትና ቦታ ታውቃለች፡፡ ማበድና ማሳበዱን ትችልበታለች ሁሉንም ነገር ተክናበታለች፡፡ ፈጣሪ በራሱ የልብ ቀማኛ ሌባ አድርጐ ሳይሠራት አልቀረም፡፡ "ምትሃታም" አለ በውስጡ፡፡

በእልህ ዓይነት የመንከስ ያህል ምጥጥ አድርጐ ሳማትና ወደ ደረቱ የበለጠ አስጠጋት፡፡

"ለምጠይቅህ ትክክለኛውን መልስ አትሰጠኝም አይደል? የፈረደብህ ገል ራስ፡፡" ተነጫነጨች፡፡

በጥፍሯ አንገቱ ስር ስትይዘው ቆዳውን ሸርክታ ጠብታ ደም እንዳታወጣ አምባር ማዋያዋን ጥርቅም አድርጎ ያዘው፡፡ ፊቷን ሲመለከት ደሟ የተለዋወጠ መሰለው፡፡ ጥርሷን ነክሳ ተመለከተችው፡፡

"ስለ ማን ሴት ነው እያወራሽ ያለሽው?" ፊቱን ሳትሰነታትረው በፊት ለመከላከል እጇን ጠበቅ አደረገና ያዛት፡፡

"ስለ ሚስትህ ነው የማወራው፡፡ ከነፍስህ አብልጠህ ትወዳት ነበር?" ከክንዱ ላይ ብድግ ብላ አዘቅዝቃ ተመለከተችው፡፡

"በአሁን ሰዓት ለምን መጠየቅ አስፈለገሽ?" በቅሬታ ፊቷን ሸቅብ እየተመለከተ መለሰላት፡፡

"ትወዳት ነበር ወይ? የምፈልገው ለጠየቅሁህ ትክክለኛውን መልስ እንድትመልስልኝ ብቻ ነው፡፡"

ስስ ጥፍሯ ወደ ሥጋው ዘልቆ ፊቱን እንዳያበላሸው የበለጠ ሰጋ፡፡ ምን ልትል እንደ ፈለገች በውል አልገባህ ብሎት ተቸገረ፡፡





"እወዳትና አፈቅራት እንደ ነበር ቀደም ሲል ነግሬሽ ነበር፡፡" ውስጡ በድንገት ሲታመስበት በረጅሙ እየተነፈሰ ከትራሱ ላይ ቀና ለማለት ሞከረ፡፡ ግን በግራ እጁ ተጭና ያዘችው፡፡

"ትዝታህን ቀስቅሼ ስሜትህን በመጉዳቴ አዝናለሁ፡፡ ለምን እንደምጠይቅህ ታውቃለህ?" አትኩራ ተመለከተችው፡፡

ውስጡ በመጥፎ ስሜት እየተበጠበጠበት ትኩር ብሎ እየተመለከታት "ለምንድነው?" ሲል ጠየቃት፡፡

"ከኔ ጋር ፍቅር በምንሠራበት ወቅት እሷን የምታስብና ስሜትህ የሚጎዳ ስለሚመስለኝ ነው፡፡ ምን እንደሚሰማኝ ታውቃለህ?" ጥፍሯን ካንገቱ ላይ አላቅቃ በኃዘኔታ አኳኋን ተመለከተችው፡፡ ኃዘን አለዚያም ብስጭት በውል ያልገባው ሁኔታ ውስጡን ሲያውክበት እየተሰማው በረጅሙ ተነፈሰ፡፡

"ብዙ ጊዜ በዚህ መልኩ መንፈሴ ስለሚነካ ባለቤትህን በእዝነ ልቦናዬ አስባታለሁ፡፡ ለዚህም ይመስለኛል እስከ መጨረሻ የእርካታ ዳርቻ ድረስ የወሲብ ስሜቴን የምሰጥህ፡፡ በየትኛውም መንገድ እሷን እንድትረሳ እጥራለሁ፡፡ አንተን ለማስደሰት ስል በምፈጥራቸው ሁኔታዎች ወደ ጠለቀ የወሲብ እርካታ እገባለሁ፡፡ ሕይወት በስሜት ርካታ ምን ያህል ደስታን እንደምትሰጥና የወሲብን ልዩ ጥበብ እንዳጣጥመው በር ከፍተህልኛል፡፡ እንዴት ደስ የሚል ሕይወት አስጀመርከኝ መሰለህ፡፡" እንዳልታሰበ የመስከረም ዝናብ እምባዋ እየተንጠባጠበ ከደረቱ ላይ ሲወድቅ እቅፍ አድርጐ ከደረቱ ላይ አስተኛት፡፡ በርግጥ የምትለው ሁሉ ለሷ ትርጉም ሊኖር ይችል ይሆናል፡፡ ከሙት ጋር የሚደረግ የመቀናናት ስሜት ከጤነኛ መንፈስ ሊመነጭ አይችልም፡፡ ቀና ብላ  ተመለከተችው፡፡ ሩቅ የሚያስብ ይመስል ዓይኑን ኮርኒሱ ላይ ተክሎ ሽቅብ አንጋጥጦ ዝም አላት፡፡ ከዓይኗ ግድብ ላይ ተንጠልጥለው የነበሩት የእምባ ዘለላዎች የበጋ በረዶ መስለው ሲንጠባጠቡ በአፉ ውስጥ በመውደቃቸው እንደ ጨው የአፉን መዓዛ ቀየረው፡፡ ሆን ብላ ወዳፉ እንዳፈሰሰችው ገባው፡፡

"የተሰበረ መንፈሴን ጠግነሽልኛል፡፡ ለሕይወቴ አዲስ ምእራፍ ..." በአፉ ውስጥ የወደቁት የእምባ ዘለላዎች ጣእም የመንፈስ እርካታ እንደ ሰጠው ሁሉ በእፎይታ ተነፈሰና ራሱን አወዛወዘላት፡፡

"ሁል ጊዜ ምን አሳብ እንደሚመጣብኝ ታውቃለህ? እንዴት ያለች ቆንጆ ትሆን? የነበራትስ የፍቅር ጨዋታ? እነዚህ ከንቱ የፈጠራ አሳቦች የህሊና ሸብር እየፈጠሩብኝ ያደክሙኛል፡፡ በራሴ የፈጠራ ድርሰት ጭንቀት እየፈጠርሁ ቀንና ሌሊት ስቀምር ያለረፍት ብዙ በጣም ብዙ ሰዓት እደክማለሁ፡፡ አብራችሁ በነበራችሁበት ጊዜ ሁለታችሁም እኩል ደስታ ነበራችሁ?"

የእጁን ጣቶች በእጆቿ እያፍተለተለች ቆይታ ወዳፏ አቅርባ ጉረሰቻቸው።

“ይመስለኛል። አብረን በቆየንባቸው የተወሰኑ ዓመታት ሁለታችንም ደስተኛ እንደነበርን አስባለሁ።” አላት ሳግ እየተናነቀው።

“ባለቤትህን ገጠር ይዘሃት በመሄድህ የጸጸት ስሜት ይሰማሃል ማለት ነው?”

“ይሰማኛል።” አላትና አንገቱን ወደ ትራሱ መልሶ ያስብ ጀመር።

“እንዳልከው ወደ ሥራ ቦታህ ሄደህ የሥራ ጊዜህን ጨርሰህ ብትመለስ ኖሮ ይህ ሁኔታ ላይፈጠር ይችል ነበር። ለሁሉም በአሁን ሰዓት ሁሉም ነገር አልፏልና ይህ ባይሆን ያ ቢሆን ማለቱ ፋይዳ የለውም።” አለችው።

“ስለ ባለቤቴ አሟሟት እውነተኛውን ታሪክ ታውቂ ነበር ማለት ነው?” ሲል ጠየቃት።

“አውቃለሁ። ያንን ታሪክ ስለማውቅም ነው ለየት ያልኩ ሴት ሆኜ ለመቅረብ ጥረት ያደረግሁት። በየትኛውም መንገድ እሷን እያሰብህ እንድትጎዳ አልፈልግም ነበር።”

“ታዝኚልኝ ነበር እንጂ አታፈቅሪኝም ነበር ማለት ነው?” በተለያየ ስሜት ውስጥ ሆኖ ጠየቃት።

“እወድህ ነበር እንጂ ወደ ፍቅር አልገባሁም ነበር። እንዳልከውም የደረሰብህን ሁሉ ሳስብ ከመጠን በላይ ኃዘን ይሰማኛል። አንተ ግልጽና ሰውን የማትጎዳ የዋህ ፍጡር ነህ። ጥሩ ተፈጥሮ ነው ያለህ። ሰው ያለህንና የነገረህን ሁሉ ታምናለህ። ብዙ መከራን እንዳሳለፈ ሰው በልብህ የቂም ቋጠሮ እንደሌለበት ሁልጊዜ ይሰማኛል። ነህም ደግሞ። እናም መውደዴና ማዘኔ ወደ እናታዊ ፍቅር የተለወጠ ይመስለኛል። እያፈቀርኩህ እሳሳልህ ጀመርሁ። የፍቅር ሚዛን ከመሳሳት ጋር እንዴት ደስ የሚል የተፈጥሮ ጸጋ ነው? እናም ፍቅር ከመሳሳት ጋር እንደ ምን የልብ ደስታ ይሰጣል መሰለህ። ይህ ሁሉ ተደምሮ ወሰን ወደማይገኝለት ውስጣዊ ስሜትና እውነተኛ ፍቅር ተለወጠ። እራሴ በማደርገው ድርጊት ወሰንና ገደብ ወደሌለው ጥልቅ የፍቅር ውቅያኖስ ገብቼ ለመውጣት የማይሞከር ሆኖብኝ ብቅ ጥልቅ ስል የበለጠ እደሰታለሁ።” እጆቿን ግራ ቀኝ አመናቅራ ከራስጌዋ ያለውን ነገር ለመያዝ እየፈለገች በስስት ዓይነት ተመለከተችው።

“በማፍቀርሽ ትጸጸችበታለሽ ማለት ነው?” ትክ ብሎ እየተመለከተ ጠየቃት። አንገቷን ቀና አድርጋ እየነቀነቀች። “እንደዚያ ማለቴ አይደለም። በማፍቀሬ እጅግ ደስተኛ ነኝ። ግን...” የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር እያቆራረጠች ወደ ውስጥ ውጣ አስቀረችው።

“ግን ምን?” ከግንባሯ ላይ እየሳማት ጠየቃት።

“ምን መሰለህ ማፍቀር መጥፎም ጥሩም ነገር ነው። ከመጠን ባለፈ ሊገመት በማይታመን መልኩ የወደድከውን ሰው እየወደድከው





ምናልባትም አጣዋለሁ በሚል ስጋት መጠራጠር ትጀምራለህ። እኔም ታዲያ አንድ ቀን አጣህ ይሆናል የሚል መጥፎ ስጋት ስለሚረብሸኝ መንፈሴ ይታወክና...” ንግግሯን አቋርጣ ታስብ ጀመር።

ከጥልቅ ጭንቀት ውስጥ እንደሆነች ተረዳላት እንጂ ቅሬታ አልተሰማውም ነበር። እናም ሊያጽናናትና ሊያረጋጋት በፍጹም እንደማይለያት ሊያረጋግጥላት ፈለገ።

“የምታስቢው ሁሉ ይገባኛል። አሁን ያለንበትን ጊዜ እንደ ትልቅ ዕድል አድርገሽ አስቢ። የነገን መኖራችንን የሚያውቅ የነገው ባለቤት ብቻ ነው። ያልተጨበጠ ስሜት ውስጥ ራስሽን እየጨመርሽ መንፈስሽን መጉዳት የለብሽም።” ጣቶቿን ጭምቅ አድርጐ ያዛቸው።

“ስሜትክን በስሜቴ ፍቅርህን በፍቅሬ ካላሰርኩት አንድ ቀን ትለየኛለህ እያልኩ መስጋቴ አልቀረም። ዝም ስለምትልም በውስጥህ የበቀል ቁርሾ የቋጠርህ ስለሚመስለኝ ክፉኛ እሰጋለሁ። የዝምታህ መሠረቱና መነሻ ምክንያቱ ለኔ ግልጽ አይደለም። ከእንደዚህ ዓይነቱ መጥፎ የቁም ቅዠት ምን እንደሚገላግለኝ አላውቅም። ድብቅና ቂመኛ ለብቀላም የተዘጋጀህ ትመስለኛለህ እጨነቃለሁ። ባለቤትህን የገደሏት ሰዎች ያሉበትን ታውቀዋለህ እንዴ?” ስትል ጠየቀችው።

ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይቶ በረጅሙ ተነፈሰ። ይህንን ሁሉ ምሥጢር በምን መንገድ ልትደርስበት እንደ ቻለች ለመገመት ተስኖት ውስጡ በተለያዩ ጥርጣሬዎች ተሞሉበት። ለምትጠይቀው ሁሉ መልስ ስለምትፈልግ ከወጠረችው ስለማትለቅቀው ተንፍሶ መገላገል አለበት።

ተወልዶ ያደገው ናዝሬት ከተማ ነው። ትምህርት ሲጨርስ በአስተማሪነት ተቀጥሮ በኦሮሚያ ክልል በአርባ ጉጉ ወረዳ ሥራ ጀመረ። በዚያው እያለ የመንግሥት ለውጥ መጣና በአማራዎች ላይ ጥቃት ተከፈተ።

በዚያው ወቅት ቅያሬ ጠይቆ ወደናዝሬት ተመለሰ። በሴት ላይ ችግር አይፈጠርም በሚል አሳብ ባለቤቱን ትቷት ነበር እሱ ወደናዝሬት የመጣው። እናም ሚስቱ ተገደለችበት።

“ጥያቄዎቿ እየከበዱበት ቢመጡም መመለስ እንዳለበት ተገንዝቧል። የሚገምታትን ዓይነት ሴት አይደለችም። እሱን ከራሱ ባለፈ እንደምታውቀው አልተጠራጠረም።

“ባውቅ ኖሮ እኔና አንቺ ባልተገናኘንም ነበር?” ድምጹ ቅርጹን ለውጦ እየተቆራረጠ ወጣ። በፍጹም ያንን ታሪክ ማሰብ አልፈለግም ነበር። እናም ውስጡን እንደ ጦር ሲሰነጥቀው ተሰማው።

“ለበቀል ነበር ማለት ነው ፖሊስ የሆንከው?” ጥያቄዋ ወሳኝ ስለ ነበር በመገረም ተመለከታት።

“እንደዚያ ነበር ያሰብኩት።”

“እና ተሳካልህ?” በሚሰረስር እይታ አትኩራ ተመለከተችው።

“ገና በፍለጋ ላይ ነኝ።” እጁን ዘርግቶ እንደ ገና በእቅፉ አስገባት።

“እስክ ዛሬ . . .” የበለጠ ፈራች።

እንደገመተችው በውስጡ በቀል ሳይኖር አልቀረም። ፍለጋውን ካልጨረሰ ከእጇ ማፈትለኩ የማይቀር መስሎ ተሰማት።

“ሁኔታው የተወሳሰበ ነው።”

“በርግጥ ብዙ ልትደክምበት እንደምትችል እገምታለሁ።”

“የፖሊስ ሥራህን ለቅቀህ ወደ አስተማሪነት ሥራህ የመመለስ ፍላጐት አለህ እንዴ?”

“እርግጠኛ ሆኜ አልነግርሽም። ያም ሆኖ የማስተማር ሙያን እወደዋለሁ። የአስተማሪነት ሕይወት ጥሩ ነው። ሁል ጊዜ ተማሪ ነሽ ሁል ጊዜ አስተማሪ ነሽ።”

“ለምን አትመለስም ታድያ?”

“እንደ ነገርኩሽ ብዙ የቤት ሥራዎች አሉብኝ።”

“ምን የነገርከኝ ነገር አለ?”

ምንም የነገራት ነገር አልነበረም። እናም አፈረና ሳቅ ፈነቀለው።

“ምንም የነገርከኝ ነገር የለም እኮ።”

“ልክ ነሽ ምንም አልነገርኩሽም።” አሳት ከልብ እያዘነላት እያባባችው ነበረች።

“እባክህ ሁሉንም ነገር ተወውና በሰላም አብረን እንኑር።”

“እየኖርን ነን እኮ።”

“ከዚህ በተሻለ ተረጋግተህ ማየት እፈልጋለሁ።”

ራሱን በዝግታ አወዛወዘላት።

“አይዞሽ እረጋጋለሁ አላት።”

ግን እርግጠኛ እንዳልሆነ ያውቃል። ያንን ሳይወጣው ከማይለቅቀው ወጥመድ ሰተት ብሎ ገብቷል።





# ምእራፍ አሥራ ዘጠኝ

ከመምሪያው ጽሕፈት ቤት ሕንፃ አጠገብ መኪናውን አቁሞ ወረደ። ወደ ውስጥ ሲገባ የመምሪያው ኃላፊ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በዕለቱ ሪፖርቶች ላይ እየተወያየ ነበር። ከየአቅጣጫው እየጎረፈ ያለው ሪፖርት አእምሮውን ወጥሮ ይዞት የሚጨብጠውን አሳጥቶታል። አዲሱ ሰው በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ ሲገባ የመምሪያው ኃላፊ ቀና ብሎ አይቶት ሁለቱን የሥራ ባልደረቦቹን እራሱን እየነቀነቀ በይቅርታ መልክ አስተዋላቸው።

“የእኛን ጉዳይ ለሌላ ጊዜ እናደርገዋለን። እንግዳ መጥቶብኛል” ከተቀመጠበት እንደመነሳት እየከጀለው በስንብት መልክ ሲናገር ማስታወሻዎቻቸውን አጣጥፈው በዝግታ እርምጃ ወደ በሩ አቅጣጫ የተንቀሳቀሱት በተመሳሳይ ስሜት ነበር።

“ሥራ ላይ ነበራችሁ?”

ተመቻችቶ እየተቀመጠ ወደ ውጭ እየወጡ ያሉትን ሁለቱን ሰዎች ከጀርባቸው ተመለከታቸው።

“ጨርሰናል። በዕለት ሪፖርት ላይ እየተነጋገርን ነበር። ከእናንተ ቢሮ የመጣውን የፋክስ መልእክትም አይተነዋል።” የተረጋጋ ለመምሰል ተጣጣረ የመምሪያው ኃላፊ።

ለተወሰኑ ደቂቃዎች ያህል በሁለቱ መካከል ጸጥታ ሰፍኖ ያለ ምንም ንግግር ቆዩ። በአለፉት ሽርፍራፊ ደቂቃዎች ሰፊው ክፍል ከወረቀት ኳኳታ በስተቀር ጸጥታ የሰፈነበት ሕይወት አልባ መስሎ ለመቀጠል ተገደደ።

ወረቀቶቹን አስተካክሎ መጨረሱን በዓይኑ ፈትሾ ከአረጋገጠ በኋላ ቀና ብሎ ተመለከተው።

“ሥራ እንዴት ይዞኻል?” ሲል ጠየቀው ዘሩባቤል።

“በየደቂቃው አዳዲስና አስገራሚ የሆኑ ሪፖርቶች ይደርሱኛል። አሁንም እየተነጋገርን የነበረው በአንድ አስገራሚ ሪፖርት ላይ ነበር። ጣቶቹን አቆላልፎ እያፍተለተለ ተመልክቶት ቀጠለ። በሪፖርቱ እንደ ተመለከትኩት አንድ እንግዳ ሰው ወደ እኛ በመቅረብ ላይ ነው።” በረጅሙ ተነፈሰ።

“ምን ዓይነት ሰው ነው?” ዘሩባቤል ጆሮና ልቡን አነቃ።

“ከሀያ ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝን ወርቅ ከሀገር ለማውጣት በመጣደፍ ላይ ይገኛል።”

“ከሀያ ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝን ወርቅ አልከኝ?” የሰማውን የተጠራጠረ በሚመስል አስተያየት ተመለከተው። በርግጥም ሊታመን የማይችል ነገር ግን እውነት ነበር።

“ስለሱ እየተነጋገርን ነበር የመጣኸው።”

የመምሪያው ኃላፊ ስለ ጉዳዩ መረጃው እንደ ደረሰው ሊያስረግጥለት ሞከረ።

“እንዴትና በየት በኩል ነው ለማውጣት እየሞከረ ያለው?” ሲል ጠየቀው።

“በአንድ ገበሬ አማካኝነት ነው አዲስ አበባ የገባው። ሪፖርቱ ላይ እንደ ተገለጠልኝ ከሆነ ወርቁን ይዞት የመጣው ባላገር በተረከቡት ሰዎች ተገድሏል። ሰውየው የተገደለው ከሳምንት በፊት ሲሆን ገዳዮቹ ወርቁን እንገዛኻለን ብለው ገዢና ደላላ በመሆን ንብረቱን እንደ ተረከቡ ሂሳብ ከመክፈል ይልቅ ገድለው ወደ አንድ ሚሊዮን ዶላር በሚጠጋ ዋጋ ለዚህ አሁን ለነገርኩህ ሰው ሸጠውታል። ወርቁን የገዛው ሰው የሳውዲ ዜግነት ያለው አረብ ነው።”

የመምሪያው ኃላፊ ተናግሮ ሲጨርስ ከወንበሩ ላይ እየተመቻቸ በረጅሙ ተነፈሰ።

“የሰውየውን ማንነት በትክክል ደርሰህበታል ማለት ነው?” ትክ ብሎ ተመለከተውና ሁለት እጆቹን ከጠረጴዛው ላይ አሳረፈ ዘሩባቤል።

“ደርሰንበታል የሚል ግምት አለን። በአየር መንገድ በኩልም ክትትል እንዲያደርጉ ለአገር ውስጥ ጉዳይ መሥርያ ቤት ሪፖርት ልኬአለሁ።”

“ሰውየውን ስለ ገደሉት ሰዎችስ ምን መረጃ አለህ?።”

“ለጊዜው ገና በክትትል ላይ ነን። ያም ሆኖ በቁጥጥር ስር እናውላቸዋለን የሚል ተስፋ አለኝ። የምርመራ ሠራተኛዬ አንደኛውን ወንጀለኛ በቅርብ እርቀት እየተከታተለው እንደ ሆነና በቅርብ ቀን ከነግብረ አበሮቹ እንደሚይዘው በሪፖርቱ ጠቅሶልኛል።”

“ሰውየው መደበኛ ሥራው ምንድን ነው?” ዘሩባቤል ሳይታወቀው በኃይል አንኮራፋ።

“የወንዶች ጸጉር አስተካካይ ነው።”

“የመኖሪያ አድራሻውን በትክክል ደርሳችሁበታል እንዴ?” አትኩሮ እየተመለከተው በርካታ አየር ተንፍሶ አወጣ።

“የመኖርያ ሰፈሩ የተለያየ ነው። ጸጉር የሚያስተካክልበትን ቦታ ግን በትክክል አውቀናል።”

“አድራሻውን ከደረሳችሁበት ለምን በቁጥጥር ስር አላዋላችሁትም?።”

“እንደዚያ ማድረግ በጣም ቀላል ነው። ነገር ግን ሌሎች ምሥጢሮችን ለማግኘት ከምናደርገው ጥረት አኳያ ቀድመን በቁጥጥር ስር ማድረግ የምናደርገውን የጉዞ መስመር እንደ መበጠስ ይቆጠራል የሚል ግምት ስለተሰማን በቁጥጥር ስር ማድረጉን አዘግይተነዋል።”

“የአንተ የምርመራ ሠራተኛ ወሬውን ያገኘው ከየት ነው?።”

“አብሯቸው ከሕገ ወጦቹ ጋር የነበረ ሰው ቢሮው ድረስ መጥቶ ነው ጥቆማውን የሰጠው።”





“ሊታመን የማይችል ጥሩ ቀልድ ይመስላል።”

ጥርጣሬውን በሚያጎላ ሁኔታ ተመለከተውና ነገሩን ሊያጣጥልበት ሞከረ።

“የለም ጥርጣሬን የሚያስወግድ እውነት ነው። ምንም ውሸት አልተቀላቀለበትም” አለ የመምሪያው ኃላፊ።

“እንዴት ሊሆን ይችላል?”

በሳቅ እየተንተከተከ ተመለከተው።

“በክፍያ ሳይጣሉ አይቀሩም። እሱ እንደሚለው ከሆነ ሊገድሉኝ ሲሉ አመለጥኳቸው” የሚል ምክንያት ነው የሰጠው።

“መርማሪው ለምን ከሰውየው አላገናኘህም ነበር ታዲያ?” አለ ዘሩባቤል።

“እስከሚረጋጋ ድረስ ከበስተጀርባው ሆኖ ለመከታተል ስለ ፈለገ ከኔ ማገናኘቱን እንዳዘገየው ገልጾልኛል” የመምሪያው ኃላፊ ሁሉም ነገር ቢገባውም ስሜቱን መቆጣጠር እንዳለበት ተገነዘበ።

“በጣም ፈርቷል ማለት ነው?”

“እንደ ነገረኝ ከሆነ ለሕይወቱ ክፉኛ ተጨንቋል። ሊገድሉት እየተከታተሉት መሆናቸውን ለረዳቴ ነግሮታል።”

“ስለ ነገረህ ብቻ አምነህ ተቀበልከው?” አለው ዘሩባቤል።

“ስለ ነገረኝ አይደለም” ቃሉን ተቀብሎታል።

“ለሕይወቱ ከለላ ከመስጠት በተጨማሪ ምን ቃል ገብታችሁለታል?”

“ለጊዜው እያሰብን ያለነው ለሰውየው ልዩ ጥበቃ በማድረግ ወንጀለኞቹን ለመከታተል ስለሆነ ከኔ ረዳት ጋርም የተነጋገርነው በዚሁ ዙሪያ ነው። አንተ በምትለው መልኩ ጥቅምን በተመለከተ የገባንለት ቃል የለም።”

“ለሰውየው ልዩ ጥበቃ ለመመደብ ተዘጋጅታችኋል?”

“በኛ እጅ ከገባበት ሰዓት ጀምሮ ሲቪል የፖሊስ ደኅንነቶች እየተከታተሉት ናቸው። በየሰዓቱ ከነሱ ሪፖርት እየጠበቅን ነን። በዚህ ዙሪያ ቀደም ሲልም የተወሰኑ ሪፖርቶች ደርሰውኛል።”

“ልዩ ደኅንነቶቹ ስለ ሰጡህ መረጃ ልትገልጽልኝ ትችላለህ? የተወሰኑትን ባውቅ?” ጥያቄውን ቀላል ለማድረግ ንግግሩን አንዛዛው።

“ከመምጣትህ ቀደም ብሎ አንድ ሪፖርት ለረዳቴ እንደ ደረሰው ነግሮኛል። ምናልባትም ዝርዝሩ ይደርሰኛል የሚል ግምት አለኝ። እንደዚያ ከሆነ ሁሉንም ሪፖርት እንድታየው እፈቅድልሃለሁ።”

“ልዩ ደኅንነቶቹ በላኩት ሪፖርት ላይ ምን ብለውት ይሆን?። ስለሱ ረዳትህ አልገለጸልህም?”

“ግለሰቡን ሰዎች እየተከታተሉት እንደ ሆነ በሪፖርታቸው እንዳስታወቁት ብቻ ነው የገለጸልኝ። እስከ አሁን ያለውን ሪፖርት ልታየው ትችላለህ” መሳቢያውን እየከፈተ ቶናገረ።

"በሪፖርቱ የተገለጸው ሌላውስ ምንድነው?። ሪፖርቱን እስክመለከተው በቃልህ ብታስረዳኝ።"

"ከሕዝብ መዝናኛ ክበቡ ሲገባ ሁለት ሰዎች ተከታትለውት እንዳነጋገሩት ጠቅሰውልኛል። ከገንዘቡ ድርሻውን እንዲወስድ እንደዚያ የማያደርግ ከሆነ እንደሚገድሉት አስጠንቅቀውታል።"

"ምን መልስ ሰጣቸው ታዲያ?"

"ከጥቅሙ የሚያካፍሉት ከሆነ አብሮአቸው እንደሚቀጥል እንደ ነገራቸው ነው የገለጹት።"

"በቅርብ የደረሰህ ሪፖርትስ በምን ዙሪያ ላይ ያተኮረ ነበር?"

"ከዕቃው ሽያጭ ያገኘነው ትርፍ ነው ብለው የሱን ድርሻ ሀያ ሺህ ብር ሰጥተውታል የሚል ነው።"

"ብሩን ከተረከበ በኋላ ወዴት እንደ ሄደስ ተገልጾልሃል? ከሆነስ ወደ ባንክ ሄደ ወይስ ወደ ቤቱ?" ፊቱን መልሶ ተመለከተው።

"የብር Cከክቡን እንደ ፈጸሙ ወደ ንግድ ባንክ ሄዶ ገቢ አድርጓል።"

"የመጨረሻውስ ሪፖርት ምንን በተመለከተ ነው?"

"የደስ ደስ እራት እንዲጋብዛቸው ጠይቀውታል።"

"ከሰዎቹ ጋር ያለውን የራት ግብዣ ተቀብሏቸው ከሆነ ከአደጋ ላይ አይወድቅም የሚል ግምት ይኖርሃል?" ፊቱን እያጠና ጠየቀው።

"የራት ግብዣውን ጥያቄ ተቀብሎ ከተገኘላቸው ሊገድሉት ይችላሉ የሚል ስጋት አድሮብኛል።"

"ራት ለመጋበዝ ሲስማማ እንደሚገድሉት አይጠረጥርም ማለት ይከብዳል። ሆኖም በፈለጋቸው መንገድ ሊያስገድዱትም ይችላሉ።"

"ለጊዜው ይህንን ለማወቅ እርግጠኛ ለመሆን ይከብዳል።"

"ምን ለማድረግ ወስነሃል?" በተደበላለቀ ስሜት አስተዋለው ዘሩባቤል።

"ማድረግ ስለሚገባኝ ነገር የወሰንኩት ነገር የለም።"

"ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ይመስላል። የሰውየውን ሕይወት ለመታደግ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባችኋል።"

"እየተነጋገርን የነበረው አንተ ያልከውን ነበር። በጉዳዩ እያሰብንበት ነው።"

እንደ ሽማኔ ድር የተጠላለፈው ነገር አሳሰበውና ዓይኖቹን ፊት ለፊት ከነበረው ግድግዳ ላይ ተክሎ ያስብ ጀመር። የመምሪያው ኃላፊም እንደዚሁ እጆቹን ከጠረጴዛው ላይ አቆላልፎ በማንተራስ በመስኮት አሻግሮ ውጭውን እየተመለከተ በሃሳብ መማሰን በመጀመሩ ቢሮው በጸጥታ ተዋጠ።

ከብዙ የጸጥታ ጽልመት በኋላ የመምሪያው ኃላፊ ከእንቅልፍ የመባነን ያህል ነቃና መናገር ጀመረ።

"ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የጠረጠርነውን የራሳችንን ሰው በቁጥጥር ስር እንዲቆይ አድርገናል።"





"አልገባኝም" አለ ዘሩባቤል።

"በአስቸኳይ እንድትመጣ የፈለግሁት በዚህ ዙሪያ እንድንነጋገር ነው። ሌሎች ጉዳዮች ስለተነሱ ይህንን አዘገየነው እንጂ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው" የመምሪያው ኃላፊ ስሜቱን ለማወቅ ትክ ብሎ ተመለከተው።

"የእናንተም ሰው እጁ አለበት እያልከኝ ነው?" ትክሻውን ከፍና ዝቅ አደረገና ጠየቀው።

"በጉዳዩ እንዳለበት ሊገልጹ የሚችሉ ብዙ ፍንጮች አሉ። ግለሰቡ በመጀመሪያ ለጥቆማ የገባው ወደሱ ቢሮ ነበር" የመምሪያ ኃላፊ ንግግሩን አቋርጦ ተመለከተው።

"እና ታድያ?" ልብና ጆሮውን ከፍቶ መልሱን ተጠባበቀ የመረጃ መኮንኑ።

"ጥቆማውን በሚሰጠው ወቅት ኃላፊነት እንደ ተጣለበት የመንግሥት አካል ተቀብሎ በትክክለኛ መንገድ ከማድመጥና መልስ ከመስጠት ይልቅ በተለያዩ ጥያቄዎች እያጣደፈ አንተ የምትለውን ሰው ስለ ማውቀው እንደዚህ ዓይነት ድርጊት ይፈጽማል ብትለኝ ላምንህና ልቀበልህ አልችልም። በንጹሕ ሰዎች ላይ ተራ የስም ማጥፋት ተግባር ከማድረግ ተቆጠብ" በማለት አስጠንቅቆ ሁለተኛ የማንንም ስም እንደማያነሳ ገልጾለት ይቅርታ በመጠየቅ ከቢሮው አፉን ይዞ ይወጣል። እነዚህ ቃላት የሚጠቁመት በጉዳዩ ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን ያለበት መሆኑን ነው።"

"ግንኙነት አለው የሚል ድምዳሜ ላይ ያደረሰህ ይህ ነው?"

"ግለሰቡ ለሕይወቱ እንደ ፈራና ሰዎች እየተከታተሉት እንደ ሆነ የሰዎቹንም ማንነት በስም ማስረጃ እያስደገፈ ሲሰጠው እጁ ባይኖርበት ኖሮ እያስፈራራ በማዋከብ አያስወጣውም ነበር ከሚል ድምዳሜ ላይ አድርሶኛል።"

"መርማሪው አሁንም በሥራ ላይ ነው ያለው?"

"ለጊዜው እየሠራ ነው ምን መወሰን እንዳለብኝ ከብዶኛል።"

"ጠበቅ ያለ ክትትል የሚያስፈልገው ይመስለኛል" አለ ዘሩባቤል።

"መርማሪውን ማለትህ ነው?" ኃላፊው በመደናገር ዓይነት ጠየቀው።

"አዎን" አለው።

"በቁጥጥር ስር ተደርጎ በማይታወቅ ስፍራ መሰወር አለበት። ያለበትን ሁኔታ ቤተሰብም ማወቅ የለበትም። ለሥራ ጉዳይ ከከተማ መወጣቱን በቢሮው በኩል እንዲወራ ማድረግ አለባችሁ። በጄ ላይ ምንም ዓይነት የመገናኛ ዘዴ የሆኑትን ስልክን ጨምሮ ማንኛውንም ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች መጠቀም የለበትም።"

የመምሪያው ኃላፊ አንገቱን በአሉታ አወዛወዘና ተመለከተው።

"እንደዚያ ለማድረግ አስቤ ነበር። ስልኩን መዝጋቱ ጠቃሚ ስላልሆነ ክፍት ሆኖ እንዲቀጥል አድርጌአለሁ።"

የጸጥታ ሠራተኛው ራሱን በአዎንታ እነቃነቀ "ትክክል ነው ያደረግኸው። ይህ አሳብ እስከ አሁን ድረስ አልመጣልኝም ነበር።"

"ያልከውን ቀደም ሲል አስቤበት ነበር። ልነግርህ የምፈልገው ቢኖር በሁሉም ስፍራ የአንተ እርዳታ የሚያስፈልገኝ መሆኑን ነው። እየተመካከርን ግዳጃችንን መወጣት አለብን" ተናግሮ ሲጨርስ በጥያቄ ተመለከተው።

"አብሬህ ለመሥራት ዝግጁ ነኝ። ወደ ቢሮ ተመልሼ ስለ ጉዳዩ ማጥናት አለብኝ። የእኛ ቢሮ በጉዳዩ ላይ መወያየትና የራሱን ውሳኔ መስጠት አለበት። እስከዚያ ድረስ የመረጃ ሰዎችህ ሙሉ መረጃ እንደሚያደርሱህ እገምታለሁ። ተባብረን ከሠራን ሁሉም ነገር በትንሽ ቀናት ውስጥ ያከትምለታል። በሌላ በኩል የግለሰቡ ሕይወት በአደጋ ላይ እንዳይወድቅ ደኅንነቶችህን አስጠንቅቃቸው። ያንጠለጠለው የሚሥጢር ከረጢት ሽምቀቆውን የምንፈታው ይመስለኛል። መርማሪው ከአንተ ረዳት የተገናኘ መሆኑን ካወቀ በቀጥታ ትዕዛዝ ሊያስገድለው ይችላል። የሚያሰጋው መሆኑ ከተሰማህ በሕግ ከለላ ስር እንዲቆይ አድርግ። መታሰሩን ለሕይወቱ ጥበቃ እንዲያመች የተወሰደ እርምጃ መሆኑን ማመን አለበት።"

"የምትለውን ሁሉ ቀደም ብዬ አስቤበታለሁ። ለመከታተል እንዲያመቸኝ እንጂ ረዳቴ የጠየቀኝ በሕግ ከለላ ስር እንድናቆየው ነበር። ይኸኛውን መንገድ አልመረጥኩም። የአንድ ግለሰብ ሕይወት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ መጨነቅ ሳይሆን ጥረቴ ምንጩን ከማግኘቱ ላይ ያተከረ ነው። ሰውየውን ልናጣ እንችላለን ከሚለው ስጋት የደረስኩት አሁን ነው። ስለሆነም በሕግ ከለላ ስር አድርጎ የቀሩ መረጃዎችን መቀበል የተሻለ አማራጭ መሆኑን በደንብ ተገንዝቤአለሁ።"

"ትክክል ነው። የግለሰቡንም ሕይወት የመጠበቅ ግዴታም አለብን። ፖሊስ የሕብረተሰቡን ሰላምና ደኅንነት መጠበቅ እንዳለበት መዘንጋት የለብህም። መዳን የምትችል ነፍስ ለመዳን መንገድ እያላት መጥፋት የለባትም። ከሥራችን ጎን ለጎን ለዚህችም ጎስቋላ ነፍስ መጨነቅ ይኖርብናል። እየሠራን ያለነው ለሕዝቡ እስከ ሆነ ድረስ ማለቴ ነው። ለማንኛውም በሚመችህ መንገድ ማንንም በማይጎዳ መልኩ አድርገው።"

"ስለ ሁሉም ነገር በቀና መልኩ እንዲጠናቀቅ እፈልጋለሁ።" ሲል መለሰለት።

"መንገዱ እስካላደናቀፈ ድረስ እርዳው እንጂ ለአንድ ግለሰብ ነፍስ ብቻ ተጨነቅ የሚል አሳብ አልሰጥህም። በጉዳዩ የእኛም መስሪያ ቤት እጁን አስገብቶ እንደሚሠራ በእርግጠኛነት እነግርሃለሁ። ሁኔታው አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ስለ ተረዳን የፖሊስ መምሪያው ብቻውን እንዲወጣው የምንተወው ጉዳይ አይደለም። ከቢሮው ጋር በጥልቀት





ከተወያየንበት በኋላ ልዩ ኃይሎች እንዲመደቡ እናደርጋለን።"

የመምሪያው ኃላፊ ራሱን በአወንታ ነቀነቀ። የነገሩ ጫፍ የት እንደሚደርስ እያሳሰበው ከመሆኑ በቀር በውል ሊገምት አልቻለም። በድጋሚ ጭንቅላቱን አነቃነቀ። ውስጡ በተደበላለቀ ስሜት ታጭቋል።

"እንዳልከው በሕግ ከለላ ስር ቢደረግ ወደ ሌሎቹ የምናደርገውን ሩጫ ሊቀንሰው ይችላል። በርግጥ ግለሰቡ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ያም ሆኖ የእኛ ትኩረት የተሰወሩትን ወንጀለኞች መያዝ እንጂ ለአንድ ግለሰብ ሕይወት በመጨነቅ ፍለጋውን ማደብዘዝ አይደለም። ግለሰቡን እያበረታታን ወደ ዋናው የነገሩ ጭንቅላት መጠጋት አለብን። የሚፈጠረውን ባናውቅም የተሻለው አማራጭ ሊያጠቁት አለዚያም ሊያግባቡት ሲመጡ ቀንደኞቹን ወንጀለኞች ለመያዝ መጣር ነው።"

"እንደ ጥጃ አስረህ ከመጠበቅ ከፊት እንዲቀድም መንገድ እየሰጠኸው ከኋላው ጭራውን ተከተል።"

ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ መስኮቱ ተጠጋ። የአዲስ አበባ ሰማይ በጥቁር ደመና ተጋርዶ በመጥለቅ ላይ ያለችው የምሽት ፀሐይም በቀይ ደመና ተጋርዳለች። ከቅራቅንቦዎቹ የከተማዋ ቤቶች አናት ላይ ረዝመው የወጡት ፎቆች ጭንቅላታቸው ከጠቆረው ደመና ውስጥ ተመስጓል። በቅርብ ቀን አገልግሎት እየሰጠ ያለው የፌደራል ፖሊስ መምሪያ ዋናው ጽሕፈት ቤት ዘመናዊ ሕንፃ የኤሊኮፕተር ማረፊያ ጭምር አለው።

"ተቀብያለሁ" ወደ መስኮቱ እየቀረበ መለሰለት።

መንገዱ ሁሉ ጨርቅ ሆኖ እንደሚለሰልስ እርግጠኛ አልነበረም። በሲ አይ ኤ የስለላ ባለ ሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቶ በመጣመር የሚሠራው የጠቅላይ ሚኒስቴር ጊዜያዊ የጸጥታ መሥርያ ቤት አሠራሩ ግልጽ ያልሆነና የተወሳሰበ ነው። አዲስ የተቋቋመው የደኅንነት መሥሪያ ቤት በጉዳዩ መግባት ለሚከታተለው የወንጀል ማጣራት ሥራ ፈታኝ እንደሚሆንበት ተሰምቶታል። (ውጭዎቹ የኃያላኑ የስለላ ድርጅቶች የቴክኒክና የቁሳቁስ ድጋፍ ክትትል እየተሰጠው ያለው የጠቅላይ ሚኒስቴር የመረጃ መሥሪያ ቤት የአሠራር ሂደት ለምንም የማይመችና ከፈንጅ ማጥመጃ ሽቦዎች የበለጠ የተጠላለፈ በትንሽ ስህተት ከአደጋ ላይ የሚጥል እንደ ሆነ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ማንኛውንም ነገር ቀለል ባለ መንገድ እየመረጠ በሚመቸው የአሠራር ዘዴ የቻለውን ያህል እየሠራና ሲደክመው እያረፈ መከታተል የማይታሰብ ነው። እንቅልፍ አጥቶ ለበርካታ ሰዓታት መሥራት ይጠበቅበታል።

በዚህ ዓይነት የተጠላለፈ የመረጃ ሥራ አለቃና ምንዝር ብሎ ነገር አይኖርም። ወንጀለኞቹን ለማዳን ከበታች ሠራተኞች ጋር እኩል መሰለፍ ከበላይም ጋር አብሮ መምከርና መግባባት ይኖርበታል። መስኮቱን ተደግፈው እየተነጋገሩ በነበሩበት ወቅት አንድ ሰው ገባ።

ሲቪል የለበሰ ቢሆንም ወታደራዊ ሰላምታ ሰጠና በነበረበት በተጠንቀቅ ቆመ:: ዘሩባቤል ከጠለቀበት ሀሳብ ተመልሶ የገባውን ሰው ትኩር ብሎ ተመለከተው:: የመምሪያው ኃላፊ በበኩሉ ዘሩባቤልን በጥያቄ ዓይነት አስተዋለው:: ምንም ዓይነት መልዕክት ስላጣ ከውጭ ወደ ገባው ፖሊስ ተመለከተ:: በአንድ ነገር የተረበሸ መሰለው:: ትክክል ነው ፊቱ አመድ መስሎ ገርጥቷል:: በዝግታ እየተራመደ ወደ ወንበሩ ተጠጋና ፖሊሱን በድጋሚ ተመለከተው::

"አዲስ ነገር አለ?" ዓይኑን ወደ ጸጥታ ኃላፊው እየወረወረ ጠየቀው::

ፖሊሱ የተወደረ ሰውነቱን ፈታና ወደ ኃላፊው ተጠጋ:: ዘሩባቤል ፊቱን ወደ መስኮቱ መልሶ እንደ ቆመ ጆሮውን አነቃ:: አንድ ትወና ሊጀመር መሆኑ መንፈሱ ነግሮታል::

"የተፈጠረ ነገር አለ እንዴ? የተቻኮልህ ትመስላለህ" የመምሪያ ኃላፊው ድምጹን ቀንሶ በድጋሚ ጠየቀው::

በመስኮቱ ውጭውን እየተመለከተ ምን እንደሚባባሉ እንደሚከታተል ተገንዝቧል የመምሪያ ኃላፊ::

"በቅርብ የደረሰኝ ሪፖርት አለ:: መልእክቱ በቀጥታ ለእርስዎ በቴሌ ግራም የተላለፈ ነው::"

"ከየት?" የመምሪያው ኃላፊ ዓይኑ ፈጠጠ:: ቃላቱን በትክክል ቢሰማም የገዛ ጆሮውን የተጠራጠረ መሰለ::

"ከሀገር ውስጥ ደኅንነት ቢሮ ነው:: የመምሪያው ሹም ናቸው:: በቀጥታ እርስዎን ማነጋገር ይፈልጋሉ:: ከአንገቱ ወደ ፊት ረዘመ::"

የመምሪያው ኃላፊ ኮስተር ብሎ ተናገረ:: "ለምን በውስጥ መስመር አላገናኘሽኝም ነበር::"

"ማድረግ ነበረብኝ" አመነታ::

"በሚሥጢር ስልኩ ደውልለት በለው:: ስልኬን ክፍት አድርጌ እጠብቀዋለሁ::"

በበላይነት ለመኮፈስ ቢሞክርም ውስጡ እየቀለጠና እየራደ ነበር ያለው::

"እሺ ጌታዬ" በታዛዥነት አንገቱን ጎንበስ አድርጎ በተጠንቀቅ ቆመ::

"መሄድ ትችላለህ" ወደ በሩ አቅጣጫ በዓይኑ አመለከተው::

ሞቅ ያለ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ክፍሉን ለቅቆ ወጣ::

"እነኝህ ውትፍትፎች ጥቃቅን ምክንያት እየፈለጉ አዕምሮዬን ሊያፈነዱት ደርሰዋል ማለት ነው:: የተረገሙ ሰይጣኖች:: የመምሪያው ኃላፊ ብቻውን እያጉተመተመ ዘሩባቤልን ተመለከተው::

የምሥጢር ስልኩ ተንጫረረ:: ከማንሳቱ በፊት ምን ማለት እንደሚገባው ማሰብ ነበረበት:: ያለ መደነጋገር መልስ መስጠት ያስፈልጋል:: ትንሽ ስህተት የሕይወት መሠረትን ለማናጋት በቂ ነች:: ያውም በየአቅጣጫው የተናጋ ሕይወት::





"ከደኅንነት ቢሮ የጸጥታ ኃላፊ" በስልኩ ጫፍ የመጣው የሚርገበገብ የሚመስል ወንዳ ወንድ ድምጽ መንፈስን የማሸበር ኃይል የተገጠመለት እስኪመስለው ድረስ ውስጡን ሲያውከው ታወቀው:: ይህንን ድምጽ ከነ መጨረሻው መስማት ባልቻለ እንዴት ዕድለኛ በሆነም ነበር::

"ገባኝ ገባኝ:: ምን ልታዘዝ" ትህትና በታጀበበት ቅላጼ ለመናገር ሞከረ::

ከደኅንነት ቢሮ ኃላፊው ጋር ለረጅም ሰዓት በሚነጋገሩበት ወቅት ዘሩባቤል መስኮቱን ተደግፎ እንደ ቆመ ሲያዳምጣቸው ቆየ:: ስልኩን እንደ ዘጋ መለስ ብሎ ተመለከተው:: ጀርባውን በመስጠት በሰፊው መስኮት አሻግሮ ውጭውን በጨለማው ውስጥ እየተመለከተ ነው::

ከወዲያኛው ያለውን ቃል ባይሰማም የመምሪያው ኃላፊ የተናገረውን በሙሉ አድምጦታል::

"ከአገር ውስጥ የጸጥታና ደኅንነት ቢሮ ነው የተደወለው" የመምሪያው ኃላፊ አየር ስቦ ከአስወጣ በኋላ ተናገረ::

"ምንድነው የሚልህ? ያ መሥሪያ ቤት ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ የዘነጋው ይመስላል:: የሀገሪቱን ደኅንነት ለማስጠበቅና ሕዝብና አገርን ከአደጋ ለመከላከል መቋቋሙን የረሳው ይመስላል::"

"ተስፋ ከሚያስቆርጥ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የለብህም:: ችግሩ ያለው በመሥርያ ቤቱ አይደለም:: እንደ አዲስ እንዲቀጥል ለማድረግ ግለሰቦችን በማስወገድ ማዋቀር ያስፈልጋል::"

የደኅንነት መሥርያ ቤቱ ከአፄው መንግሥት ጀምሮ ብዙ ሥራዎችን ሲሠራ የቆየ ቢሆንም እንደ ተጣለበት ኃላፊነት የግለሰቦችን ክብርና ጥቅም ከማስጠበቅ በዘለለ በሀገር ጥቅምና ደኅንነት ማስጠበቅ በኩል የሠራው ፋይዳ አልነበረም:: ጠንካራ ኃላፊነት የሚሰማው የስለላ ድርጅት ለዚች ጥንታዊና ታላቅ አገር ያስፈልጋታል ተብሎ ቢታመንም በሥነ-ምግባርና በአገር ፍቅር የተገነቡ ባለ ሙያዎችን ማፍራት ሳይችል ነው የቆየው:: ጥቅሙንና እራሱን ለሀገሩ ደኅንነትና ታላቅነት ሲል አሳልፎ የሚሰጥ ባለሙያ ቦታውን ሊረከብ አልቻለም:: መሥርያ ቤቱ ይፈተሽ ቢባል በሀገር ደኅንነት ጥበቃው በኩል ያለው የሥራ ልምድ ይህንን ያህል ታሪክ ያለው አልነበረም:: ተቋሙ የአገርን ደኅንነት ከመጠበቅ ይልቅ ይሠራ የነበረው ለባለ ሥልጣኖቹ የግል ብልጽግና ስለ ነበር ጭራሽ ከወሮበላዎች ጋር የጥቅም ድርድር ተያይዟል::

"እንዳልከው መሥርያ ቤቱ በትክክል ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው ለማለት አያስደፍርም:: ቢሮው ብዙ ችግሮች አሉበት:: ከታተደለትና ከተጣለበት ኃላፊነት ውጭ እየሠራ እንደ ሆነ የአደባባይ ምሥጢር አድርጎታል::"

"በዚህ ዙሪያ ነበር የምትነጋገሩት?" የሚለውን ለመስማት የጓጓ መሰለ::

"ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ግምቱ ያልታወቀ ወርቅ በአንድ የአረብ ዜጋ በሕገ ወጥ መንገድ ሊወጣ ሲል* ተደርሶበታል:: ሕገ ወጦቹን ለመያዝ

ተጨማሪ ኃይል ወደ ስፍራው ላክ ነው የሚለኝ" በረጅሙ ተነፈሰ።

"እንዴት?" ዘሩባቤል። ጠየቀው።

"ሁሉንም ነገር በዝርዝር አልገለጠልኝም። የሱ ሠራተኞች እየተከታተሉት እንደ ሆነ ጠቅሶልኛል።"

"የጠየቀህን ኃይል ልትልክለት ወስነሃል ማለት ነው?" አንድ ዓይነት ስሜት ተነበበበት።

"በማሰብ ላይ ነኝ። የጠየቀኝን ኃይል መላክ እንዳለብኝ አምናለሁ።"

"የተባለው ሰው ብቻውን ነው?" ፊቱን ትኩር ብሎ እየተመለከተ ጠየቀው።

"ሊሆን አይችልም። ይህንን ያህል ዕቃ ለብቻው ይዞ ለመውጣት የሚሞክረው አይመስለኝም። ለማንኛውም የጠየቀኝን ኃይል መላክ አለብኝ።"

"እንደሱ አድርግ" አለው ዘሩባቤል።

"ምሥጢሩን እየተከታተለ የነበረውን የውስጥ ሠራተኛ ወደኔ መላኩን ገልጾልኛል። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ይደርሳል። ስለ ሁሉም ነገር እሱን ከአነጋገርሁ በኋላ ከአንተ ተነጋግሬበት እንወስናለን። ሰውየውን ለብቻው ማነጋገር አለብኝ። ለትንሽ ጊዜ ከጸሐፊዋ ቢሮ ትጠብቀኛለህ። የምንነጋገረውን ስለምቀዳው የሰጠኝን መረጃ ከድምጽ ማህደሩ መስማት ትችላለህ።"

ከደኅንነት ቢሮ የተላከው ሰው ቀልጣፋና የራስ ቅሉ እንደ ጣልያን ኮዳ ከጉንና ጉን የተጣበቀ የሚመስል ዓይኖቹ ልምና መልኩ ብጭጭ ያለ ቀይ ነበር። ፍጥነቱ እንደ ሸማኔ መወርወርያ የተካለበ ነው። ወደ ቢሮው ከመግባቱ እያንዳንዱን ነገር አንገቱን እያዘዋወረ ፈተሸው። ሁለመናው የፈጠነ ነው። የማስታወሻ ደብተሩን እያገላበጠ በልም ዓይኖቹ ሰረቅ እያደረገ የመምሪያውን ኃላፊ ተመለከተው። ኃላፊውም እያየው ነበር። ትናንሽ ልም ዓይኖቹን ልብ ብሎ አስተዋላቸው። በፍጹም የሚያዩ አይመስሉም። መልኩ ከቀይነት ወደ ቢጫ ቀለም ስለሚያደላም ከቻይና ስለ አለመደቀሉ ማረጋገጫ አይገኝለትም። መልኩ ብቻ ሳይሆን አቋሙም እንደዚሁ ከሩቅ ምስራቅ አገራት ሕዝቦች ጋር ይቀራረባል። ፍጥነቱም እንደዚሁ ከነዚያ ሕዝቦች የሚቀራረብ ነው።

"አንድ ነገር በማደን ላይ እንደ ሆናችሁ አለቃህ ነግሮኛል" ፊቱን እያጠና ጠየቀው የመምሪው ኃላፊ።

"ጎፋ ገብርኤልም አንድ አስገራሚ ታሪክ ተፈጥሯል። ያልተለመደ ክስተት ነው" ሁለት እጁን እያፋተገ ሌላም መረጃ ጠቆመው።

"የምን ታሪክ ነው? ተዘረፈ?" የተደናገጠ በሚመስል ድምጽ ጠየቀው።

ሰውየው ዓይኖቹን ፊት ለፊት ተከለበት። እሱም ትክ ብሎ አስተዋለው። ልም ዓይኖቹ ቅንድብ ስለ ሌላቸው የጉርጥ ዓይን ይመስላሉ።





"ምን ዓይነት አስቀያሚ ፍጥረት" የመምሪያው ኃላፊ ዓይኑን ከላዩ ነቀለ።

"እንደሱ አይደለም ጌታዬ። አንተ ከምትለኝ ትንሽ ለየት ያለ ክስተት ነው የታየው።" ዓይኖቹን ወደ ማስታወሻው መልሶ ተመለከተና ቀና አለ።

ለወሬ የሻቀሉት የመምሪያው ኃላፊ ቀልቦች በላዩ ላይ ነበሩ።

"እና ምን ተፈጠረ ልትለኝ ነው?" ዓይንና አፉን ከፍቶ ተመለከተው።

"ነገሩ የሚታመን አይመስልም። ለመቀበል አስቸጋሪ ነው። ያም ሆኖ ድርጊቱ ተከስቷል። ያልተለመደ ነገር ግን እየሆነ ያለ ክስተት በመሆኑ ያመንኩት በስፍራው ደርሼ ከተመለከትሁ በኋላ ነው። አራት ሰዎች በቤተ መቅደሱ በስተ-ደቡብ ምስራቅ በኩል ደርቀው ተገኝተዋል።"

"አልገባኝም" አለ እየተቁነጠነጠ የመምሪያው ኃላፊ። "የምን ሰዎች ናቸው ደርቀው የተገኙት?" ግራ የተጋባ መሰለ።

"በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ በገለጽኩልህ ስፍራ ላይ ሰዎቹ አፋቸው ተለጉሞ ተገኝተዋል። እስከ አሁንም ድረስ ምንም መናገር አይችሉም። ከነሱ ሌላም ሦስት ሰዎች እንደ ጨው አምድ ደርቀው አይቻለሁ።" እነዚህ ግን በሕይወት ያሉ አይደሉም።"

"ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?" የመምሪያው ኃላፊ ግራ መጋባቱ ጨመረበት። "ተገድለው ተገኙ ልትለኝ አስበህ ነው?" ጠረጴዛውን በስኪሪኝቶው እየወገረ ጠየቀው።

"አይደለም ጌታዬ። በፍጹም የሰው እጅ አላረፈባቸውም። ሁለቱ የውጭ አገር ዜጎች ሲሆኑ ሦስቱ ግን ኢትዮጵያውያን ናቸው። በሕይወት የሌሉት ሁሉም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን አረጋግጫለሁ።"

"ወደ ቤተክርስቲያኑ ለምን ሊገቡ እንደ ቻሉ የታወቀ ነገር የለም?"

"እንደበታቸው በመዘጋቱ ለምን ሊገቡ እንደ ቻሉ ጠይቆ መረዳት አልተቻለም። ቤተ ክህነትም የጠፋ ነገር ካለ በማጣራት ላይ ስለ ሆንሁ ለጊዜው መግለጫ አልሰጥም ብላለች። እንደሚመስለን የታቦቱ ቁጣ ሳይሆን አይቀርም።"

"ይህንን ሪፖርት የሰማኸው በስንት ሰዓት ላይ ነበር።"

"ከቀኑ አራት ሰዓት ላይ ነው። ሪፖርቱን እንደ ሰማሁ ወደ ስፍራው ሄጄ ስለ ነበር የተባሉትን ሰዎች በዓይኔ አይቼ አረጋግጫለሁ። ሦስቱ ሰዎች በቤተ ክርስቲያኑ በስተ-ምስራቅ በኩል ከቤተ-መቅደሱ በሃምሳ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ዋሻው የሚያስገባውን በኮንክሪት የተዘጋ በር ለመክፈት በሚቆፍሩበት ወቅት መድረቃቸውን ከስፍራው ከነበሩ ሰዎች መረጃ አሰባስቤአለሁ። ወደ ዋሻው ለመግቢያ የተዘጋጀውን በር ለመክፈት ሲታገሉ እንደ ነበር በእጃቸው ተጣብቆ ያለው የዲጂኖ ብረት መጠነኛ የሆነ ፍንጭ ይሰጣል።"

"የምን ዋሻ ነው የሚከፍቱት?" አለ የመምሪያው ኃላፊ::

"የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ያረፈው ከምድር ውስጥ በተገነባ ሰው ሰራሽ ዋሻ ላይ እንደሆነ ተነግሮኛል። በግራውንዱ ዋሻ ውስጥ ብዙ መናንያን መነኩሴዎች ተሰውረው ይኖራሉ የሚል ግምት አለ። አንድ አባትም የገለጹልኝ ይህንኑ ነው። ሰዎቹ የኮንክሪት መከደኛውን ለማንሳት ወፍራም የፌሮ ብረት አስገብተው በኀበጡበት ቀና ሳይሉ ደርቀው ቀርተዋል። ሕዝብ ለማነቃነቅ ቢገፋቸውም ትንሽ እንኳን ነቅነቅ ሊያደርጋቸው የቻለ የለም። ይህ አንዱ አስገራሚ ትእይንት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰዎቹ በቆሙበት ስፍራ እየተወረወረ የሚወጣ የሳት ነበልባል ይታያል። ወላፈኑ ደርቀው የቀሩትን ሰዎች አያቃጥላቸውም። እየሆነ ያለው ሁሉ ተአምር ሊባል የሚችል ነው::"

"ጠዋት በአራት ሰዓት የደረሰን መረጃ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ነው ሪፖርት የምታደርግልኝ?" ሰዓቱን እየተመለከተ ጠየቀው::

"በፍጹም አላረፍኩም ነበር::"

"ኘሬሶች አውጥተውታል?"

"ቀን የሚታተሙ ጋዜጦች ስለሌሉ አልወጣም::"

"በሬድዮስ የተላለፈ ነገር ይኖራል?"

"የሬድዩ ጣቢያዎችን እንዳያስተላልፉ በስልክ ነግረናቸዋል::"

የመምሪያው ኃላፊ የሚሰማው ሁሉ ከእሱ እሳቤና ቁጥጥር ውጭ ስለሆነ በረጅሙ ተንፍሶ ተመለከተው::





# ምእራፍ ሀያ

የአረብ መልክ ያለው ዕድሜው በሃምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ እንግዳ በተፈቀደው የመኪኖች ማቆሚያ ስፍራ የኪራይ ማርሴዲስ መኪናውን አቆመና ወደ ሕንፃው በሚያስተላልፈው ደረጃ እየተፋጠነ ገሰገሰ። ከመጨረሻው ደረጃ ላይ እንደ ደረሰም የይለፍ ፈቃዱ ወደሚታደስበት አንደኛ ፎቅ ሁለት ሁለቱን ደረጃ እየተራመደ ወጣ። "የይለፍ ፈቃድ ዋና ቢሮ" የሚለውን ጽሑፍ እንደተመለከተም እንደ መቆም ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ። የጥንቱ የሀገር ግዛት ሚኒስቴር የአሁኑ የሕዝብ ደኅንነት መሥሪያ ቤት በመቶ የሚቆጠሩ ባለ ጉዳዮች አጨናንቀውታል። በረንዳው ላይ ተቀምጠው ተራ የሚጠብቁትን ሰዎች እየገረመማቸው አልፎ ከአንድ በር ላይ ሲደርስ ቆመ። የማይቀር ጉዳይ ነው። የተዘጋውን በር በማንኳኳት ወደ ውስጥ ዘለቀ። ከሚያደርገው እንቅስቃሴ መረዳት የሚቻለው ለስፍራው እንግዳ ያለ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በራስ የመተማመን መንፈሱንም ጭምር ነበር። ወደ ቢሮው እንደ ገባም የፋይል ጥራዝ የተሸከመች ልጅ እግር ሴት ገጠመችውና ኃላፊው መኖሩን የአረብ ቃና ባለው እንግሊዝኛ ጠየቃት። በግንባር ምልክት ስትነግረው ጊዜ አላባከነም። የተዘጋውን በር ገፋ አድርጎት ወደ ውስጥ ገባ። "የይለፍ" ተጠሪው በራሱ አሳብ ተውጦ አንድ ነገር እያብሰለሰለ ነበር። በድንገት በሩን በርግዶ የገባው እንግዳ ያለ ማንም ጋባዥ ከወንበሩ ላይ በመቀመጥ ቀጭን ፉጨት አፏጨ። ባለ ሥልጣኑ በትኩረት እየተመለከተው ግራ በመጋባት እንደ መሳቅ ከጀለው::

"ምነው ምን ተፈጠረ? እንደ ሕፃን መሆን ያስደስትሃል ማለት ነው?" ባለ ሥልጣኑ ቀልዶ እራሱ ሳቀ።

አረቡ ከመጠን በላይ በመደንገጡና በመበሳጨቱ ፊቱ የተጠበሰ ሳምባ መስሏል።

"ምናባክንስና ያንተከትክሃል? በሰው ላይ እየዘለሉ ለመደነስ መሞከር ከየት የመጣ ድፍረት ነው::" ባለ ሥልጣኑ በውስጡ አጉተመተመ::

"ምን የተፈጠረ ይመስልሃል?" መልሶ ጠየቀው አረቡ። የደፈረሰው ደሙ በፊቱ ላይ ሲተረማመስ ቢመለከተውም አላስበረገገውም።

"ምንም የደረሰህ ሪፖርት የለም ማለት ነው? ወይስ እንደ ሞኝ እየቀለድክብኝ ነህ::"

"ሂልተን ሆቴል ችግር እንደ ተፈጠረ ለቢሮአችን ጥቆማ ደርሶት እያጣራነው ነን። በሱ ውስጥ የአንተ ሰዎች አሉበት እንዴ?" አለ ባለ ሥልጣኑ::

"እየቀለድክብኝ መሰለኝ?" በእልህ እየተናጠ ተወራጨ። "ጥሩ

ትቀልዳለህ። ያም ሆኖ ቀልድህ የሚያዝናና አይደለም። እንደ ገና ለመተወን ሞክር" ከአንገቱ ወደ ፊት እየተጠጋው በጥርሱ መካከል ተናገረው አረቡ።

"የምቀልደው ከለቅሶ በዘለለ ማንንም አስቆ አያውቅም። አንተም የምትነግረኝ ይህንኑ መሰለኝ" ሳቅ አለ ባለ ሥልጣኑ።

"መሐመድን የአንተ የደኅንነት ሠራተኛ ገድሎታል። ከሱ ጋር የእናንተ አባል የነበረ አንድ ሰውም አብሮ ተገድሏል።"

"የእኛ ሠራተኛ ስለ መገደሉ ምን መረጃ አለህ" አለው ባለ ሥልጣኑ።

"መረጃ አይደለም ያለኝ የገደለውን ሰው በትክክል ደርሼበታለሁ" ፎቶውን አውጥቶ እያቀበለው "ድድብናህን ለኔ ለማሳየት በመተወን ላይ ነህ። እንዳልከው ቀልድህ ወዝ ያጣ ኮቸሮ ስለ ሆነ ለሳቅ አይሆንም። ይህንን ከተረዳኸው ቀልድህን እንድታቆም እመክርሃለሁ"።

"አንድ ጊዜ ቆም በል" አለ ባለ ሥልጣኑ።

"ገድሏቸው ሲወጣ ቀጥሎ ከነበረው ክፍል ሰዎች አይተውታል።"

"እርግጠኛ ነህ ወይስ ግምት ነው?" የይለፍ ባለስልጣኑ በትኩረት ተመለከተው።

"እርግጠኛ ነኝ። ከሚቀጥለው ክፍል የነበሩ ሰዎች በመስኮት በኩል ሆነው ሁሉንም ነገር እየተከታተሉ ነበር።"

ለተወሰኑ ደቂቃዎች በሁለቱ መካከል ጸጥታ ሰፍኖ ያለ ምንም ንግግር ቆዩ።

ሁኔታው ጥሩ ሊሆን እንደማይችል ሲረዳው የይለፍ ባለ ሥልጣኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ልቡን ጥርጣሬ ተሰማው። ሁሉም ነገር እየተበላሸ ነው።

"ለምን ሲይዙት አልሞከሩም ታዲያ?" የማሽሚጠጥ ቀልዱን ሲደግምለት አረቡ ተበሳጨ።

"መሣሪያ አልታጠቁም ነበር?" የውስጥ ንዴቱን ለማመቅ እየታገለ መለሰለት።

ልክስክስ ከሃዲ! ለራስህ ስትል የኔን መውጫ ታዘጋጃለህ ካለበለዚያ ጉድህ እየተጎለጎለ ይወጣል። አለ በውስጡ።

"እንደዚያ ከሆነ አስገራሚ ታሪክ ነው የምትነግረኝ።"

"ደደብ ነህ" አረቡ በልቡ ውስጥ እጉተመተመና ትኩር ብሎ እየተመለከተው መናገር ጀመረ።

"ታሪክ ሳይሆን የተደረገ ዜና ነው የምነግርህ። ጉዳዩ የሚመለከተው አንተን ሊሆን ስለሚችል ቀልድ መሳይ ድራማህን ትተህ ብታስብበት የሚሻልህ መሰለኝ።"

"እና ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው?" እስከ መጨረሻው በድፍረት ለመቀጠል የተሳነው መሰለ የይለፍ ባለ ሥልጣኑ።

"ፊቃዴን አድስልኝና ዛሬ ምሽት ኢትዮጵያን. . . " አንጠልጥሎ ተወው።





ኃላፊው በረጅሙ ተነፈሰና ከወንበሩ ላይ ወደ ኋላው በመለጠጥ የሚያስብ መሰለ።

ከብዙ ውዝግብ በኋላ ከባለ ሥልጣኑ ቢሮ የወጣው ደስታ ሳይሰማው እየተበሳጨ ነበር። በሁለቱ ባልደረቦቹ መገደል ብቻ ሳይሆን የእሱም ቀጣይ ሰጣ ፈንታ አሳስቦታል። የአዲስ አበባ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫን ይዞ ገሰገሰ። በሃሳቡ እየተብሰለሰለ መኪናውን በሚያሽከረክርበት ወቅት ከመንገድ ላይ ምን እንደ ገጠመውም እንኳን ትዝ አይለውም። ፍተሻ ጣቢያው ከመድረሱ ቀደም ብሎ ብዙ ማሰብ ቢኖርበትም አላሰበም። ፖሊስ ለየጣቢያዎቹ ትዕዛዝ ሰጥቶ ከሆነ በቁጥጥር ስር መዋሉ የማይቀር ነው። የይለፍ መምሪያ ኃላፊው ሁኔታም ይህንን ያረጋግጣል። መኪናውን አቆመና መሪውን ተደግፎ ለብዙ ሰዓት ሲያስብ ቆየ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ወደ ቃሊቲ ስለ ሄደበት ሁኔታ የሚያውቀው ነገር አልነበረም።

እራሱን እየነቀነቀ ብቻውን ከተነጋገረ በኋላ የመኪናውን አፍንጫ ወደ አዲስ አበባ አቅጣጫ ጠመዘዘ። የቃሊቲ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን በቀኝ እየተመለከተ ትንሽ ከፍ እንዳለ ዋናውን መንገድ ለቀቀና በግራው በኩል በመታጠፍ የነዳጅ ማደያውን አልፎ ክራውን ሆቴል ገባ። ወደ ሆቴሉ የመኝታ ክፍሎች ያመራው ከመጠን በላይ እየተቻኮለ ነበር። ከመተላለፊያው ላይ ያገኛትን አንዲት ሴት ገፍትሯት አለፈ። ለማሰብ አረፍ የሚልበት ቦታ ያስፈልገዋል። አዕምሮው እየተዛባበት ነው። እረፍት አድርጎ ምን እያደረገ እንደ ሆነ በትክክል ማወቅ ይኖርበታል። ክፍል እንደ ገባ ገላውን በቀዝቃዛ ውኃ ተለቃለቀና በማቀምቀም ላይ ያለውን ጺሙን ሙልጭ አድርጎ ላጨው።

የመቅለል ስሜት እየተሰማው ቢሆንም አልተረጋጋም። የሁለቱ ጓደኞቹ አሟሟት አይደለም እንደ አልኮል ያሰከረው። የይለፍ ባለ ሥልጣኑ ያሳየው ሥነ-ምግባር የጎደለው ድርጊቱ በራሱ ወደ እብደት የሚስደድ ነው። ከሻወር ቤቱ ወጣና ከነልብሱ ጋደም ለማለት ሞከረ። እንቅልፍ እንዲወስደው አልፈለገም። የሚቀረው ጣጣ አለ። የሆቴሉን ፎርም አልሞላም። ፎርሙን ሞልቶ ጣጣውን ከጨረሰ በኋላ ነው ማረፍ ያለበት። በጥንቃቄ ለመከታተል ጣጣውን ቀድሞ መጨረስ አለበት። በዚህ መካከል አንድ ነገር ትዝ ሲለው ስልኩን አንስቶ የሚፈልገውን ቁጥር እንዳገኘ ወደ ጆሮው አስጠጋ። ድምጽ እንደ መጣለት እርጋታ በማይታይበት ሁኔታ መናገር ጀመረ። አንዱን በሌላው ላይ እየደራረበ ያለፋታ መናገሩን ቀጠለ።

"የኢየሱስ ያለህ አብዱልአዚዝ ረጋ ብለህ አናግረኝ እንጂ" ሊያረጋጋው ሞከረ ስልኩን ያነሳው ሰው።

"እየነገርኩህ ያለሁት በአደጋ ውስጥ መሆኔን ብቻ ነው። በድርጊቱ ፖሊስ እጁን እንዳስገባበት እርግጠኛ ነኝ። የደኅንነት መሥርያ ቤት የይለፍ ባለ ሥልጣኑም ያሳየኝ ቸልተኛነት ያለፈውን

ግንኙነታችንን ስላላስታወሰኝ እጀግ አሳስቦኛል:: ይኼውልህ ፓስተር እንድትረዳኝ የምፈልገው ከአዲስ አበባ ሳልወጣ እራሴን የምደብቅበት ስፍራ እንድታዘጋጅልኝ ብቻ ነው::"

"ወደ ኤምባሲህ መግባት አትችልም?" የፕሮቴስታንቱ ኃላፊ ሌላ መላ ሊጠቁመው በመሞከሩ አበሳጨው::

"እንደዚያ አላደርግም:: በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው የሀገሬ መንግሥት በማያውቀው መንገድ መሆኑን ጠንቅቀህ ታውቃለህ:: የሳውዲና የኢትዮጵያ መንግሥትም በጸጥታ ጉዳይ ላይ በጋራ ይሠራሉ:: ደኅንነቶች እየተከታተሉኝ እንደ ሆነ እየተሰማኝ ነው:: ወደ ኤምባሲዬ ብሄድ እጀን አንጠልጥለው ለደኅንነቶች ይሰጡኛል:: ያንን ባያደርጉም እንኳን በሰንሰለት አስረው ወደ አገሬ ይልኩኛል:: በዚህ መልኩ ወደ አገሬ ብመለስ የሚጠብቀኝ... የአንገት መቀላት እንደ ሆነ ይገባሃል?"

"እና ምን ይሻላል ትላለህ?" ዶክተሩ በጭንቀት ቀጠለ:: "በምን መንገድ ነው አንተን ከደኅንነቶች ክትትል ላስመልጥህ የምችለው?" የፕሮቴስታንቱ ቄስ በወዳጅነቱ ሳይሆን ለራሱ ጭምር እየተጨነቀ መልሶ ጠየቀው::

በርግጥም የአብዱልአዚዝ በደኅንነቶች እጅ መግባት የብዙ ሰዎች መዘዝ ነው:: ቄሱም ቢሆን የሠራውን ያውቃል:: አብዱልአዚዝ እግረ መንገዱን የሚነግረው ይህንኑ እንደ ሆነ ገብቶታል::

"አላውቅም" አለው ተስፋ በመቁረጥ "የማውቀው ቢኖር አገርህ ስለ ሆነ በሆነ ቦታ ደብቀህ ከደኅንነቶች እጅ እንዳልገባ ልታደርግ እንደምትችል ብቻ ነው::"

"አይመስለኝም አብዱልአዚዝ:: ደኅንነቶች እየተከታተሉህ ከሆነ በፍጹም ዋስትና ልሰጥህ አልችልም::"

"እስከሚረጋጋ ድረስ እራሴን የማቆይበት ስፍራ እንድትፈልግልኝ ነው እየነገርኩህ ያለሁት:: ያንን የማታደርግ ከሆነ ችግሩ የኔ ብቻ አይደለም:: በጉዳዩ ትልቁን ድርሻ የሚሸፈነው ማለቴ እኔ ከሚደርስብኝ በላይ ችግር የሚገጥምህ አንተን ነው::"

"አዝናለሁ አብዱልአዚዝ:: እንደዚህ በአለው ሁኔታ ላይ እጀን አልከትም:: ከአሁን በፊት የደረሰብኝን ታውቃለህ:: እባክህ አታስቸግረኝ:: ምንም የምረዳህ ነገር ያለ አይመስለኝም:: ከአንድ ቦታ ሁንና የሚመጣውን ተጠባበቅ::"

ዶክተሩ በሕገ ወጥ ንግድ ተጠርጥሮ እስር ቤት ከመግባቱም ከእሱ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረ ፈረንጅ በግብረ ሰዶም ተከሶ በህብረተሰቡ ዘንድ ጥሩ ስም የለውም:: በመንግሥት በኩልም የሚታየው በአይነቁራኛ ነው:: የጎደፈ ስም ባለቤት ነው::

"እራስክን በአገኘኸው ቀዳዳ ወትፈህ ተሰወር የማውቀው ይህንን ብቻ ነው" ስልኩ በላዩ ላይ ተዘጋ::





"የውሻ ልጅ ድሮስ አበሻ መቼ ልቡን ሰጥቶ ያውቃልና ነው" አብዱልአዚዝ በደኅንነት ፖሊሶች ክትትል እየተደረገበት መሆኑን ሲያስበው በንዴት ጭንቅላቱን አወዛወዘና ከሆቴሉ ጋር የሚያገናኘውን የመጥሪያ ደወል ተጫነው::

በሩን ከፍቶ የገባው አስተናጋጁ ሳይሆን የቅፅ መሙያ ፎርም የያዘች ልጅ እግር ሴት ነበረች:: ውስጡን ቅሬታ እየተሰማው ልጅቷን ተመለከታት::

ምንም ትኩረት ሳትሰጠው ፎርሙን እያቀበለችው "ይቅርታ ቅድም ዝም ያልኩት በጣም ተዳክመው ስለ ነበር እንዳላስቸግርዎት ብዬ ነው" አለችው::

ሊስቱን ስታስተካክል ፓስፖርቱን ሰጣት:: ቁጥሮቹን ሞልታ ስትጨርስ አንዳንድ ጥያቄዎችን አቅርባለት አመስግናው ወጣች::

ሆቴሎች አልጋ ከመያዙ በፊት በቅድሚያ መታወቂያ አለዚያም ፓስፖርት እንደሚጠይቁ ያውቃል:: እንደዚያ ማድረጋቸውም ስህተት እንዳልሆነ ያምናል:: ማን የት እንዳለና ከማን ጋር ምን እየሠራ እንደሚገኝና የከተማዋን ጸጥታ የሚቆጣጠሩበት ከደኅንነት ቢሮ ጋር የተዘረጋ የተጠላለፈ አሠራር እንደ ሆነ ገብቶታል:: የዚህ ዓይነት አሠራር በአንድ ጐኑ እንግዶች የሚያንገላታ ቢመስልም ከሕግ አንጻር ትክክል በመሆኑ ብዙም ቅር ሳይለው ለፎርም ሞይዋ ጥያቄዋን መለሰላት::

ክራውን ሆቴል የመኝታ ክፍል ውስጥ መሆኑንና የተኛበትን የአልጋ ቁጥር የአዘዘውን የምግብና የመጠጥ ዓይነት ለሀገር ውስጥ ደኅንነት ሠራተኞች ሪፖርት የደረሳቸው ሆቴሉ በገባ በደቂቃዎች ልዩነት መሆኑን አብዱልአዚዝ የሚያውቀው ነገር አልነበረም:: የሚጠጣው ነገር ከክፍሉ ድረስ እንዲመጣለት አዝዞ ሁሉም ነገር ቀርቦለታል:: ከምግብ በኋላ ቡና የጠጣውም በአልጋው ላይ እንደተጋደመ ነበር:: ይሁን እንጂ እሱ እንዳሰበው መንፈሱ ሊረጋጋለትና እረፍት ሊያገኝ አልቻለም:: ሃሳብ በሃሳብ ላይ እየተቀጣጠለ አዕምሮውን ሊያፈነዳው ትንሽ ነው የቀረው::

ሰዓቱን እርግጠኛ ባይሆንም በደኅንነቶች እጅ መግባቱ የማይቀር መሆኑን ተረድቷል::

# ምእራፍ ሀያ አንድ

ሰዓቱ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ነው፡፡ ከደኅንነት መሥርያ ቤት የወጣውን ጥቁር ማርሴድስ የደቡብን አቅጣጫ ይዞ እየከነፈ ጎተራ ተብሎ ከሚጠራው የባቡር ሃዲድ መስመር ላይ ደረሰ፡፡ ከውስጡ ሹፌሩን ጨምሮ አራት ሰዎች የተቀመጡ ሲሆን የደኅንነት መኮንኑን ያጀቡ ስቪል የደኅንነት ዘቦች አውቶማቲክ ሽጉጥ የታጠቁ ናቸው፡፡

በየጎዳናው ዳር የተደረደሩት የመሸታና የመጠጥ ግሮሰሪዎች በጠጭዎች ተጨናንቀው ሰካራሞች እየጮኹ ይደንሳሉ፡፡ የምሽት ሴቶች በመንገዱ ግራ ቀኝ በየፖሉ ጥላ ስር ሁለትና ሦስት እየሆኑ ደንበኛ እየተጠባበቁ ናቸው፡፡ የቤት መኪናዎች የመንገዱን ጠርዝ ይዘው እየቆሙ ከሴቶቹ ጋር ይደራደራሉ፡፡ አዲስ አበባ ለምሽት ተረኞች ትራፊኳ ክፍት ሆኗል፡፡ ጨለማን ተገን አድርጎ አንደኛው ሲሸጥ፣ ሌላኛው ሲገዛ፣ አንደኛው ሲቀማ ሌላኛው ሲቀማ በጎስቋላዋ ከተማ ጎስቋላው ንግድ ደርቶ ሸማችና ገዢው ይጣደፋል፡፡

የአጥሩን ዙሪያ ያስጌጡትን የተለያዩ መብራቶች እየተመለከተ ወደ ነገረው አቅጣጫ በመታጠፍ ክራውን ሆቴል ውስጥ ገባ ማርሴዲስ፡፡

በሩ ሲንኳኳ የእርግማን መአት ለማውረድ ሲዘጋጅ በድጋሚ ተንኳኳ፡፡ በዚህን ጊዜ ነበር ራሱንና ያለበትን ቦታ የተገነዘበው፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ሲንኳኳ "ማነው?" አለ አብዱልአዚዚ፡፡

"እኔ የሆቴሉ ኃላፊ ነኝ" አለ ዘሩባቤል፡፡

በሩ የመሸከርከር ድምጽ አሰምቶ ሲከፈት የመርማሪው ሽጉጥ ደረቱ ላይ ተደቀነ፡፡ "ምን እየሆንክ ነው" ሲል ጠየቀው፡፡

"ወደ ውስጥ ግባና እንነጋገራለን፡፡"

ይህ እብድ አበሻ ለመተኮስ አስቧል ማለት ነው ሲል አሰበ አብዱልአዚዝ፡፡ ያለ ምንም ማመንታት ይህንን ያደርጋል አለው ለራሱ፡፡

"እጅህን ከፍ አድርግ" አለው ዘሩባቤል፡፡

ካቴና አጠለቀለትና ፍራሹን እየገለጠ መበርበር ሲጀምር ሳቅ አለ፡፡

"ሽጉጥ የደበቅሁ መስሎህ ነው፡፡"

"እንዴት ነው ይህንን ሆቴል ወደድከው?" አለው በሹፌት፡፡

ወንጀል መርማሪዎች ተራ የሚመስል ጥያቄ ማቅረብ ከሚሰጣቸው ኮርስ አንዱ መሆኑን ሲረዳ ጥያቄው ተገቢና ተራ እንዳልሆነ ተገነዘበ፡፡ የአተካሮ ጓዳ ማንጎዳጎድ የለበትም፡፡ የሽጉጥ ሰደፍ ይከተለውና መንጋጋዎቹ ሊረግፉ ይችላሉ፡፡

"ተስማምቶኛል፡፡" አለው ቀልድ ለመለማመድ እየሞከረ፡፡

"ዘሩባቤል እባላለሁ፡፡ በሀገር ውስጥ ደኅንነት መሥርያ ቤት





የመረጃ ሠራተኞች ተቆጣጣሪ ባልደረባ መርማሪ ሹም ነኝ" ውብ ጥርሶቹን ገለጥ አርጐ አሳየው፡፡ መልኩንም ስሙንም ያውቀዋል አብዱልአዚዝ፡፡

"ምን ስለ አጠፋሁ ልትመረምረኝ መጣህ?" የቅሬታ ጥያቄ አቀረበለት፡፡

"ያጠፋ ብቻ ይመርመር ያለው ማነው? ጤነኞቹም እኮ ለደኅንነታቸው ሲባል ቢጠየቁ አይከፋም፡፡ ቅር አለህ እንዴ?" ከውስጡ ድረስ ዘልቆ በሚገባ አመለካከት አስተዋለው፡፡

"ስለ ጤንነቴ ተጨንቀህ ከሆነ የመጣኸው አንተን ብቻ ሳይሆን መንግሥትህንም ጭምር አመሰግናለሁ" እጁ ላይ ያጠለቀለትን ካቴና እየተመለከተ መለሰለት፡፡

ወንጀለኞች ጸጥታ ሲበዛባቸው ከጥልቅ ውቅያኖስ ውስጥ እንደ ተወረወሩ ያህል ውስጣቸውን ቅዝቃዜ ስለሚሰማቸው የተጠየቁትን አይደለም ያልተባሉትንም መናገር ይጀምራሉ፡፡ የመለፍለፍ ዋናው ምክንያታቸው ጸጥታው የሚፈጥረው ቅዝቃዜ ለመሆኑ መርማሪው ያምናል፡፡ የተጠየቀውን ሁሉ በቀጥተኛ መንገድ መመለስ እንደሚገባው ለራሱ ማሳመን ነበረበት፡፡ በቃ ከዚህ በቀር የተሻለ የመውጫ ቀዳዳ ለነፍሱ የላትም፡፡

መከራከሩ የሚያዋጣ አይደለም፡፡ እነኚህ ዲሪቶዎች ሁሉንም ነገር ያውቃሉ፡፡ ግመል የሚያክለውን ወንጀሌን ከኒላዬ እየጎተተሁ አጎንብሼ መራመድ የሞኝ ሥራ ከመሆን ውጭ ግመሉን መደበቅ የምችልበት ብቸኛ ዘዴ ሊሆን አይችልም፡፡ እውነቱን ከመናገር ሌላ የተሻለ መንገድ የለም፡፡ "ከኔ የምትፈልጉት ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው፡፡

"ስምክን ከነ አያትህ የተወለድክበትንና ያደግህበትን እንደዚሁም የተማርክበትን በሥራ ዓለም ያሳለፍክበትን ሳታጠላልፍ እንድትተርክልኝ እፈልጋለሁ፡፡ እኔ ፓስፖርትህን እየተመለከትሁ ስለማረጋግጥ እንዳትሳሳት እረጋ ብለህ መገንዘብ ይኖርብሃል..." አስጠነቀቀው ዘሩባቤል፡፡

"እስከ አሁን የተናገርከው ትክክል ይመስለኛል" አለውና ትክ ብሎ ተመለከተው፡፡

"ልክ መሆኔን ስለምረዳ ነው የነገርኩህ" ሲል መለሰለት አብዱልአዚዝ፡፡

ዘሩባቤል የጸጥታ ፖሊሶቹ እንዲገቡ ጠራቸውና በታዛቢነት አስቀመጣቸው፡፡

"ዛሬ ኢምግሬሽን ቢሮ ሄደህ ነበር?" አብዱልአዚዝ ቀና አለ፡፡

"ሄጄ ነበር" ሲል በአጭር መለሰለት፡፡

"ምን ነበር የፈለግኸው?" የጓደኛ በሚመስል ዓይነት የውይይት ዘይቤ ነው ምርመራውን የጀመረለት፡፡

"የይለፍ ፈቃዴ እንዲታደስልኝ ነበር፡፡"

"ፈቃድህ ጊዜው አልፏል ማለት ነው?" የሚሰጠውን መልስ ቶሎ ቶሎ እየመዘገበ ነበር የሚጠይቀው፡፡

"አንድ ወር ያህል አልፎታል::"

"እንደ ወጣህ ያመራኸው ወዴት ነበር?" መጻፉን አቁሞ ተመለከተው:: ዘሩባቤል::

ረዳቶቹ የሚሰጠውን ቃል እየጻፉ ናቸው:: ከጠረጴዛው ላይ ያለችው መቅረጫም ሥራዋን ቀጥላለች አብዱልአዚዝም እየተናዘዘ ነው::

"የምፈልገውን ለይቼ የማውቅ አልመሰለኝም::"

"የምትፈልገውን ሳትረዳ የት ለመድረስ ተነሳህ?" ዘሩባቤል ሳቅ አለ::

"ኢምግሬሽን መሥሪያ ቤት በገባሁበት ሰዓት ከባለ ሥልጣኑ ጋር ስንነጋገር ያልጠበቅሁትን መልስ በማግኘቴ ይመስለኛል እራሴን ስቼ ነበር::"

"ከአንድ ሰው ጋር በስልክ ተነጋግረህ ነበር" ትክ ብሎ ተመለከተው::

"አዎን ተነጋግረናል::"

"ሰውየው ለምን ሊተባበርህ አልፈለገም" ትኩር ብሎ ተመለከተው::

"ሊያናግረኝ አልፈለገም ነበር" አለው በቁጭት ዓይነት::

"በጥሩ ሁኔታ ያላስተናገደህ ለምን ይመስልሃል? ሲል ጠየቀው::

"እራሱን ለማዳን ይመስለኛል" አለውና በረጅሙ ተነፈሰ::

"የሚጽፍበትን እስኪሪብቶ በጥርሱ መሃል ይዞ ዓይኖቹን አጥብቦ ተመለከተው:: "ከምንድነው ራሱን የሚያድነው?"

"አብሮን ይሠራ ነበር::"

"ምን ያህል እርግጠኛ ነህ?" እይታውን ሳይነቅል ለደቂቃ ተመለከተው::

"እርግጠኛ ነኝ:: አብረን ብዙ መንገድ ተጉዘን ከዚህ ደርሰን ነበር" የተቆጨ መሰለ አብዱልአዚዝ::

"አብረን ብዙ መንገድ ተጉዘን ከዚህ ደርሰን ነበር አልከኝ?" ሳቅ አለ::

"የነገሩን መበላሸት ተረዳውና ፊት ነሳኝ እንጂ እንደዚያ ነበር"::

"መቼ እደተገናኛችሁ ትዝ ይልሃል? የመጀመሪያ ግንኙነታችሁን ዘርዝር አድርገህ ብትነግረኝ..." ከባሻገሩ ያለውን ግድግዳ እየተመለከተ ጠየቀው::

"ጉሙሩክ የሚሠራ ሰው ነው ያስተዋወቀን:: የተገናኘንበትን ጊዜ በውል አላስታወሰውም::"

"ጉሙሩክ ያለውን ሰው ታስታውሰዋለህ? ከእሱ ጋር ያስተዋወቃችሁን::"

"አስታውሰዋለሁ" አለውና በረጅሙ ተነፈሰ::

"በምትሠሩት የሕገ ወጥ ዝርፊያ ውስጥ እሱም አለበት?" ሲል ጠየቀው::

"ወደ ውጭ ለሚወጡ ዕቃዎች ትብብር የሚያደርግልን እሱ ነው::"

"አሁንም በዚያው እየሠራ ነው?" መርማሪው የሚሰማው ሕልም ሁሉ እየመሰለው ነበር የሚያዳምጠው::





"ከትንሽ ጊዜ በፊት ተገናኝተን ስለ ነበር በዚያው መሆኑን ነግሮኛል::"

"በጉሙሩክ መስሪያ ቤቱ ውስጥ ያለውን የሥራ ድርሻ በትክክል እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ" ኮስተር ብሎ ተመለከተው::

ድርሻውን ሲነግረው በጥንቃቄ እያዳመጠ መዘገበ:: የተባለውን የጉምሩክ ተጠሪ ያውቀዋል:: በትንሽ ዓመታት ውስጥ ካቴጃሮች ተርታ ለመመደብ ወደ ፊት እየገሰገሰ ያለ ሰው ነው:: ረዳቶቹን ተመለከተ:: እነሱም ግራ በመጋባት ስሜት እየተመለከቱት ነበር::

"ከሱ ውጭ የምታውቃቸው ይረዷችሁ የነበሩ ግለሰቦችስ ይኖራሉ?" አለው የተለያየ ስሜት አእምሮውን እየበጠበጠው::

"በስም ልለያቸው አልችልም" እንጂ ብዙ" አለው::

"ከሀገር ውስጥ የደኅንነት ቢሮ እንደ ወጣህ በስልክ የተገናኘኸው ሰው እንደ ነበር ነግሬህ ነበር:: ከዚህ ሰው ጋር ለብዙ ሰዓት ተነጋግራችኋል:: ይህ ሰው ከእናንተ ጋር የነበረው ግንኙነት ምንድነው?::"

"አብረን አንዳንድ ነገሮችን ሠርተናል::" ሲል መለሰለት::

"እስቲ ዘርዘር አድርግና አስረዳኝ:: ግንኙነታችሁ በዚሁ ዙሪያ ነበር እያልከኝ ነው?" አለው ዘሩባቤል::

"የሜሪኩሪ ንግድም አብረን ሠርተናል:: ከሱ ጋር የነበረን ግንኙነት የቆየ ነው" አብዱልአዚዝ በረጅሙ ተነፈሰ::

"የቆያችሁ ወዳጆች ናችሁ ማለት ነው? ሜርኩሪንም አብራችሁ ትነግዱ ነበር:: ከሜሪኩሪው ጠቀም ያለ ትርፍ እንደምታገኙ እገምታለሁ:: ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገባህ?::"

"ወደ ኢትዮጵያ በመጀመሪያ የገባሁት ዲፕሎማት ሆኜ ነበር:: ከሥራዬ በተደራቢነት እከታተል የነበረው ሜርኩሪና የዩራንየም ማዕድንን" ቢሆንም ያን ያህል አመርቂ አልነበረም::"

"ዩራንየም በኢትዮጵያ ውስጥ አለ እንዴ?" በመገረም እየተመለከተ ጠየቀው::

"ትክክለኛውን የዩራንየም ማዕድን ልንደርስበት አልቻልንም:: ወደ መጨረሻ የእስራኤል ሰላዮች አግኝተው መውሰዳቸውን ሰምቻለሁ::"

"የምትለኝ ሁሉ ትክክል ነው? እንዳትሳሳት ተጠንቀቅ" አለው::

"ትክክል ስለሆነ ነው የምነግርህ" አለና ቀና ብሎ ተመለከተው::

"ስትደውልለት ምን ብሎ መለሰልህ?" ወዳጅህ የነበረው ሰው::

"እንደማይተባበረኝና በራሴ መንገድ እራሴን ለማውጣት መጣር እንደሚገባኝ ገልፆ ስልኩን ዘጋብኝ::"

አረቡ የተናገረው እውነቱን ነበር:: ስልኩን ስለ ጠለፈው ሁለቱ የተመላለሱትን ቀድቶ ይዞታል::

"በቋሚነት የሚሠራበትን መሥሪያ ቤት ለይተህ ታውቃለህ?" አትኩሮ ተመለከተው::

"የፕሮቴስታንት የወንጌል ሰባኪ ነኝ ይላል። ራሱ ከነገረኝ በቀር እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም።"

"በእሱ በኩል መጥተው የምታውቃቸው ካሉ ብትነግረኝ።"

"ሁለት ሰዎች አውቃለሁ። ያም ሆኖ ከአስተዋወቀን ብዙ ጊዜ በመሆኑ ስማቸው ተዘንግቶኛል።"

"በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኩል የምታውቃቸውና ከእናንተ ጋር የነበሩ ግለሰቦችን ታውቃለህ?"

እራሱን በአወንታ አወዛወዘና "ሁለት ሰዎች አውቃለሁ።" ሲል በአጭሩ መለሰለት አብዱልአዚዝ።

"በቅርብ ትገናኛላችሁ?" ሲል ጠየቀው።

"አልፎ አልፎ እንገናኛለን ሲል መለሰለት።"

"በቤተ ክርስቲያን በኩል ያላቸው የሥራ ድርሻቸው ምንድን ነበር።"

"የኦርቶዶክስን ሕግና ሥርዓት ስለማላውቅ ጠይቄያቸው እነሱም ነግረውኝ አያውቁም።"

በሃይማኖት ሽፋን እየተሠራ ያለውን ደባ ሲያስብ ውስጡን እንደ እሳት የሚቃጥል ብስጭት እረፍት ሲነሳው ታወቀው። ለሁለት ሰዓታት ያህል ጠይቆት ያረካውን መልስ አግኝቷል።

በመጨረሻ ላይ ያቀረበለት ጥያቄ የራሱን ማንነት የሚፈታተን ቢሆንም እውነቱን አፍረጥርጦ ለመናገር ተገደደ።

"ወደ ኢትዮጵያ የመጣኸው ለስለላ ተግባር ነበር። ይህስ እውነት አይደለም?"

"እንዳልከው ወደ ኢትዮጵያ የገባሁት ለመረጃ ሥራ ነበር" አለ አረቡ።

"ሌብነቱ አመዘነብህና ወደ ዝርፊያ ገባህ።"

"መዝረፍ ፈልጌ ሳይሆን በግዳጅ ነው የተመለመልኩት።"

"ማነው የመለመለህ።"

"የጠረፋ ንጉሥ ተብሎ ይጠራል።"

"እሱን ወደ ኋላ እናነሳዋለን። በምን ምክንያት ነው የምትሰልለን።

"ግብጽ ያለ አባይ መኖር እንደማትችል ኢትዮጵያ የምታውቀው እና የተረዳችው አትመስልም። ይህ ጥያቄ አዲስ ሳይሆን እንደ ሰንሰለት ተያይዞ የመጣ ነው። የግብጽ ሕልውና የአባይ ወንዝ እንደመሆኑ የአባይ ጉዳይ እራስ ምታት ሆኖ እንቅልፍ አይሰጣትም።"

"ኢትዮጵያ አባይን እንዳትገድብ ትሰጋላችሁ ማለት ነው?" እንደ መሳቅ ብሎ ተመለከተው ዘሩባቤል።

"ትክክል ነህ።" እሱም ፈገግ ለማለት ሞከረ። ንግግሩን ቀጠለ።

"እስከ መቼ የሚሠራ ይመስልሃል? እርስ በርስ የማበጣበጥ ዘዴ እንደ ዘላቂ የአንድ አገር መፍትሔ የፖለቲካ ሥራ ሲወሰድ ይችላል እንዴ? ከዚህ መልካም ጉርብትና አይሻልም።"





"የምትለው የመልካም ጉርብትና እንደ አባይ ለአለው ጉዳይ የሚሠራ አይደለም።"

"ግብጽ ከኢትዮጵያ ከሚፈሱ ወንዞች ጠብታ ውኃ የማታገኝበት ጊዜ እንደሚመጣ እነግርሃለሁ።"

"ቀደምት የኢትዮጵያ መሪዎችም ይህንን ለማድረግ ሞክረው አልተሳካላቸውም" ትንፋሹ እየተቆራረጠ ተናገረ አብዱልአዚዚ።"

"ወደ ሕገ ወጥ ሥራ የገባኸው ይህንን የመሰለ ኃላፊነት ትተህ በመሆኑ እንደ ክህደት አያስቆጥርብህም እንዴ?" ሲል በፌዝ ጠየቀው።

"እንደ ክህደት አልወሰደውም" አለ አብዱልአዚዝ።

"በችግር ላይ እያለህ ለምን ወደ ኤምባሲህ አልገባህም?" ሲል ጠየቀው።

"አሁን እኮ ኤምባሲዬ አያውቀኝም። ዜግነቴም ሆነ ፓስፖርቴ የሚያስረዳው ሳውዲያዊ መሆኔን ነው።"

"ወደ ሳውዲ ኤምባሲስ ለምን አልሞከርክም ታዲያ?"

"ያለኝ መረጃ የሐሰት ነው።"

"በአገርህ በነበርክ ወቅት በምን ሥራ ተሰማርተህ ነበር የቆየኸው።"

"ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ የተመደብኩት በውጭ የመረጃ ሥራ እንድሠራ ነበር። በቀጥታ የመጣሁት ወደ ኢትዮጵያ ነው።"

"የሽፋን ሥራህ ምን ነበር ኢትዮጵያ ውስጥ?።"

"በአዲስ አበባ በስተ ደቡብ ምስራቅ ወሎ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ሬስቶራንት ቤት አለኝ።"

መርማሪው እራሱን አነቃነቀ። ሬስቶራንቱን ከነውስጠ ሚሥጢሩ ያውቀዋል። እስከ አሁን በተነጋገሩበት ሁሉ የሰጠው መልስ በሙሉ እውነት ነው። ግብጻዊው ሰላይ እራሱን ማስቃየት አልፈለገም። እናም እውነቱን ይናዘዝ ጀምሯል። ሬስቶራንቱም የሃሺሽ መናኸሪያ ነው።

"ለስለላ ወደ ኢትዮጵያ የገባኸው መቼ ነበር?" ሲል ጥያቄውን አከለ።

"በዘጠና ሁለት መጨረሻ ላይ ነበር።"

"ብዙ ጊዜህ ነው።" አለው ዓመታቱን በአእምሮው እያሰላና በትኩረት እየተመለከተው።

በአወንታ እራሱን አወዛወዘና "ልክ ነህ ብዙ ዓመታትን አሳልፌአለሁ" ሲል ሩቅ እያሰበ መለሰለት።

በነዚህ ዓመታት የማይረሱ ብዙ ትዝታዎችን አሳልፏል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ነገር ባለቤት እንደሌለው አዝመራ ከልካይ የለውም። ፍላጐትን የሚገድብ ወሰን የለም። ሁሉንም መዝረፍ ይቻላል።

"ችግር እንደተከሰተ ኤምባሲህን አላማከርክም?" ይህንን ጥያቄ የደገመለት ያለ ምክንያት አልነበረም። ቀደም ሲል በጠየቀው የተሟላ መልስ እንዳልሰጠው ያምናል። ለስለላ እስከ መጣ ድረስ ኤምባሲው የማያውቀው ምሥጢር የለም።

"አልችልም" አለና መለሰለት ግብጻዊው ሰላይ።

"ለምን አትችልም።" ትኩር ብሎ እየተመለከተ ጠየቀው።

"መንግሥት የላከኝ የመረጃ ሥራ እንድሠራ እንጂ አልባሌ ነገር ላይ ተሰማርቼ የተጣለብኝን ኃላፊነት እንድዘነጋ አልነበረም" ይህንንም ቀደም ሲል ገልጨልሃለሁ።

"መንግሥትህ ቢያውቅ ኖሮ እርምጃ ይወስድብህ ነበር ማለት ነው?" ፊቱን አትኩሮ እየተመለከተ ጠየቀው መርማሪው።

"ከባድ የሆነ ክህደት ነው የፈጸምኩት።"

"ቀደም ባለው ውይይታችን ሕገ ወጥ ሥራህ ኢትዮጵያን ስለሚጎዳት ለግብጽ ጥቅም ይሰጣታል ብለኸኝ ነበር" አለው መርማሪው።

"ያ የግሌ አስተሳሰብ ነው። መንግሥቴ አላዘዘኝም" አለው።

"በሕገ ወጥ ተግባሩ ላይ ተሳታፊ የሆንከው መቼ ጀምረህ ነው?" ያልጠበቀው ጥያቄ ስለ ነበር ግራ የተጋባ መሰለ።

"በሁለት ሺህ መጀመሪያ ላይ በፈረንጆቹ አቆጣጠር።

"ከስድስት ዓመት በፊት መሆኑ ነው?" በሚሰረስር አስተያየት አስተዋለው።

ትንሽ ሲያስብ ቆየና ቀና ብሎ እየተመለከተው "እውነተኛውን ማንነቴን ይፋ አድርጋችሁ በመገናኛ ብዙኃን ታወጡታላችሁ ማለት ነው?" ሲል ጠየቀው።

"ወደ ፊት መንግሥት የሚወስነው እንጂ እንደፈለግሁ ብይን የምሰጥበት ተራ ነገር አይደለም። የኔ ድርሻ ከሰጠኸኝ ቃል ጋር አስተሳልፌ ለበላይ አካላት መስጠት ነው።"

"ምን ቅጣት ይጠብቀኛል ብለህ ታስባለህ?" አለና ፊቱን በግማሽ እየተመለከተ ጠየቀው አብዱልአዚዝ።

"እሱም እኔ ከምገምተው በላይ ይመስለኛል" አለ ዘሩባቤል።

"እንደማልገደል ተስፋ ይኖረኛል ብለህ ታስባለህ" በፍርሃት ዓይነት አስተዋለው።

"በቂ መልስ ልሰጥህ አልችልም። የሌላ አገር ዜጋ ወንጀል ሲሰራ ቢገኝ የሚሰጠው ፍርድ እንደ ወንጀሉ ዓይነት ይለያያል" ትኩር ብሎ ተመለከተው።

"በአገር ላይ አደጋ ሲያደርሱ አለዚያም ሲሰልሉ በተገኙ ግለሰቦች ላይ የተጣለ የቅጣት ዝርዝር አልተቀመጠም እንዴ?

"ቢቀመጥም ምን እንደ ሆነ ልነግርህ አልችልም። ወንጀልህ ከባድ ጥፋተኝነትን የሚያሰጥ ስለሆነ ዓለም አቀፍ ሕግ አለው። የሚጠብቅህን ቅጣት እራስህ መገመት ይኖርብሃል።"

ማስታወሻውን አጠፈና ወደ ጎን ከሰበሰበ በኋላ አረቡን ትኩር ብሎ እየተመለከተው "ለዛሬው የሰጠኸኝ ቃል ይበቃል። ወደ ማረፊያ ቤት ተመልሰህ ቀሪውን ሌላ ጊዜ እናወራለን" አለው ቀለል አድርጎ።





# ምእራፍ ሀያ ሁለት

ሸማግሌው ፕሮፌሰር በላይኛው ግራውንድ ስላሉት እናቶች ሁኔታ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይጠብቃሉ። የልፋታቸው ውጤት በዚያ ክፍል ውስጥ ባሉት እናቶች ማኅፀን የተፀነሰው አዲሱ የሰው ዘር ነው። ልዩ ክትትልና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ባሉት እናቶች ማኅፀን ውስጥ ያለው አዲሱ ሰው ወደዚች ዓለም የመምጫው ጊዜ እየቀረበ ነው።

አርባ ሁለት እናቶች ሴሉ ወደ ማኅፀናቸው ከገባ ሁለተኛ ወሩን በማገባደድ ላይ ይገኛል። ከአጠገባቸው ያሉት ባለ ሙያዎች በየሰዓቱ ስለ ጽንሱ ሁኔታ ክትትል ያደርጋሉ። የመጨረሻው ፍጻሜ እየተቃረበ መምጣቱን የተረዱ የሚመስሉት ሽማግሌው ፕሮፌሰር ውስጣቸው በተለያየ ስሜት መታወክ ጀምሯል። ዕለት በለት ስለ ሁሉም ነገር ማብራሪያ ይጠይቃሉ። ነገሩ እንደ በፊቱ የቀለላቸው አይመስልም። ማንኛውም ነገር ወደ ፍጻሜው በሚቃረብበት ወቅት ያስጨንቃል። ጦርነትም እንዲሁ መዳረሻው ያስጨንቃል። ሰላምም ሲቃረብ ይረብሻል። ሁሉም ነገር በቀረበ መጠን ስሜት መፍጠሩ የማይቀር ነው።

ምርምሩ ምን እንደሚያስከትል የሚታወቅ ነገር የለም። በጣም አስፈሪ ክስተት ሊያስከትል ይችል ይሆናል። ይህንን የሚያውቀው በጥልቁ ውስጥ ያለው ዲያብሎስ ብቻ ነው። እግዜአብሔር በዚህ ጉዳይ እጁን አያስገባም። ይህ ምርምር በራሱ ፈጣሪ ያልተጠራበትና ያልተሳተፈበት እንደ ሆነ ያውቃሉ። ለሁሉም ፍጻሜው ደርሷል። ምጽአተ ፍጻሜ። ዓለምና የዓለም ሕዝቦች ይዘትና ቅርጻቸውን የሚቀይሩበት ዘመን አሮጌው ትውልድና ዓለም በአዲሱ ፍጡር ሊተካ የቀረው መጠነኛ ጊዜ ነው። የእውቀታችን መገለጫ ውጤታችን ይህ ብቻ ነው። እንደ ወንጀለኛ ከሀገር ወደ አህጉር ተሰድደንበታል። እንደ ወንጀለኛ ማደኛ የወጣብንም በዚሁ ነው። የሌላ ሀገር ሀብትና ንብረት የዘረፍነውም ለዚሁ ተግባር እንጂ መዝረፍ አሰኝቶን አለዚያም ተቸግረን ልንበላው አልነበረም። ምጽአተ ፍጻሜው ነው የሚረብሸው። እየቆየ የማይለመድ ነገር የለምና ሞትም በራሱ ይለመዳል።

"እናቶቹ በምን ደረጃ ላይ ናቸው? ፅንሱስ እንዴት ነው?" አንገታቸውን ከግራ ወደ ቀኝ እያመላለሱ ሁሉንም ተመለከቱ ፕሮፌሰሩ።

"እስከ አሁን ድረስ ያለው ጤንነታቸው ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ ቢሆንም እናቶቹ የመረበሽ ስሜት ይታይባቸዋል። ጫጩቶቹ በእናቶቹ ማኅፀን ውስጥ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከመደበኛው የሰው ልጅ የጽንስ እንቅስቃሴ የተለየ ነው። የፅንሱ እንቅስቃሴ በመለየቱ የተረበሹ መሆናቸውን እየገለጹልን ናቸው።" ኢትዮጵያዊው ሳይንቲስት ፈጋ ብሎ ለማብራራትና ለማስረዳት ሞከረ።

"አልገባኝም" አሉ ኘሮፌሰሩ። "ስለምን ጫጩት ነው ልትነግረኝ የፈለግኸው?" አትኩረው ለማየት መነጽራቸውን አስተካከሉ።

"ይቅርታ ኘሮፌሰር። ፅንሱ ከመደበኛው የሰው ልጆች የመፀነስ ተግባር የተለየ ሆኖ ነው የቀጠለው።"

"እኮ እንዴት?" ኘሮፌሰሩ ግራ በመጋባት ሁሉንም ተመለከቱ።

ቻይናዊው ተመራማሪ እጁን ብቅ አድርጐ የተዘጉ የሚመስሉ ዓይኖቹን በእንቁራሪት ዓይነት አርገበገባቸውና መናገሩን ቀጠለ።

"ጓደኞችን እንደ ገለጸው የፅንሱ አፈጣጠር ከተለመደው የሰው የፅንስ አፈጣጠር የተለየ ሆኖ ነው የቀጠለው። ፅንሱ ሁለተኛ ወሩ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በጣም ፈጥኖ ይንቀሳቀሳል። በዚህ ከቀጠለም በሦስተኛ ወሩ ላይ ይወለዳል ማለት ነው። በሌላ በኩልም እያንዳንዶቹ እናቶች በማኅፀናቸው የያዙት ፅንስ እስከ ስድስት ሊደርስ የሚችል ጫጩት ነው። ለዚህም ይመስለኛል ጓደኛዬ ጫጩት ብሎ ለመግለጽ የሞከረው። ይህ ብቻ አይደለም። ፅንሱን በሲኖግራፊ እንደተመለከትነው ክንፍ ያለው በመሆኑ ከሰው የተለየ ፍጡር ሆኖ ነው እያደገ ያለው።"

"ጥሩ" ሳቅ አሉ ኘሮፌሰሩ "ለማንኛውም በምትገልጹበት ወቅት ጫጩት የሚለውን ሕፃን በሚለው ተክታችሁ ተጠቀሙ። ጫጩት ለዶሮ እንጂ ለሰው የሚሰጥ መጠሪያ ሊሆን አይችልም።" ሁሉንም እየተዟዟሩ ሲመለከቱ ትንሿ የስብሰባ አዳራሽ በሳቅ ተናጠች።

"በተፈለገው መልኩ ብንጠራውም ለውጥ እስካላመጣ ድረስ ምንም ችግር አይፈጥርም። ችግሩ የእናቶቹ መረበሽ ብቻ ነው። ከላይ ወንድሜ ለመግለጽ እንደ ሞከረው የፅንሱ እንቅስቃሴ በጣም የፈጠነና ከሰው የፅንስ እንቅስቃሴ የተለየ በመሆኑ እናቶቹ ከአእምሮ ቀውስ ውስጥ እንዳይገቡ ስጋት አለኝ" አለ እስራኤላዊው ተመራማሪ።

ኘሮፌሰሩ እያንዳንዳቸው የሚሰጡትን መግለጫ አጕንብሰው ከማስታወሻቸው ላይ እያሰፈሩ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ቀና ብለው ወደ ሁሉም ይመለከታሉ ።

"የምርመራ ውጤቱ የሚያሳየው በአርቢዎቹም እናቶች ማኅፀን ውስጥ ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ፅንስ መኖሩን ነው ያም ማለት ሁለት መቶ ሃምሳ ሕፃን በአንድ ጊዜ ሊወለድ ይችላል ማለት ነው። በርግጥ የዚህ ዓይነት አረባብ አራት የምንፈልገውን ያህል ቁጥር ለማግኘት ጠቃሚ ቢሆንም እናቶቹ ሁሉንም አጥብተው ለማሳደግ እንዳይቸገሩ..." አሜሪካዊው ተመራመሪ የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር አንጠልጥሎ ተወው።

"ይህንን እንደ ትልቅ ችግር በመውሰድ መረበሽ ተገቢ አይመስለኝም። ዛሬን አያድርገውና።" ወደ ቻይናዊው እየተመለከተ ሳቅ አለ "ዛሬን አያድርገውና ጥንታዊያን ቻይናዊ እናቶች ተመሳሳይ ሕፃናትን ወልደው አሳድገዋል።" በፈረንሳዊው አባባል ሁሉም ሳቁ።





"ዕንሶቹ እንደ መደበኛው የመውለጃ ወቅት ዘጠነኛውን ወር ጠብቀው የሚወለዱ አይደሉም። በሦስተኛው ወር ላይ ወደዚህ ምድር የሚደባለቁበት ጊዜ መሆኑን አምነናል። እንደኔ እምነት ቅድመ ዝግጅት መደረግ አለበት። ሕፃናቱን የሚንከባከቡ ሞግዚቶች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም አንድ እናት ስድስት ሕፃናትን በአንድ ጊዜ መንከባከብ ይከብዳታል" ኮሪያዊው ተመራማሪ ተናግሮ ሲጨርስ እጆቹን እርስ በርስ አፋተገ።

"ከተወለዱ በኂላ ስለሚደረገው የመንከባከብ ሥራ አሁን ላይ ብዙ የሚያስጨንቅ መስሎ አልታየኝም። በቅድሚያ መታሰብ ያለበትና መፍትሔ የሚያስፈልገው እናቶቹ ምን ዓይነት ሕፃናትን እንደሚወልዱ ቀድመው እንዲገነዘቡ የማድረጉ ጉዳይ ይመስለኛል። ስለተፀነሱት ልጆቻቸው ከመውለዳቸው በፊት ካልተረዱ በወለዱ ጊዜ በድንጋጤ እስከ መሞት የሚደርስ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። እንደኔ እምነት በፀነሷቸው ሕፃናት ዙሪያ ሰፋ ያለ የቅድሚያ ሥነ ልቡና ትምህርት ቢሰጣቸው የተሻለ ነው" ጣሊያናዊው በሰጠው ገለጻ ሁሉም የተስማሙ መሰሉ።

"እናት የወለደችውን ሕፃን ትጠላለች ብሎ ለማመን የሚከብድ ቢሆንም የተለየ ፍጡር ሲመጣባቸው መደናገጣቸው የማይቀር ነው። ስለሆነም ስለሚወልዱት ሕፃን የተለየ ባህርይም ሆነ ስለ ብዛታቸው ለእናቶቹ ቅድሚያ የሥነ ልቦና ግንባታ ትምህርት ይሰጣቸው" እራሻዊው ሳይንቲስት ተናግሮ ሲጨርስ የሁሉንም ፊት ተመለከተ።

ሽማግሌው ኘሮፌሰር ሁሉም የተናገሩትን ከማስታወሻቸው ላይ ሲያሰፍሩ ቆይተው ቀና አሉ። የተማራማሪዎቹ መንፈስ ከእሳቸው ላይ መሆኑን ሲመለከቱም መነጽራቸውን ከጠረጴዛው ላይ በጥንቃቄ አስቀምጠው ፊታቸውን በሁለት እጆቻቸው መዳፍ አሻሹና መነጽራቸውን መልሰው ከአደረጉ በኋላ ንግግራቸውን ጀመሩ።

"የሁላችሁንም አሳብ አድምጫለሁ።ያነሳችሁት በሙሉ ጥሩ አሳብ ነው። የእናቶቹን ሥነ ልቡና በተመለከተ ቅድሚያ ልንዘጋጅበት የሚገባ ተግባር በመሆኑ በጥንቃቄ መሥራት ይኖርብናል። ምን ዓይነት ልጅ እንደሚወልዱ እናቶቹ ይነገራቸውና ከአሁኑ እየተለማመድት እንዲመጡ ይደረጋል። ይህ ወሳኝ ሁኔታ ነው። የሕፃኖቹን እንክብካቤ በተመለከተም በቂ የማቆያ ስፍራ ስለ አለን የምንቸገር አይመስለኝም። የሞግዚትነቱንም ሥራ ሁላችንም የመሥራት ኃላፊነት አለብን። ሕፃኖቹ እንደተለመደው የሰው ልጅ ዕድገት አዝጋሚ ባለ መሆኑ የሞግዚትነት ሥራችን ብዙ ወራቶችን የሚጠይቅ አይሆንም። በአንድና በሁለት ወራት ራሳቸውን ችለው የሚፈልጉትን ነገር መጠቀም ይችላሉ።

"ቀጥሎ ያለው ሁኔታ ወደ ፊት የሚታይ ቢሆንም አሁን ላይም ማንሳት ያለብኝ ይመስለኛል። እሱም ምንድነው? ሕፃናቱን ወደ ምድር እንዲደባለቁ የሚደረግበት የጊዜ ገደብ በምንና እንዴት መሆን

ይኖርበታል የሚለው ነው። እነዚህ ሕፃናት ወደ ሰው መቀላቀላቸው የማይቀር ነው። ሲቀላቀሉ እንደ ማንኛውም እንግዳ ሰው ዝም ብለው የሚደባለቁ አይሆኑም። በምድር ላይ እየኖረ ከአለው የሰው ዘር የሚለዩበት አካል ስላላቸው ህዝቡ ሊደናበርና ሊሸበር ይችላል። የተለዩ ፍጡራን መጡ የሚለው ዜና ለዓለም ሕዝብ ይዳረስና መንግሥታት ራስን የመከላከል እርምጃ ይወስዱባቸዋል። እነሱ ላይ የሚሰነዘርን ጥቃት መቋቋም እስከሚችሉ ድረስ በዚሁ እንዲቆዩ ማድረግ ዋናው መፍትሔ ነው። በሚቀጥሉት ሶስት ሳምንታት ውስጥ ወደዚች ዓለም የሚመጡበት ጊዜ እንደ ሆነ እየተናገራችሁ ነው ሁላችንም የምንናፍቀው የልፋታችን ውጤት መገለጫ ቢሆንም ሰው ነንና መረበሻችንም መደሰታችንም ብዙም እንዳያስገርመን። ነገር ሁሉ ፍጻሜው በተቃረበ መጠን የመረበሽ ኃይል አለው። አንድ ዓይነት ስሜት በሁላችንም ውስጥ ተፈጥሯል። እንደዚህ ያለው ከባድ ተግባር ይቅርና ትንሽ ድርጊትም ብትሆን ለተወሰኑ ጊዜያት የልብን ጓዳ በመነካካት ትንፋሽን ማዛባቷ የማይቀር ጉዳይ ነው።

"ኢንጂነር በአንተስ በኩል ምን እየተከናወነ ይገኛል? ወዳጆቻችን ምን እያደረጉ ናቸው?" መነጽራቸውን መልሰው ከዓይናቸው ላይ እያስተካከሉ ጠየቁት።

"የተለየ ነገር የለም" "ሁሉም ነገር በነበረበት መልኩ እንደቀጠለ ነው። ኢንተርፖል ኃይሉን ለማጠናከር አዳዲስ ረዳቶቹን ወደ ኢትዮጵያ አስገብቷል። ሞሳድና ሲአይኤን የመሳሰሉት የስለላ ድርጅቶችም የኢትዮጵያውን የደኅንነት መሥርያ ቤት ከፊት አስቀድመው በተለያየ አቅጣጫ የመረጃ ሥራውን እየገፉት ናቸው" አለ ኢንጂነሩ።

"አልገባኝም? ነገሩን ግልጽ ብታደርገው" እሱን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ገጽታ አስተዋሉ ኘሮፌሰሩ።

"የኢትዮጵያ የደኅንነት መሥሪያ ቤት የተለያዩ ስፍራዎችን በጥብቅ እንዲፈትሹ ግፊት እያደረገ ነው። ከኢንተርፖል ጋር ተጣምሯል።"

"የኢትዮጵያ መንግሥት ስለ እኛ አዉቋል እያልከኝ ነው?" አሉ ኘሮፌሰሩ።

"የውጭ ሰላዩቹ ለኢትዮጵያ መንግሥት እየነገሩት ያሉት የተሰወሩት ዜጎቻቸው በአንድ ሕንፃ የምድር ውስጥ ግራዉንድ ታግተው እንደሚገኙ ነው።"

"ግራ የገባኝ ነገር አለ። ለምንድነው? ለኢትዮጵያ መንግሥት ሚሥጢሩን ሊደብቁት የፈለጉት?" ኘሮፌሰሩ ግራ ተጋብተው ኢንጂነሩን ጠየቁት።

"እንደዚህ ያለውን ከባድ ምሥጢር ለማንም አሳልፈው አይሰጡም። ለምሳሌ የእስራኤል ሁለቱ የስለላ ድርጅቶች አንደኛው ለሌላው ምሥጢር አይነግረውም። ሲአይኤም እንደዚሁ ለኤፍ ቢ አይ





አይገልጥለትም። በጥምር እየሠሩም እንኳን ስለ ጉዳዩ በግልጽ አይነጋገሩም። በጉዳዩ ዙሪያ እየተነጋገረ የሚሠራው ኢንተርፖል ብቻ ነው።"

"ኢትዮጵያ መንግሥት በግሉ ስለ እኛ የሚያውቀው ይኖራል?" ኘሮፌሰሩ ጠየቁት።

"የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያውቀው ስለ ማፍያው ቡድን ብቻ ነው።" ኢንጂነሩ በእርግጠኛነት መለሰላቸው።

"ለሁሉም የሰይጣን ጆሮው ይከፈት" አሉ እንደ መተከዝ ብለው ሁሉንም በየተራ እየተመለከቱ።

" አልገባኝም " አለ ኢንጂነሩ ግራ በመጋባት እየተመለከታቸው።

ኘሮፌሰሩ እራሳቸውን በአወንታ እነቃነቁ "ይህ እንደሚሆን የኔም ግምት ነበር። በሕንፃው ላይ ያሉት ሰዎቻችንስ እንቅስቃሴ እንዴት እየሆነ ነው?" በትኩረት ተመለከቱት።

ኢንጂነሩ አሳብ የገባው መሰለ። "የነሱ ጉዳይ ወደ መጠናቀቂያው የተቃረበ ይመስለኛል።"

"አልገባኝም?" በጥያቄ ተመለከቱት።

"ኢንተርፖሎች ደርሰውባቸዋል። በኢትዮጵያ የጸጥታ ሠራተኞች በኩል እየተጠጓቸው ናቸው።"

"የሰነዶቹስ ጉዳይ?" ኘሮፌሰሩ ሁሉንም በጥያቄ መልክ ተዟዙረው ተመለከቱ።

"ሰነዶቹ ቦታ ይዘዋል። በኮምፒውተሮቹ ላይ ያሉትን ዳታዎች ዲሊት ተደርገው ፋይሎቹ ወደኔ ቢሮ መጥተዋል" አለና በረጅሙ ተነፈሰ ኢንጂነሩ።"

ኘሮፌሰሩ በብዙ ቢሊዩን ብር የተጨናነቀውን ሰነድ ዓይናቸውን ከድነው አሰቡ። የሁሉም ነገር ሴል ያለው በዚህ ሰነድ ውስጥ ነው። ተዝቆ የማያልቅ ሀብት በነዚህ የኮምፒውተር ዳታዎች ውስጥ ይገኛል። ከአጠገባቸው ያለው የሳተላይት ባለ ሙያው የነዚያ ሰነዶች አድራጊን ፈጣሪ መሆኑን ሲረዱም ውስጣቸው እፎይታ ተሰማው። በተቀላጠፈ ሳይንሳዊ ሙያው ዳታዎቹን ወደ ራሱ ኮምፒውተሮች እንዳመጣቸው ያምናሉ። ሥራውን እንዳጠናቀቀም በኢንተርኔት አማካኝነት ዴሊት አድርጓቸዋል። በዚያ ሕንፃ ውስጥ ያሉት ባለ ሙያዎች ይህ ስለመደረጉ የሚጠቁም ፍንጭም ሆነ ችሎታው የላቸውም። እነሱ የሚያውቁት ፋይሉ በአጠቃላይ በድንገት ዴሊት ስለመሆኑ ብቻ ነው። ለዚህም ቫይረስን እንደ ምክንያት ወስደው ይሆናል። ካሉበት ሕንፃ በረጅም እርቀት ጥልቀት ውስጥ ስለሚከናወነው ማንኛውም ምሥጢራዊ ሥራ የሚያውቁት ወይም ደግሞ የተነገራቸው ምንም ነገር የለም።

የነሱ ተግባር ከማን እንደሚመጣ በማያውቁት ትእዛዝ የተለያዩ ዘረፋዎችን በማድረግ የተገኘውን ሀብት ወደ ጥሬ ገንዘብ ለውጠው

በማያውቁት ሰው የባንክ አካውንት ገቢ እንዲሆን ማድረግ ብቻ ነው። ይህንን ያደርጋሉ እንጂ ማን እንደሚያዛቸውም ሆነ ለምን እንዳደረጉት በትክክል አይረዱትም። የሚጠይቃቸው ኃይል በሚመጣበት ወቅትም ቢሆን ይህ ነው ብለው ትክክለኛ መረጃ መስጠት አይችሉም። የሚዘረፉትን ሀብት አድራሻ ቢጠየቁ ከዚህ ስፍራ ይገኛል ብለው መልስ ለመስጠት ትክክለኛ መረጃ የላቸውም። ይህንን ለማወቅም አቅምና እውቀታቸው የሚፈቅድላቸው አይደሉም። የሚያውቁት አንድ ስም ብቻ አለ። ይህ ስም "የጠረፉ ንጉሥ" ተብሎ የተሰየመ ነው። ለተጠየቁት ወይም ለጠየቃቸው አካል መልሳቸው የጠረፉ ንጉሥ አዘዘን የሚል ይሆናል።

"መልካም" አሉ ፕሮፌሰሩ "መደረግ ያለበት ወቅትና ጊዜውን እየጠበቀ ተደርጓል። ፎቅ ላይ ከሚገኘው አካል ከአሁን በኋላ የምንፈልገው ጥቅም የለም። የሞተ ጉዳይ ነው። የሞተ ሰው የሚጠብቀው መቃብር ብቻ ነው። ድርጅቱም ስለ ሞተ ከአሁን በኋላ ሕይወት እንዳለው ነገር የመቀጠል እስትንፋስ የለውም። የሚጠበቅበትን ያህል አገልግሏል። ማብቃት በሚገባው ወቅት ነው ያበቃው።"

ፕሮፌሰሩ ተናግረው ሲጨርሱ እንደተለመደው ሁሉንም ተመለከቱ።

"ሃሳቤን ተቀብላችኋል ማለት ነው። እንደነገርኳችሁ የላይኛው ቡድን የአገልግሎት ምእራፍ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ይዘጋል ማለት ነው። ከአሁን በኋላ ከዚያ ቡድን የምንፈልገውም ሆነ የምንጠብቀው ምንም ነገር አይኖርም። ሁሉም ትኩረታችን የሚሆነው ባለንበት በዚህ ስፍራ በምናከናውነው ሥራችን ላይ ብቻ ይሆናል። ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ የሚመጡት የምንጠብቃቸው ፍጥረቶች ያልተለመዱ እንግዶች ናቸው። ለዚች መከራና ወንጀል ለበዛባት ዓለም መልስና መፍትሔ ያመጣሉ ብለን ያመንባቸው ፍጡራን መምጫቸው እየቀረበ ነው። ከመጡ የኛም ጊዜ እነሱን በመንከባከብ ላይ ይጠመድና ስለ ሌላ የምናደርገው ከንቱ አሳብ ይዘጋል። ዓለምን መግዛት የዘላለም ምኞትና ፍላጎታቸው የነበረው ኃይሎች ምኞታቸው የበጋ ጉም የመሆኛው ዘመን ሊፈጸም ተቃርቧል። የዓለም አምባ ገነኖች እነዚህን እንግዳ ፍጡራን የሚቋቋሙበት እውቀትና ጉልበት ያስፈልጋቸዋል። ይህ ደግሞ የማይታሰብ ጉዳይ ነው።"

ፕሮፌሰሩ በስሜት እየተወራጩ ተናግረው ሲጨርሱ የሲጋራ ፖኬታቸውን ፍለጋ ወደ ኪሳቸው እጃቸውን ሰደዱ።





# ምእራፍ ሀያ ሶስት

ከሦስተኛው ፎቅ ላይ የነበረው የምግብ አዳራሽ የመጀመሪያ ተግባሩን አቋርጦ ወደ ስብሰባ አዳራሽነት ከተለወጠ ዓመታትን አስቆጥሯል። ሦስት ሺህ ካሬ እስኩየር ሜትር ቦታ ላይ የተገነባው ማራኪ ሕንፃ ታሪካዊ ይዘት ያለው ሲሆን ሁለት የመሰብሰቢያ አዳራሾችና ከሰማንያ በላይ ክፍሎች አሉት። እነኚህ ክፍሎች የተለያዩ እንግዶችን እንደ መኝታነት እያገለገሉ በዚያውም እንደ ቢሮ ይጠቀሙባቸዋል።

ከመንገዱ ባሻገር ሆኖ ሕንፃውን አሻግሮ ተመለከተው። ግማሽ አካሉ በጨለማ ተውጧል።

ሙሉ ደርዘን የሚሆኑት የጸጥታ ሠራተኞች ሕንፃውን ከብበው ለመያዝ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። የመገናኛ ሬድዮኑ በአንድ ሰው ድምጽ ስለ ተያዘ ከቀበቶው አውጥቶ ተመለከተው። የታፈነ የሚመስለው ድምጽ እየተቆራረጠ በሬዲዮው ይሰማዋል። መስመሩን በአውራ ጣቱ ተጭኖ ከፈተው። ከዋናው የደኅንነት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ነበር የተደወለው። መነጋገሪውን ወደ ጆሮው አስጠግቶ "ቀጥል ይሰማኛል" አለውና መስመሩን ነጻ አደረገለት።

"ከፈለግሁህ ቆይቻለሁ። መስመሩ አልመለስ ብሎኝ ነው።" የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው እየተቻኮለ መናገር ጀመረ።

"ሌላ ስልክ እያነጋገርሁ ስለ ነበር ነው አይቸዋለሁ" አለ ዘሩባቤል።

"የጸጥታ ቢሮ ተጠሪው ሊያነጋግርህ ይፈልጋል። በራሱ ስልክ ላይ ደውልለት።"

"ለምን ፈለገኝ? በግዳጅ ላይ መሆኔን አያውቅም እንዴ?" የመረጃ አላፊው ጠየቀው።

"ያውቃል። የፈለገህ በዚሁ ዙሪያ ሊጠይቅህ ይመስለኛል። ደውልለትና አግኘው። የአንተን ስልክ ቀጥታ ማግኘት ስለ አልቻለ ነው ለኔ ደውሎ የነገረኝ። አሁኑኑ ደውልለት" አለው እየተጣደፈ።

"እደውልለታለሁ" አለውና በተለያዩ ሀሳቦች አእምሮው ሲወጠር በረጅሙ ተነፈሰ ዘሩባቤል።

"ወደ ሕንፃው ገብታችኋል እንዴ?" ሲል እግረ መንገዱን ጠየቀው።

"ሕንፃውን በቅርብ እርቀት እየጠበቅን ነው ያለነው" ሲል መለሰለት።

"በአካባቢው ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው? ሰዎች እንደ ልብ እየወጡ ይገባሉ?" አለ ጸጥታ ተቆጣጣሪው።

"አልፎ አልፎ ነው የሚዘዋወሩት። ብዙም ግርግር አይታይም። ሁሉም ነገር ጭር ማለት የጀመረው ስድስት ሰዓት ተኩል ላይ ነው። አብዛኛዎቹ ክፍሎችም መብራት አልባ ናቸው" ሲል መለሰለት ዘሩባቤል።

"ስልክህን ክፍት አድርገው። ልመጣ እያሰብሁ ነኝ። የኔ እርዳታ የሚያስፈልግህ ይመስለኛል" አለው።

"ልትመጣ በማሰብህ ተደስቻለሁ። ሰባት ሰዓት ሲሆን የሕንፃውን በር አስከፍተን ስለምንገባ ፈጠን ለማለት ሞክር" አለ ዘሩባቤል።

የመገናኛ መስመሩን እንደ ዘጋ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊውን ስልክ ቢሞክረው ተይዟል። ለብዙ ሰዓት እየደጋገመ ቢሞክረውም አልተለቀቀም። ከበላይ ባለ ሥልጣናት ጋር እየተነጋገረ ይሆናል ሲል አሰበና መደወሉን ተወው። የመገናኛ ሬዲዮኑ በድንገት መንጫጫት ስለ ጀመረ ከቀበቶው ላይ አላቀቀና መነጋገሪያውን ከፈተው። ከወዲኛው የመነጋገሪያ ጫፍ የመጣለት የሕህዝብ ግንኙነቱ ኃላፊ ድምጽ ነበር።

"ደረስክ እንዴ" አለው ያልተረጋጋ በሚመስል ድምጽ።

"ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን ያለውን መብራት ተሻግሬያለሁ።"

"ወደ ውስጥ እየገባሁ ነኝ። ዝግጁ እንዲሆኑ ለረዳቶቼ ትእዛዝ ሰጥቻለሁ።"

"ትንሽ ደቂቃ ጠብቀኝ። ምናልባትም ከኔ ጋር መሆን ሳይሻልህ አይቀርም።"

"ብቻህን ነህ..." አለው የመረጃ መኮንኑ።

"አይደለሁም። ሦስት የጸጥታ ሠራተኞች አብረውኝ አሉ።" "እጠብቅሃለሁ።"

ሰውነቱን እንደ ቀጭኔ መዝዞ ከመኪናው ወረዳና አስፋልቱን በፍጥነት እየተራመደ ተሻግሮ በሕንፃው በር ላይ ደረሰ። የደንብ ልብስ የለበሰ ጥቁርና ረጅም አፍሪካዊ ተክለ ሰውነት ያለው የጥበቃ ሠራተኛ የመግቢያውን በር ለቀቀለትና ጎንዮሽ ተመለከተው። የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ግቢውን አቋርጦ ያመራው ወደ ሕንፃው የውጭ ደረጃ መወጣጫ ነበር። ከሁለተኛ ፎቅ ላይ የደረጃውን ብረት ተደግፎ እንደ ቆመ አገኘው ዘሩባቤልን።

"በመምጣትህ ደስ ብሎኛል።"

"ወደ ውስጥ መግባት እንደሌለብህ አዘውሃል" አለው የሕዝብ ግንኙነት ተቆጣጣሪው።

"ምን እያልክ ነው" በቀዘቀዘ ስሜት ጠየቀው።

"ሕንፃውን መፈተሽ እንደማይኖርብህ አስጠንቅቀዋል።"

"እንደዚህ ያለው መመሪያ ምን ማለት ነው?" አለ ዘሩባቤል።

በመቋድሾ ከተማ በስተደቡብ የተወለደና የመጀመሪያ ድግሪውን በግብጽ አሌክሳንድሪያ የተከታተለ የተዋጣለት የፎርጅድ ዲዛይነር የሆነው ሰው በአራተኛ ፎቅ ላይ እንደሚገኝ ያውቃል። የአሜሪካን ዶላሮችን ሳይቀር ከዋናው የብር ኖት ጋር እያመሳሰለ በመሥራት ለጥቅም ያውላቸዋል። የይለፍ ካርዶችንና ፖስተሮችን ከዋናዎቹ ጋር እያመሳሰለ ይሠራል። እነዚህን ብቻ ሳይሆን ፎርጅድ የሜርኩሪ ውህዶችንም ከዋና





የሜርኩሪ ውህድ እያመሳሰለ የመቀመም ችሎታ ያለው ስለ መሆኑ ለመረጃ መኮንኑ ሙሉ ሪፖርት አለው። የኃብት ደረጃውን በተመለከተም ቀላል ተብሎ ግምት የማይሰጠው በመሆኑ ከፍተኛ የሀገሪቱን ባለ ሥልጣናት ወደ ፈለገበት አቅጣጫ ለመጠምዘዝና በራሱ ቻናል ለመቀየር ይችላል። የምርመራ ሹሙ ይህንን ሲያስብ ልቡን ሲቀዘቅዝ ተሰማው።

ወደ ውስጥ እዳይገባ ገደብ የተጣለበት ከዚህ ጋር በተገናኘ ሊሆን ይችላል። አደገኛው ሰው ከተያዘ ብዙ ምሥጢር መውጣቱ የማይቀር ነው። ስለዚህ የሚያመልጥበት መንገድ እስኪመቻች ድረስ ተከልክያለሁ ማለት ነው። የራሳቸውን የረከሰ ፍላጎት ከሀገራቸው የወደ ፊት ጥቅም በማስቀደም የዚህን ወንጀለኛ ምሽግ እየጠበቁለት ናቸው። እንደ ቆመ ሁሉንም ለማሰብ ሞከረ።

ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደኅንነቶችን ከአደጋ ላይ የጣለን ወንጀለኛ ለመያዝ የሚደረግን ክትትል በምክንያት እየጎተቱ ወደ ኂላ ማዘግየት ለምን ያስፈልጋል? የማምለጫ መንገዱን ለማመቻቸት ሲባል ታስቦ ከሆን ይህ በፍጹም የማይሆን ሙከራ ነው። ባይፈቅዱም ያደርገዋል። የሀገርን ደኅንነት ከአደጋ ላይ የሚጥል ወንጀለኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ የተሟላ መረጃ ይዞ እንዲያመልጥ ዕድሉን አይሰጠውም።

ቅድሚያ የሚሰጠው ወንጀለኛውን ለመያዝ መጣር ነው። ማመንታት ለኀሊና ጥያቄ መልስ መሆን አይችልም። ከጎኑ የቆመውን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ተመለከተው "ይህ ሰውም በዚህ ሕገ ወጥ ሥራ ላይ የጥቅሙ ተካፋይ ይሆን እንዴ? ሲል አሰበ።

ከሕገ ወጥ ንግዱ በስተጀርባ ለአገር ደኅንነት አደጋ የሆነ ሴራም ሊኖርበት ይችላል የሚል ግምት ነበረው። አደገኛ ወንጀል የሠሩና በኢንተርፓል መዝገብ ውስጥ በቀንደኛ ወንጀለኝነት የሚታደኑ ግለሰቦች አሉበት። በነፍስ ግድያና በአሽሽ ዝውውር ተከስሰው ከተለያዩ አገራት የመጡ በዓለም ዙሪያ ስማቸው በአደገኝነት የተጠቀሰ ግለሰቦች ስለ መኖራቸው በቂ መረጃ አለው። የሰውን አካል ጭምር ለመለዋወጫነት የሚጠቀሙ ምሁሮችም አሉ ነው የሚባለው። ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጐች እየተሰወሩ ያሉትም በዚሁ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

የቡድኑ አባላት በየሀገሮቻቸው መንግሥታት ማደኛ የወጣባቸው ናቸው። ከአውሮፓ እስከ ኤሺያ ከሩቅ ምሥራቅ እስከ አፍሪካና አሜሪካ በተዘረጋው የግንኙነት መስመራቸው በርካታ የግድያ እና የሕገ ወጥ ንግድን ያካሂዳሉ። ዋና ቢሯቸው የሚገኘው በኢትዮጵያ ዋና መዲና በአዲስ አበባ ከተማ በሁለት ስፍራ ሲሆን እንደ ማንኛውም የሚኒስቴር መሥርያ ቤት በሕግና በደንብ የሚመራ በሥራ ክፍፍል ተዋረድ የተዋቀረ ነው። የሲቪልና የጸጥታ ማስከበር ሥራ የፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጥ የተሰየመ ዳኝነት ሲኖረው ሁሉንም ያጣመረ የራሱ ፖሊሲና መዋቅር እንደ ማንኛውም

የመንግሥት መሥርያ ቤት ሕግ ወጥቶለትና በሥራ ተከፋፍሎ በደመወዝ የሚተዳደር ሠራተኛም አለው። ሠራተኛውም ያለ ምንም ቅሬታ መመሪያውን ተከትሎ ይሠራል። ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የተሰየመው ፍርድ ቤታቸው እስከ ሞት ቅጣት ይፈርዳል።

የመረጃ መኮንኑ ከፍተኛ ስህተት ውስጥ የገባ መሆኑን ሲገነዘብ እራሱን በቁጭት አነቃነቀና የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪውን በጨለማው ውስጥ በድጋሚ አስተዋለው። ትክሻውን ሰጥቶት እንደ ቆመ ነበር። ነገሩን ሲያስበው ከፍተኛ ውድቀት ላይ የደረሰ ያህል ሆኖ ተሰማው ዘሩባቤል።

"እንዳልገባ ትእዛዝ የተሰጠኝ ለምንድነው?" አለ በድጋሚ።

"በውል የማውቀው ነገር የለኝም። እንደምገምተው ከሆነ ሕንፃውን ለመፈተሽ የፍርድ ቤት ትእዛዝ መያዝ እንደሚያስፈልግ ስለተረዱ ይመስለኛል።"

"የሀገርን ደኅንነት ለመከላከል በሚወሰዱ እርምጃዎች ከመቼ ወዲህ ነው ከፍርድ ቤት ትእዛዝ ወጥቶ የሚያውቀው?" እየተገረመ ጠየቀው።

"ሕግና ሥርዓትን ለማክበር ይመስለኛል" የህዝብ ግንኙነት ተጠሪው እየዋሸው እንደ ሆነ እየገባው መጣ።

"የማፍያዎቹን ዋሻ ለመፈተሽ የፍርድ ቤት ትእዛዝ?" አለው የሞኝ ዓይነት ሳቅ እየሳቀ።

የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪው ምንም መልስ ሳይሰጠው ወደ መጣበት አቅጣጫ ፊቱን መልሶ ደረጃዎቹን መውረድ ጀመረ። በዚህን ጊዜ ለመረጃ መኮንኑ አንድ ነገር እየተገለጸለት መጣ። እራሱ ነው እየተከላከለው ያለው። የበላይ ባለ ሥልጣናት እጅ በክልከላው ዙሪያ የለበትም። እንቅፋቱ እራሱ ነው። ለምን? ጥያቄው ወደ ፊት የሚታይ ይሆናል። የሚቀድመው ይቀድማል። ማድረግ ያለበት ይህንን ብቻ ነው።

የመገናኛ ሬድዮኑን አወጣና ደወለ። የመለሰለት የደኅንነት ቢሮው ምክትል ሹም ነበር። ለበርካታ ደቂቃ ነበር ያነጋገረው። መነጋገሪያውን አጥፍቶ ፈገግ በማለት የሕዝብ ግንኙነቱ ወደ ወረደበት አቅጣጫ ተመለከተ። ደረጃዎቹን ጨርሶ ከሕንፃው የመጨረሻ ወለል ደርሶ ቆሞ ነበር። በጨለማው ውስጥ እንዳፈጠጠ የውሻ ልጅ አለ በልቡ። ጠብቅ አንተ የማትረባ ልክስክስ። የሀገርና የሕዝብን ጥቅም በግል ፍላጎትህ እየተደራደርክበት መሆኑ ገብቶኛል። ለዚህ ተግባርህ የሚበቃህን ያህል ዋጋ ይከፈልሃል።





# ምእራፍ ሀያ አራት

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው በራሱ የበታች ሠራተኛ መሣሪያ ሲደቀንበት ሳይገርመው አልቀረም። ይህ የማይታመን ቀልድ ነው አለው ለራሱ።

"ምን እየሠራህ ነህ? በመሣሪያ መቀለድ ጀመርክ እንዴ?" በመገረም ተመለከተው።

"ቀልጀ አላውቅም። እንደማልቀልድም ታውቃለህ" ሽጉጡን ወደ ግንባሩ ገፋ አድርጎ እያሳየው በእልህ አንክራፋ ምክትሉ።

"ምን እየሆንህ ነህ?" ጠየቀው የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪው።

"የምትመለከተውን እያደረግሁ ነኝ" ረጋ ብሎ መለሰለት።

"የምትቀልደውን አቁምና የምንነጋገረው ስላለ ነው የጠራሁህ።"

"የምንግባባ ይመስልሃል?" ቃላቶቹን በጥርሱ መካከል ያወጣቸው በግድ ታግሎ ነበር።

"ባይሆንም እንኳን ቅድሚያ መነጋገር አለብን። እያደረግህ ያለኸው በመጨረሻ ላይ ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ነው።" መደናገጡን አምኖ ተቀበለው።

"እራስክንና ጥቅምህን ስታስብ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ከአደጋ ውስጥ ጨምረሃል። ብዙ ሰዎችን ይዘህ ወደ መቃብር ከመውረድህ በፊት እገድልሃለሁ።"

"እንደዚያ ከማድረግህ በፊት የሰላም መንገድ ለመፍጠር እንሞክር።"

"የመደራደሪያ ጊዜህ አብቅቷል። የዘረጋኻቸው የተንኮል ድሮችህ እየተሰበሰቡ በመጠቅለል ላይ ስለሆኑ ከሰዓት በኋላ በቁጥጥር ስር ትውላለህ። ሁሉንም ነገር እንደምትናዘዝ አልጠራጠርም። እገድልህና የብዙ ሰዎችን ሕይወት አድናለሁ። እንደ ይሁዳ ክደህ ያስካድከን ስለ ሆንህ በቂ ቅጣትክን ማግኘት አለብህ። የሠራኸውን በሙሉ አረቡ ተናዝዞ ተናግሯል። ይህም አልበቃ ብሎህ የማፍያዎቹን መኖሪያ ላለማስፈተሽ በፈጠርከው ዘዴ ከበላይ የታዘዝህ አስመስለህ ዘሩባቤልን ተከላክለሃል። የምትፈጥራቸው ዘዴዎች በሙሉ እራስህን ተከላክለውልህ መፍትሔ የሚሰጡ ሳይሆኑ በወንጀል ላይ ወንጀልን እየደመሩ የሚረዝሙ ከንቱ ሙከራዎች ናቸው።"

የሽጉጡን መጠበቂያ በአውራጣቱ ተጭኖ ሲያስለቅቀው ሲመለከት አይኖቹ ወደ ዳር ፈጠው የሞት መልእክተኛ አስመሰሉት።

"ትንሽ ጊዜ ስጠኝና ላስብበት። ምንም አማራጭ ከጠፋ እራሴን በራሴ እገድላለሁ። እኔን መግደልህ የሚሰጥህ ጥቅም የለም።"

በግፍ ያስገደላቸውንና የገደላቸውን ሁሉ አሰባቸው። ሞትን ፊት ለፊት ማየት እንደዚህ ያስፈራ ኖሯል? እባካችሁ ለነፍሴ ምሕረትን ስጡልኝ። የሁሉም ነፍሶች በህሊናው ሲንጫጩ ተሰማው።

"ጸሎት እያደረግህ መሰለኝ? ከሆነ መልካም። ጊዜ ስለሌለኝ አጠር አድርገህ ጨርስ።"

"እባክህ ተረጋግተህ ለማሰብ ሞክር አሁን..." አላስጨረሰውም።

"ከአሁን በኋላ ስህተት አልሠራም እያልከኝ ነው? የምትሳሳትበት ጊዜ የለህም። ባዘገይህ የጸጥታ ኃይላት መጥተው ይወስዱሃል። መሞት ያለብህ አሁንና በእኔ እጅ መሆን አለበት።"

ሽጉጡን ወደ አፉ አስጠጋውና ተመለከተው ረዳቱ የነበረው ሰው።

"እኔን ገድለህ ወዴት ልትሔድ ነው" ከወንበሩ ላይ እየተንሸራተተ ጠየቀው።

"የራሴን መጨረሻ የምወስነው የአንተን አሟሟት ካየሁ በኋላ ነው" አለውና የእብድ ሳቅ ሳቀበት።

"እንደዚያ ከሆነ እኔም ሽጉጤን ላውጣና እርስ በርስ ተተኳኩሰን እንገዳደል" እጁን ወደ ጠረጴዛው ኪስ ሊዘረጋ ሲንጠራራ እንዲሰበሰብ አዘዘው።

"ደምህ ጎርፍ ሰርቶ ሲወርድ መመልከት እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ ግን ሞት ምን እንደ ሆነ ስትቀምሰው ላማየት ቸኩያለሁ።"

"ስትመጣ ባውቅ ኖሮ..." በቁጭት አልጎመጎመ።

"ብታውቅ ልትደበቅ ነበር" ከእርምጃው ወደ ኋላው ሲርቅ ሲመለከት በሁለት እጆቹ አይኖቹን ሸፈናቸው።

"እኔን ተመልከተኝ። እንደ ሞት ጭንቅን የሚገላግል መልካም የእረፍት ቦታ የለም። ዘላለማዊ እረፍት የሚገኝበት የእረፍት ስፍራ ስለሆነ ዓይንህን ገለጥና ሞትን እያየኸው ሙት። ስትንቦቀቦቅ ይንቅህና ትቶህ ሊሄድ ይችላል" የዲቢሉስ ሳቅ አሰማው።

የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ፊት ለፊት ለመመልከት ወኔና ድፍረት አልነበረውም። በለፈለፈበት ቁጥር የበለጠ እየፈራ ሰውነቱን ኃይለኛ ብርድ ገብቶ ያንቀጠቅጠው ጀመር። የመሣሪያ አፈ-ሙዝ እይ ብሎ ትእዛዝ ምን ማለት እንደ ሆነ ሊገባው አልቻለም። ምን መልካም ገጽታ አለው።

"ተኩስ..." አለው ፊቱን እንደ ሸፈነ።

"እያየኸኝ ካልሆነ አልተኩስም" በሽጉጡ አፈ-ሙዝ ግንባሩን ነካው።

ምን አይነት የእብድ አሳብ እያሰበ ነው? ሲል ራሱን ጠየቀ። ነገሩ ሁሉ ሕልም እየመሰለው ዓይኖቹን ሲገልጣቸው ሽጉጥ ከደቀነበት ራዳቱ አጠገብ የመረጃ መኮንኑ ዘሩባቤል አለምሰገድን ቆሞ ተመለከተው መጥፎ አጋጣሚ ነው።

"በጣም ብልህ ሰው ትመስለኝ ነበር" በጀርባው በኩል ዞሮ ከወንበሩ ላይ እየተቀመጠ ተናገረ ዘሩባቤል።

ሁሉም ነገር ሕልም ቢሆን ወደደ። ያም ሆኖ ሕልም አይደለም።





ኩቱናውን ከአምባር መዋቢያው ላይ ያጠለቀለት የራሱ የበታች ሠራተኛ ነው።

"በጣም ብልህ ሰው ትመስለኝ ነበር።" አለው ደገመና።

"በፍጹም ብልህ ሰው አይደለሁም" ሲል መለሰለት እራሱን እያወዛወዘ።

"ለምን ይመስልሃል ብልህነት የጎደለህ?" እረጋ ብሎ ጠየቀው ዘሩባቤል።

"አልጠግብ ባይነቴ ይመስለኛል። ሆዳም በሬ ሣሩን ሲያሳድድ ገደል ገብቶ መሞቱ የማይቀር ነው ይሉ ነበር አባቴ።"

"እየተጸጸትህ ያለኸው በሠራኸው ወንጀል ሳይሆን እራስክን ማዳን ባለመቻልህ ተሳስቻለሁ?" በጀርባው በኩል እየዞረ ጠየቀው።

"ትክክል ነህ። የተጸጸትኩት በአንተ እጅ በመውደቄ ነው። እራሴን ከአንተ ማዳን ነበረብኝ" አለው በብስጭት።

"የምንሠራቸው ብዙ ሥራዎች ስላሉ መኖርክን እንፈልገዋለን"።

የተናገረው ከምሩ እንደሆነ ተረድቶታል። ተዝቆ የማያልቅ ምሥጢሩን እንደ ያዘ ወደ መቃብሩ ቢወርድ ኖሮ የመረጃ መኮንኑ ይበሳጭ ነበር። ወደ ከፍተኛው የሥልጣን እርከን የሚያወጣው እርካብ ሆኖ እንደ ታየው አልተጠራጠረም።

"ወንጀለኛ መሆንክን ለራስህ አሳምነህ ተቀበል። ስሜትህ የማይታዘዝልህ ከሆነ ይጎዳሃል። በእኔና በአንተ መካከል ያለው ግንኙነት በወንጀለኛ እና በሕግ አስከባሪ መካከል የሚደረግ የመርማሪና የተመርማሪ ቀረቤታ መሆን ይኖርበታል።"

"ከአንተ እጅ ላይ ጣለኝ" አለው በድጋሚ።

"የምጠይቅህን በቀጥተኛ መንገድ መመለስ ይጠበቅብሃል። ማንኛውም ሰው የሚመለከትህ እንደ ማንኛውም አደገኛ ወንጀለኛ ነው። ለአንተ ሕይወት ምንም ዓይነት ርህራሄ አይኖረውም።"

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ረዳት ሽጉጡን ወደ ኪሱ መልሶ በአንደኛው ሶፋ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ።

"ምንድነው የምትፈልገው?" ከትከሻው ላይ የነበረውን ሸክም ወደ ፊቱ ለማዞር በሚጋብዝ የድምጽ ቃና የመረጃ መኮንኑን ጠየቀው።

"በጣም ብዙ የምፈልገው ምሥጢር አለኝ" አንገቱን በትከሻው በኩል አሳልፎ ፊቱን ለመመልከት ሲሞክር ሸክሙ የበለጠ ከበደውና ስሜቱ እየቀዘቀዘበት መጣ። ሆን ብሎ እንዳደረገው ገብቶታል።

"ከፊቴ ተቀምጠህ እንነጋገርም ታድያ?" የተጫነውን ክብደት ለመቀነስ ትከሻውን ወደ አንድ ፊት እያዘመመ ጠየቀው።

"እንድቀመጥ ሳይሆን እንድሮጥ የተፈጠርሁ ስለሆነ ብሮጥም እንኳን መሮጥ ይኖርብኛል" በጆሮው እያንሾካሾከ መለሰለት።

"እየተያየን እንነጋገር" በተሰላቸ ስሜት ነበር የተናገረው።

አጭበርባሪ መንፈሱ እንደ ገል ደቅቋል። ጥርሱን እየቀረጨ
በማይሰማ ቃል በጆሮው አንሾካሾከበት። ስሜቱ እየቀዘቀዘ መሆኑን ሲረ
የድምጽ መቅረጫዋን ከፈታትና ጥያቄና መልሱ ቀጠለ። እንደ በፊ
ጥድፊያ እንደማያስፈልገው ያውቃል።

"ግብጻዊውን ሰላይ በደንብ የምታውቀው መሰለኝ?" ከፊት ለፊቱ ዞር
ጠየቀው።

"ስለ የትኛው የግብጽ ሰላይ ነው የምትጠይቀኝ?።"

"ስለ አብዱልአዚዝ። ግንኙነታችሁ እንዴት እንደ ነበር አስረዳኝ?"

"እንደ ማንኛውም እንግዳ ወደ ቢሮዬ ይመጣ ነበር።"

"እንዳትሳሳት መጠንቀቅ ይኖርብሃል። እሱ የነገረኝ በዚህ መልክ
አይደለም። እውነቱን ንገረኝ።"

"ወንጀለኛ መሆኑን እስከምረዳ ወዳጅ ነበርን ከተረዳሁ በኋላ
አባርሬዋለሁ።"

"ወንጀለኛ መሆኑን ካወቅህ ይበቃል። ከአንተ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት
የመሠረታችሁት ከመቼ ጀምራችሁ ነው?" የመረጃ መኮንኑ ዓይኖች
ለሰኮንድ ሽርፍራፊ ከፊቱ ላይ ሳይነቀሉ ተመለከተው።

"ከአምስት ዓመት በፊት ይመስለኛል። አይደለም ከሰባት ዓመት በፊት
ነበር።" አለውና በረጅሙ ተነፈሰ።

"ከሱ ውጭ የነበሩ የቡድኑ አባላትን ትቀርባቸው ነበር ወይስ ሁሉም
ነገር ይመጣልህ የነበረው በሱ በኩል ነው?" የመረጃ መኮንኑ ሲጠይቅ ረዳቱ
የሚናገረውን ከማስታወሻው ላይ ያሰፍራል።

"የተወሰኑትን በግንባር አውቃቸው ነበር።"

"በነበረህ ኃላፊነት ምን ስትረዳቸው ቆየህ?"

"የተለያዩ የሕግ ድጋፎችን አደርግላቸውም ነበር።"

"ከአንተ ጋር በትብብር የሚሠራ ባለ ሥልጣን ነበር ወይስ አንተ ብቻ
ነህ?" ሙት ይዞ ይሞታል። ረዳቱ መጻፋን አቁሞ ቀና አለ።

"ይኖራሉ።" አለው ባጭሩ።

"ስማቸውን ትሰጠኛለህ" ጥያቄ ሳይሆን ትእዛዝ ሰጠው።

ስማቸውን መዝግቦ ሲጨርስ ራሱን አነቃነቀ። ብዙዎችን ይዟቸው ወደ
መቃብር እየወረደ ነበር። የማይረባ አሮጌ ፍየል ነው።

"እየደወልህ እንደምትፈልጋቸው ትነግራቸዋለህ" ቀጭን ትእዛዝ
ሰጠው።

"እንደዚያ የማደርግ አይመስለኝም"።

"ለምንድን ነው የማታደርገው?"

"ቤተሰቤ ላይ ጉዳት ይደርስባቸዋል?" ልቡ በፍጥነት መምታት
ጀመረች።

"ለቤተሰብህ ማሰብ የነበረብህ ወቅት አልፏል።"





"እንደዚያ ከሆነ እኔን ግደለኝ።"

"ከሞት የከፋ ጥፋት እቀጣሃለሁ።"

"ያንን እንደምታደርግ አውቃለሁ።"

የተገረመ በሚመስል መልኩ ተመለከተው።

"አልማዝና ወርቅ ይሰጡህ እንደ ነበር ሰምቻለሁ። እኩል ነበር
የምትካፈሉት።"

"አልነበረም" አለው።

አልማዝ? ምን ይመስላል? እስቲ በደንብ አስረዳኝ።"

"አልማዝ አይተህ አታውቅም ማለት ነው?" ሳቅ አለ።

"እውነተኛውን የአልማዝ መዓድን መሆኑን በምን እርግጠኛ መሆን
ይቻላል?"

"እርግጠኛ መሆን ይከብዳል። ከአሁን በፊት ያየሁት ዕቃ አይደለም።
እነሱ በነገሩን ብቻ ነው አምነን የተቀበልናቸው።"

"አልማዝ የራሱ የሆነ ኳሊቲ ስለ አለው ከሌላው ንጥረ ነገር ወይም
የከበረ ድንጋይ ለመለየት አይከብድህም" የሚል እምነት አለ።

"በርግጥ ሁላችንም አልማዝ ነው ብለን ራሳችንን በማሳመን
ተቀብለናል።"

"የአገራችሁን ጥቅምና የሕዝባችሁን አደራ በግል ፍላጐታችሁ መለወጥ
ነበረባችሁ።"

"ይህንን የተገነዘብኩት የተሰጠኝን አልማዝ በካዝና ቆልፌ ሳስቀምጠው
ነበር።"

"ለመጸጸቻ የሚሆንህ የቀረ ሽርፍራፊ ጊዜህ አሁን ነው።"

"አውቃለሁ።" በረጅሙ ተንፍሶ ተመለከተው።

"ጸጸትና የፍየል ጭራ አንድ ነው። በነገራችን ላይ የአልማዙ ምንጭስ
ከየት እንደ ሆነ የምታውቀው ነገር ይኖራል?" ሲል ጠየቀው።

"ከኢትዮጵያ ነዋ ሌላ ከየት ይመጣል?"

በዚህ መልሱ ሞኝ የሆነ መሰለው። አለዚያም ደግሞ ሞኝ ለመሆን
እየተለማመደ መሆን ይኖርበታል።

"ኢትዮጵያ የአልማዝ መዓድን አታመርትም እኮ" ሳቅ አለ። ዘሩባቤል።

"አልማዝ ላታመርት ትችላለች። የአልማዙ ባለቤት ግን የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ።"

"እንዴት?" አለው ከአንገቱ እየረዘመና እየተጠጋው። እንደ አሰበውና
እንደ ገመተው ሞኝ ለመሆን እየሞከረ አልነበረም። ሞኝ ለመሆንም
አላሰበም።

"ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው የተገኘው።" ሲል መለሰለት።

"በየትኛው ቤተ ክርስቲያን?" ጫልሱን ለመስማት ከምን ጊዜውም በላይ

ንጉቶ ነበር የተጠባበቀው። ተረት የሚመስለው ሁሉ እውነት እየሆነ ነው።

የቤተ ክርስቲያኑን ስም ነገረው። ቀደም ሲል የመረጃ ጭምጭምታ ቢኖረውም እውነት ነው ብሎ ሳይቀበለው ነበር የቆየው።

"በዚህ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተደብቆ የኖረ መሆኑ ይታመናል። አልማዙ ንግስተ ሳባ ከንጉሥ ሰለሞን በስጦታ የወሰደችው ነው የሚል ግምትም አለ። ያም ሆኖ አልማዙን በቤተ መቅደሱ የገዳሙ ሙዝየም እንዲቀመጥ ያደረጉት አቡነ ቴውፍሎስ ናቸው የሚል ወሬ አለ።" "ከአክሱም ወደ ሸዋ እንዴት ሊመጣ ቻለ? እስከዚያስ ድረስ የት ቆየ?"

"ስለሱ የማውቀው ነገር የለም።"

"ቀደም ሲል ከምእመናንና ከሊቀጳጳሱ ጋር ችግር ተፈጥሮ እንደ ነበር አውቃለሁ። ሊቀጳጳሱ ከስፍራው በተገኙበት ወቅት ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ የሰው ሕይወትም ጠፍቷል። ችግሩ ተከስቶ የነበረው ምክንያቱ ከዚህ ጋር ተያይዞ ይሆን እንዴ" ሲል ጠየቀው።

"በወቅቱ የተሰጠው ምክንያት የተምታታ ስለ ነበር ይህ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም።"

"ምን ነበር የተምታታው ምክንያት?" አለው።

"የተምታታው ምክንያት ቤተ-ሙዝየሙ ለኘሮቴስታንት ቤተ-መዘመሩ ተከራይቷል የሚል ወሬ ነበር።"

"ስለ ጉዳዩ ይህ መሥሪያ ቤት መረጃ ያለው ይመስለኛል። በወቅቱ በሕዝብና በእምነት አባቶቹ መካከል የነበረውን ችግር ይከታተል ነበር።"

"ሊቀጳጳሱ የምድር ውስጥ ገዳሙንና ቤተ ሙዚየም መጎብኘት አለብኝ ብለው ጥያቄ በማቅረባቸው አንዳንድ የቤተክርስቲያኗ የእምነት አባቶችና ምእመናኑ የጳጳሱን ጥያቄ ባለመቀበላቸው ችግር ተፈጥሮ ነበር። ለፕሮቴስታንት ሊያከራዩት ነው የሚል ወሬ ተናፍሶ ጳጳሱ ወደ ቤተ መቅደሱ ሲመጡ ችግር ተፈጥሮ የኛ መሥሪያ ቤት ውጥረቱን ለማብረድ ጣልቃ ገብቶ ምርመራውን እየተከታተልነው ቆይቷል።"

"በወቅቱ ጳጳሱ መጎብኘት የፈለጉበት ምክንያት ምን እንደ ነበር መሥርያ ቤታችሁ የጠቀሰው ወይም በትክክል የተረዳው ምሥጢር ነበር? ጉዳዩን ከሚከታተሉ ሰዎች አንዱ እንደ ነበርህ ገልጠህልኛል።"

"እርግጠኛ መሆን ባልችልም ጳጳሱ ቤተ መቅደሱንና የምድር ውስጥ ገዳሙን ለመጎብኘት የተነሱበት ዋናው አላማ የአቡኑ አጽም በዚሁ ሙዝያም ውስጥ መኖር አለመኖሩን አይተው ለማረጋገጥና የምድር ውስጥ ሙዝየሙን ለጎብኝዎች በሚመች መንገድ ክፍት ሆኖ የውጭ ቱሪስቶች እንዲመለከቱት ለማድረግ ነው የሚል መልስ ነበር የሰጡት። ሕዝብ ሊቀበለው ባለመቻሉ ችግር ተፈጥሯል።"

"የጳጳሱን አሳብ ሕዝቡ ያልተቀበለው ለኘሮቴስታንት እንዳያከራዩት ነው?"





"የማስፋፋት ሥራውን እንደ መግቢያ ሊጠቀሙበት አስበው እንጂ አላማቸው በአቡነ ትዮፍልዮስ ጊዜ ተቀብሮ የነበረውን ወርቅ አውጥተው ለመውሰድ የተጠቀሙበት ዘዴ ነው የሚል ነው። በዚህ መካከል በቤተ ክርስቲያኗና በጳጳሱ መካከል ነገሩ በመካረሩ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ የእኛ መሥርያ ቤትም ሁኔታውን ለማርገብ እጁን አስገብቶ ነበር።"

"የእናንተ መሥሪያ ቤት ነገሩን ለማጣራት ቀጠለ ወይስ በደፈናው ዝም ብሎ አለፈው?" አለ ዘሩባቤል።

"የመንግሥት እጅ ስለገባበት ነገሩ ወደ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ተቀይሮ ችግሩ እየተባባሰ ወደ ሙሉ ቀውስ ስለ ተቀየረ የእኛ መሥርያ ቤት ትኩረት ሰጥቶ ከ1991 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ሲከታተለው ቆይቶ ነበር። መጨረሻ ላይ ነገሩ እየከረረ መጥቶ ጳጳሱን በዚያ ያለው ሕዝብ ዓይናቸውን እንዳላይ በማለቱ መንግሥት ውጥረቱን በኃይል ለማስቆም ባደረገው ንቅናቄና በ1992ዓ.ም በተወሰደ እርምጃ የሰው ሕይወት ከመጥፋቱ በተጨማሪ የተለያዩ ድርጅቶች ግፊት አድርገው የቤተ ክርስቲያኑ ቀውስ ሙሉ በሙሉ ወደ ፖለቲካ ጥያቄ ተቀየረ። ሊቀ ጳጳሱም ከኢትዮጵያ የእምነት አባቶች ክብርና አምልኮ ውጭ በሆነ ስሜት ወደ ቤተ-መቅደሱ በፌዴራል ወታደር ታጅበው ለመግባት ተገድደውም ነበር። በዚህ ሁኔታ ቢገቡም ሕዝቡ በድንጋይ በመደባደቡ እርምጃ ወሰድን።

"እንደዚያ አምርሮ የታገለው አለ የተባለውን የወርቅ ክምችት ለመከላከል ነበር ማለት ነው? ግልጽ ሳድርግልህና በሙዚየሙ ወርቅና አልማዝ ስለ መኖሩ ሕዝቡ የሚያውቀው ነገር ነበር?" ሲል ጠየቀው የመረጃ መኮንኑ።

"አይመስለኝም። አብዛኛው ሕዝብ የተባለው ንብረት ስለመኖሩ አሁንም ድረስ አያውቅም። ይቃወም የነበረው ቤተ ክርስቲያኒቷን ሊቀ ጳጳሱ ለፕሮቴስታንት ቤተ-ሙዝየም ሊያከራዩት ነው ተብሎ ስለ ተነገረው ነው። ይህንን የመሰለው ቅስቀሳ በሰፊው ተሰራጭቶ በሕዝቡ እምነት አሳጥቷቸዋል።"

"አለ የተባለው የወርቅ ክምችት አልማዝ ነበር ማለት ነው?" ሲል ጠየቀው።

"ይመስለኛል። በዘረፋው ወቅት ከተገኙት ውድ ቅርሶች ዋናውና ከፍተኛውን ብልጫ የያዘው ዕቃ አልማዙ እንደ ነበር ይታመናል።"

"እንደምትለኝ ከሆነ ይህ አልማዝ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከእስራኤል የመጣ ነው። እስከ አቡነ ቴዎፍሎስ ማለት እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የት ነበር የተቀመጠው።"

"በዚህ በኩል መረጃው በግልጽ የሚጠቀመው ምንም ፍንጭ አልነበረም። መሥሪያ ቤታችንም ጥናት አላደረገም።"

"አልማዙ በእናንተ ቡድኖች እጅ መግባቱን ግን እርግጠኛ ነህ?" ሲል ጠየቀው ዘሩባቤል፡፡

አንገቱን በአወንታ አነቃነቀ "ትክክል ነህ፡፡" አልማዙም ሆነ ወርቁ በዘራፊዎቹ እጅ ነው ያለው፡፡"

"የወርቁን መጠንስ ታውቃለህ?" አትኩሮ ተመለከተው፡፡

"መጠኑን አላውቅም፡፡" አለው፡፡

"አልማዙስ በገንዘብ ደረጃ ቢተመን ስንት ያወጣ ይመስልሃል፡፡"

"ይህንን ያህል ይሆናል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡ ወርቁ ብቻ ብዙ ኪሎ ግራም እንደ ነበር መረጃው አለኝ፡፡ አልማዙን በተመለከተ ለኔና ከኔ ጋር ለነበሩት ከሰጡን ውጪ ምን ያህሉ እንደ ቀረ የማውቀው ነገር የለም፡፡" አለ የጸጥታ ተጠሪው፡፡

"ሊቀ ጳጳሱ ይፈልጉ የነበረው እነኝህን ነገሮች ሊሆን እንደሚችል በመግቢያችን ጠቁመኸኝ ነበር፡፡?"

"እርግጠኛ ሆኜ ለመናገር ይከብደኛል፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ጳጳሱን በተደጋጋሚ አነጋግሬያቸው የሰጡኝ መልስ ቤተ-መቅደሱ ታሪካዊ ይዘት ያለው ስለ ሆነ ለቱሪስት አመቺ ሆኖ እንዲታደስ ማሰባቸውን ነበር፡፡ ሕዝብ ሳይቀበለው በመቅረቱ ለጊዜው አሳባቸውን ማንሳታቸውን በመጨረሻው ውይይታችን ነግረውኛል፡፡"

"ታሪካዊ ቦታ ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ከሌሎቹ ቤተ-መቅደሶች ይለያል እንዴ? ይህ ቤተ-መቅደስ የተገነባበት ዘመን ከሌሎች ሲወዳደር በጣም አጭር ነው፡፡"

"ታሪካዊ ነው ያሉበት ምክንያት በደርግ መንግሥት የተገደሉት ጳጳስ የአቡነ ቴዮፍሎስ ሃውልትና መቃብር ስለሚገኝበትና ቤተ መቅደሱን ያሠሩት ሚቹ ጳጳስ በመሆናቸው የጎብኝዎችን ቀልብ መሳብ ስለሚችል ይመስለኛል፡፡ በውይይታችን ወቅት የነገሩኝ ይህንኑ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ከሌሎቹ የአዲስ አበባ ገዳማት በሀብት ብዛቱ ተወዳዳሪ የሌለው በመሆኑም ሀብቱን ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው ሲሉ ያደረጉት ዘዴ ነው የሚል አስተያየትም ነበር፡፡"

"ከነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ውጭ ሌላ የገቢ ምንጭ አለ ማለት ነው?" አለው ዘሩባቤል፡፡

"በአራት ኪሎ ሁለት ባለ አራት ፎቅ ዘመናዊ ሕንፃዎች አሉት፡፡ እያንዳንዳቸው በወር እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ ኪራይ የሚሰበስብባቸው ናቸው፡፡"

"በቤተክርስቲያኑ ስም የተሠራ ሕንፃ አለው እያልከኝ ነው?" በአትኩሮት አስተዋለው የመረጃ መኮንኑ፡፡

"ከዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ያሉት በወንዝ ጠጠር የተለሰኑ ውብ ዘመናዊ መንታ ሕንፃዎች ለዚሁ ቤተክርስቲያን ሚቹ





ጳጳስ ያሠሯቸው ናቸው፡፡ የሕንፃዎቹ ኪራይ እየተሰበሰበ ገቢ የሚደረገው ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ግምጃ ቤት አልነበረም፡፡ በደርግ መንግሥትም ወደ ቤተ ክህነት ሳይጠቃለል እራሱን በራሱ እያስተዳደረ ነው የቆየው፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ሌሎች አድባራትን ይረዳል እንጅ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚፈልገው ምንም ነገር የለም፡፡ በሀብት ደረጃውም ቢሆን ከቁልቢ ገብርኤል ቀጥሎ የሚገኝ ነው የሚል ግምት አለ፡፡"

"ገቢው አሁንም እንደዚያው ነው የቀጠለው?" ሲል ጠየቀው የመረጃ መኮንኑ፡፡

የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪው እራሱን በተቃውሞ ከፍና ዝቅ አደረገ፡፡

"ከብዙ ውዝግብ በኋላ የልደታ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ በቤተ ክህነት ስር እንዲሆኑ ቢደረግም የተሳካው ከብዙ ችግር በኋላ ነበር፡፡ የዚህ መረጃ ዝርዝር በቢሮአችን ስላለ ፋይሉን አውጥተህ ልትመለከተው ትችላለህ" እሩቅ እያሰበ መለሰለት፡፡

"እነዚህ ሁለት ገዳማት ከሌሎቹ ገዳማትና አድባራት መለየት የፈለጉት ለምን እንደ ነበር የሚታወቅ ነገር ይኖር ይሆን?"

"በዚህ ዙሪያ የደረሰኝ መረጃ የለም፡፡ ከእምነት ጋር የተገናኘ በመሆኑ እያንዳንዱን ዝርዝር መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ በወሬ ደረጃ የቤተ ክርስቲያኑን ሀብት እንዳይባክን ለመጠበቅ ነው ከቤተ ክህነት ጋር ገቢያቸው እንዳይጠቃለል የተደረገው የሚል የሕዝብ አስተያየት አለ፡፡"

"ጥሩ" አለ በረጅሙ እየተነፈሰ፡፡ "ለማንኛውም ቀሪውን ወደ ፊት የምናየው ስለሆነ ከዚህ ላይ ይበቃናል፡፡"

የድምጽ መቅረጫ መሣሪያውን ዘጋና የመጥሪያ ደውሉን ሲጫነው ሁለት የጸጥታ ፖሊሶች ተከታትለው ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ በዓይኑ ምልክት ሲሰጣቸው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊውን ከተቀመጠበት ግራ ቀኝ አንጠልጥለው ይዘውት ሲወጡ የመረጃ መኮንኑን ፊት በጥላቻ አስተዋለው፡፡

በሁለቱ ሰዓት ደግሞ ከአሜሪካ ቆንስላ ቅጥር ግቢ በተቋቋመው ጊዜያዊ የኢንተርፖል ጽሕፈት ቤት የተቀመጡት የመምሪያ ኃላፊዎች በየቀኑ ከሚመጣላቸው ሪፖርት ብዛት ዓይናቸው እንቅልፍ ከነጠፈ ወራትን አስቆጥሮ ፊታቸው ገርጥቷል፡፡

"ለነገሩ ፍንጭ እየተገኘ ይመስለኛል" አሉ የጸሐፊያቸውን የገረጣ ፊት እየተመለከቱ የቡድኑ መሪ ኮሎኔል፡፡

"እንደዚያ ይመስላል" አለ ጸሐፊያቸው፡፡ "የኢትዮጵያ ጸጥታ ሠራተኛ አመርቂ የሆነ ሥራ ላይ ነው" አለ፡፡

"በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ያለ ይመስለኛል፡፡ ወደ ዋናው ጉዳይ እየተቃረበ ነው" አሉ ኮሎኔሉ፡፡

"ጠበቅ ያለ ምርመራ ከተደረገበት አንድ ፍንጭ ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ" አለ ረዳታቸው፡፡

"እንደዚያ ይመስለኛል" ሲሉ መለሱለት።

"የተያዘው የፅጥታው ኃላፊ ከወሮበላዎቹ ጋር ግንኙነት ስለነበረው መንገድ የሚከፍት ይመስለኛል።"

"ምርመራውን ጠበቅ አድርገው ከያዙት እንዳልከው አንድ ፍንጭ መገኘቱ የማይቀር ነው። ለማንኛውም የእኛን ሰው ደውለህ ትጠራልኝና እንድንገናኝ ታደርግልኛለህ። በዚህ ዙሪያ በደንብ መነጋገር አለብኝ" አሉት።

"ደውዬለት ነበር" አለ ጸሐፊያቸው።

"እንዴት ለምን ጉዳይ ነበር የደወልክለት?" አሉ ግር ብሏቸው።

"ደውልና አገናኘኝ ብለው ነበር እኮ እረሱት እንዴ?" አለ ጸሐፊያቸው፡

የመምሪያው ኃላፊ ሃፍረት ቢጤ የተሰማቸው መሰሉ።

"ይቅርታ ረስቼው ነው። ሪፖርትም ደርሶኛል። ለማንኛውም ደግመህ ደውልለት። ነገሩ ወደ ጫፍ እየደረሰ ስለ ሆነ በትኩረት መከታተል ይኖርብናል። ጡዘቱ ሲፈጥን እኛም መፍጠን አለብን" አሉት።

"ከሰዓት እንደሚመጣ ነው ቀጠሮ የሰጠኝ ሁሉንም ነገር በቅርብ ይከታተለዋል የሚል እምነት አለኝ" አለ ጸሐፊው።

"የደኅንነት መዋቅሩ አሠራር የተጠናከረ ይመስላል።"

"ትክክል ነዎት በጣም የተሻለ ለውጥ እየመጣ ነው። ብዙ ነገሮችን እየፈለፈለ በማውጣት ላይ ነው ያለው።"

"በዚህ ከቀጠሉ በቅርብ ቀን የነገሩ አስኳል ይገኛል የሚል እምነት አለኝ። ከሚደርሰን መረጃ እንደ ተረዳሁት የሁሉም ነገር ጫፍ እየተገኘ ነው። እንቅልፍ የለም በርትታችሁ ተከታተሉ" ሲጋራ ፍለጋ ወደ ኪሳቸው ገቡ።

"አደጋ ላይ ተኝተን እንዴት ነው የምናቀላፋው?" አለ ጸሐፊው።

"በየደቂቃው የሚመጡትን መረጃዎች እየተቀበልክ አድርስ። ማንም ሰው መተኛት የለበትም። የአበሾቹ የጸጥታ መሥሪያ ቤት በጣም እየፈጠነ ስለሆነ እኛም ጡዘቱን ተከትለን መሽከርከር ይኖርብናል። በጣም ፍጠኑ" ሲጋራ ሲያቀጣጥሉ እንዳሰናበቱት ገባውና ከተቀመጠበት ተነሳ ረዳታቸው።





# ምእራፍ ሃያ አምስት

"ዓለም ምን እንደሚል ሳስብ ይገርመኛል" አለ ኢንጂነሩ ራሱን እያሻሸ።

"ምንም የሚያስገርም ነገር አይኖርም። አሁን የምንመለከተው የሰው ዘር ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ከሌሎች ፍጡራን መዳቀል የተገኘ ነው ተብሎ ይታመናል። ዘመኑ እየራቀ ሲመጣ ሁሉም ነገር ወደ ተረት እየተቀየረ ነበር፣ አሉ እየተባለ ይተረክለታል። ለምሳሌ በቻይና ግዛት በአንድ ወቅት የተገኙት ሰው መሰል ፍጡራን በአንድ ወቅት ከዮፎዎች የተዳቀሉ የሰው ልጅ ዝርያ እንደ ሆኑ ይገመታል።"

"በቻይና ተገኙ የተባሉት የሰው ዝርያዎች አሁን ካለው የሰው ልጅ ዝርያ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ሊያስረዱን የሚችሉ ምንም የሥነ-ፍጥረት መረጃዎች የሉም።" አለ ኢንጂነሩ።

"የሚመሳሰሉበትም የሚለያዩበትም መንገድ ስላለ ከሚመሳሰሉበት ብንነሳ በ 1960ዎቹ መጀመርያ ላይ በቻይና ግዛት በአንድ ተራራማ አካባቢ እቋማቸው የሰውን ልጅ የሚመስል ቁመታቸው ከሰው ቁመት በጣም በብዙ ልዩነት የረዘመ ፍጡራን መገኘታቸውን ሻንጋይ የተባለው ጋዜጣ በአምዱ ይዞ ብቅ ብሎ ነበር። ጋዜጣው እንዳሰፈረው ከሆነ ፍጡራኑ እቋማቸው የሰውን ቢመስልም አካላቸው በጸጉር የተሸፈነና ጸጉራቸው ከሰውም ሆነ ከእንስሳ እንደማይመሳሰል ያብራራል።

ስለ ፍጡራኑ ጸባይ ሲጠቅስም በጣም ፈጣንና በሰዓት ብዙ ኪሎ ሜትሮችን መሮጥ የሚችሉ የሰው የሚመስል ሳቅ ለረጅም ጊዜ የሚስቁ ናቸው ይላል። እነዚህ ፍጡራኖች ከሰው ዝርያ የተዳቀሉ ናቸው የሚል መላምት በወቅቱ እንደ ነበር አስታውሳለሁ።"

"እነዚህ ፍጡራኖች በአሁን ወቅት ሊኖሩ ይችላሉ? ከሆነስ በየትኛው ክፍለ ዓለም ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል?"አለ ኢንጂነሩ።

"ስለነዚህ ፍጡራን መኖሪያ በትክክል የተቀመጠ ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ለማግኘት ብዙ የተደከመበት ቢሆንም ከግምት በስተቀር ይህ ነው ተብሎ የተረጋገጠ መረጃ ማግኘት አልተቻለም። ለምን ቢባል መኖርያቸውን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ይዘትና ቅርጽ ጭምር እንደ ፈለጉ መለዋወጥ ስለሚችሉ ፍጡራኑ የእነሱ ዲቃላ ሳይሆኑ አይቀሩም ተብሎ ታምኗል።"

"በተደጋጋሚ ብቅ የሚሉት ፍጡራንን ምንነት ለማወቅ የተደረገው የሳይንስ ሙከራ እስከ አሁንም ድረስ ውጤት ማስገኘት አልቻለም የሚል መላምት አለ። ከሰው ልጅ ጋርም ስለአላቸው አሉታዊ አለዚያም አወንታዊ ክስተት ለመረዳትም የሰው ልጅ በአገኘው መጠነኛ የእውቀት ብልጭታ የእነሱን ምንነት ለመረዳት የተለያየ ሙከራ ማድረጉ ይታወሳል።